# የማኅሌተ ጽጌ ትርጉምና ታሪክ፤

## ክፍል ሁለት

### ሁለተኛ እትም !!

ድንግል ሆይ እግዚአብሔር፣ አንቺን ባያስቀርልን ኖሮ
እንደ ሰዶም በሆን፣ እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር፤
ገጽ 6

ትርጉም ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያብል

አዘጋጅ ይርጋለም ወሰኑ


ዓለም አታሚዎች ታተመ።

አዲስ አበባ

ግንቦት አንድ ቀን ፳፻፬ (2004) ዓ.ም።



www.ethiopianorthodox.org

23 ድንጋዩ ማንን መስሎ ተመታ?.................................. 52

24 ተጋቢኦሙ በደመና ሰማይ (ሐዋርያት በሰማይ ተሰብስበው ምን አዩ?) .............................................. 55

25 እመቤታችን፣ የታዴዎስ የስንዴ እሸት እንዴት ተባለች?.......... 56

26 እመቤታችን፣ የበርተሎሜዎስ ወይን እንዴት ተባለች?............. 57

27 ከሞት የተነሡ ወንድማማች፣........................................ 59

28 የሥልጣነ ክህነት፣ ኃይል.............................................. 60

29 እመቤታችን፣ የጊዮርጊስ ምልክትና የሞቱ መታሰቢያ ለምን ተባለች?.................................................................. 63

30 ሁለት እስጢፋኖሶች፣ የመጀመሪያ ሰማዕታት እንዴት ተባሉ?... 64

31 ሰውንና ወፍን፣ ስለሚያስወልድ ተአምረኛ ድንጋይ............ 65

32 ስለ ሰማዕቱ ፊቅጦር፣.................................................. 65

33 በተገፈፈ ቆዳው ሙት ስላስነሳው ሰማዕት ...................... 66

34 በሃይማኖት፣ተራራን ስለማፍለስ.................................... 68

35 እመቤታችን፣ በኢያሪኮ ዳርቻ ስላደረገችው ተአምር............ 70

36 በብርሃን ስለታጀበው ልጅ፣........................................... 71

37 የተቆረጠች እጅ፣ በቅዳሴ ጊዜ ስለማብራቷ....................... 72

38 ስለ መልእክተኛው ወፍ................................................. 73

39 ወርቅን የያዘ ዓሣ......................................................... 74

40 እመቤታችን፣ በቃና ሰርግ፣ ወይን እኮ! አልቀባቸዋል ያለችበት ምሥጢር ........................................................... 75

41 ውሃውን ባርኮ፣ ኅብስት ስላደረገው ጻድቅ...................... 77

42 ድንጋዩ፣ ወርቅ መስሎት ሃይማኖቱን ስለካደ ሰው.............. 79

43 ጌታ፣ ሴቲቱ ሽቱውን ለመቃብሬ ጠበቀች ለምን አለ?......... 83

44 ከአነጋገር ጉድለት፣ የመጣ መቅሠፍት.............................. 84

45 ዋቢ መጻሕፍት ............................................................ 86

46 ምስጋና ..................................................................... 88




፶.50 አይኑ ዘተገብረ ፈውስ፣
እንበለ (እምቅድመ) ትትወለዲ ድንግል እምቤተ ክህነት ወንግሥ፣
መድኃኒተ (መድኃኔ) ዓለም ኮነ ደመ ጽጌኪ ክርስቶስ፣
እሰግድ ለተአምርኪ በአብራከ ሥጋ ወነፍስ፣
በከመ ሰገደ ለኪ (ለወልድኪ) ዮሐንስ በከርሥ::

*ድንግል ሆይ ከቤተ ክህነትና ከቤተ መንግሥት (ከነገደ ሌዊና ከነገደ ይሁዳ) ሉቃ.22.12-23፣ ዕብ.7.5-15 ከመወለድሽ በፊት ምን የተደረገ ድኅነት አለ? (ምን ሕይወት ነበረ?) በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን ተብሎ ትንቢት እንደ ተነገረ ኢሳ. 53.4-7.*
*የልጅሽ የክርስቶስ ደም፣ የዓለም መድኃኒት (ዓለምን የሚያድን)፣ ሆኗልና፣ ኤፌ. 2.13-14፣ 1ኛ ዮሐ. 1.7-8. ዮሐንስ በማሕፀን ሳለ ለአንቺና ለልጅሽ እንደሰገደ፣ ሉቃ. 1.41. ጉልበትም ሁሉ ለእኔ (ለጌታ) ይንበረከካል እንደተባለ ኢሳ.45. 23-24፣ ፊልጵ. 2.10-12. ለተአምርሽ (ተአምርን ለሚያደርግ ልጅሽ) በነፍስና በሥጋ እሰግዳለሁ::*

ስግደት፣ ስንት አይነት እንደሆነ በክፍል አንድ፣ ገጽ 103 ላይ ተገልጿል::

፶፩- 51 ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ፣
እግዚአብሔር ኢያኪ እመ ኢያትረፈ ለነ፣
በትረ ተአምር ማርያም እንተ ጸገይኪ መድኅነ፣
ዘይቤ ኢመጻእኩ እጸውዕ ጻድቃነ፣
አላ ለንስሐ ኃጥኣነ::

*ጻድቃንን እጠራ ዘንድ አልመጣሁም ኃጥኣንን ወደ ንስሓ ልመልስ መጣሁ እንጂ ብሎ እንደተናገረ ማቴ.9.13.*

---

(1) *ለሥጋ - ሕይወት፣* ረቂቅ አካል ሆና የተፈጠረች ነፍስ፣ ዘፍ. 2.7-8፣ በኀ ሥራ ልትሠራ ትወዳለች፣ማቴ.26.40-42::


www.ethiopianorthodox.org

*ዓለምን የሚያድን ጌታን የወለድሽልን የተአምር ብትር ማርያም ሆይ በአዳምና በሔዋን ምክንያት ከመጣ መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስ ዘፍ.3.10-20. እግዚአብሔር፣ የምንድንብሽ አንቺን ያስቀረልን ባይሆን ኖሮ፣ እንደ ሰዶም በሆን፤ እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር ኢሳ. 1. 9. ሮሜ.9. 29::* (ሐተታ) እመቤታችንን፣ እግዚአብሔር አንቺን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆን፣ እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር ማለቱ፣ ጌታ አንቺን ከመርገመ ሥጋ፣ ከመርገመ ነፍስ ጠብቆ ከአንቺ ባይወለድ ኖሮ ዓለም ከፍዳ ባልዳነም ነበር ማለቱ ሲሆን፣ የተአምር በትር ነሽ ማለቱም፣ የአሮን ብትር ውሃ ሳትጠጣ፣ በተአምር አብባና አፍርታ እንደተገኘች ዘኁ.17.1-11 እመቤታችንም ያለዘር ጌታን ፀንሳ መውለዷን የሚያስረዳ ነው፣ ማቴ.1.18-25:: በ1948 ዓ.ም የታተመውና መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ የተባለው የኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት እንደተናገረውም፣ እግዚእ ማለት፣ ገዝአ ገዛ፣ ጌታ ሆነ፣ ከሚለው ግእዝ የተገኘ ሲሆን፣ ብሔር ማለት ደግሞ፣ ዓለም ማለት ነው፣ በዚህ መሠረት እግዚአብሔር ተብሎ በአንድ ሲነበብ የዓለም ገገር፣ የዓለም ጌታ፣ ዓለምን የፈጠረ ማለት ነው::

፶፪- 52 እመ ተሰቅለ ቍልቍሊተ ወተተክለ በርእሱ፣
እንበለ ረድኤትኪ አልቦ ዘይክል አድኅኖተ (አድኅኖ) ነፍሱ፣
አኮ ድንግል በፈጽሞ ቃላት ስሱ፣
ለተአምርኪ ከመ ይትነከር ሞገሱ፣
በገነተ ጽጌ ሢምኒ ምስሌኪ አንሶሱ::

*ድንግል ሆይ ተዘቅዝቆ ቢሰቀልና በራሱ ቢተከል ያለ ረድኤትሽ ነፍሱን ማዳን የሚችል የለም፡ ብራብ አበላችሁኝ፤ ብጠማ*

(2) ሥጋ፣ ደካማ ነውና፣ ወደ ክፉ ሥራ እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ ማቴ. 26.40-42::



*እንግዳ ብሆን ተቀበላችሁኝ፤ ብታረዝ አለበሳችሁኝ፤ ብታመም ጠየቃችሁኝ፤ ብታሰር ጎበኛችሁኝ የሚሉ ስድስቱ ትእዛዛትን (ስድስቱ ሕጎችን) በመፈጸም ብቻ አይደለም ኢሳ.58.7.9፣ ሕዝ.18.7-10. ማቴ. 25. 35-37. የተአምርሽ ክብር ይገለጽና ልጅሽ ባዘጋጃት ገነት ከአንቺ ጋር እኖር ዘንድ አድዪኝ እንጂ::*

፶፫-53 ከመ ታቦት ሥርጉት በወርቀ ዓረብ ወተርሴስ፣
በድንግልና ማርያም ሥርጉተ ሥጋ ወነፍስ፣
ተአምረ ነቢር አርአይኪ በቤተመቅደስ፣
ኢያቄም ወሐና ቀንሞስ ቀናንሞስ፣
እምዘጸገዩኪ ለጳጦስ በዓመት ሠላስ::

*ጥሩ በሆነ በዓረብ እና በተርሴስ ወርቅ (ተርሴስ፣ ቢረሌ፣ በተባለ ዕንቍ መኃ.5.14፣ ሕዝ.1.16) እንዳጌጠች ታቦት ዘጸ. 25. 1-23፣ ዕብ 1.9.4 በሁለት ወገን (በነፍስና በሥጋ) ንጽሕት የሆንሽ ማርያም ሆይ ሙሴ፣ ጳጦስ ለምትባል ቍጥቋጦ፣ ዘፀ-3.2-4፣ አሮን ያለ ውሃ ለበቀለችና ላፈራች ብትር ምሳሌ ሆነሽ፣ ዘኁ 17. 1-12. በትንቢት መነጽር በአዩሽ በ3ኛው ሺህ ዓመት እና መዓዛው ደስ ከሚያሰኝ ቀንሞስ፤ ቀናንሞስ ከሚባል ሽቱ የከበሩ ኢያቄምና ሐና አንቺን በወለዱሽ በ3ተኛው ዓመት፣ ለቤተ መቅደስ ከሰጡሽ ዘንድ በቤተ መቅደስ የመኖርን ተአምር አሳየሺ::*

(ታሪኩ) ሙሴና አሮን፣ እመቤታችንን በትንቢት መነጽር ባይዋት በ3ኛው ሺህ ዓመት እና በተወለደች በ3ኛው ዓመት፣ ታኅሣሥ (3) ቀን ኢያቄምና ሐና ለቤተ መቅደስ ስእለት መስጠታቸውንና በቤተ መቅደስ መኖሯን የሚገልጽ ነው::

፶፬-54 ያፍኒ ረከበት ቤተ ለኑባሬ፣
እሴብሐኪ እንዘ እብል በመዝሙረ ዳዊት ወውሉደ ቆሬ
(ዘውሉደ ቆሬ)፣

(3) የመንፈስ ፍሬ ፍቅር፣ ሰላም፣ እምነት፣ በጎነት፣ ይህን የመሰለ ሁሉ ነው ገላ.5.22::

www.ethiopianorthodox.org

ተአምርኪ ማርያም ዘትጸጊ ሕገ ዝማሬ፤
ትመስል ዕፀ ዘባቲ ኅበ ሙሐዘ ማይ ሠራሬ፤
በበጊዜሃ እንተ ትሁብ ፍሬ።

ማርያም ሆይ በዳዊትና በቆሬ ልጆች ምስጋና (የቆሬ ልጆች በሚያመሰግኑት በዳዊት ምስጋና)፤ በርግብ የተመሰለች ማርያም፤ መኖሪያ ቤትን (ቤተ መቅደስን) አገኘች እያልኩ አመሰግንሻለሁ፤ መዝ83.3፤ ሆሴ.11.10. በአበባ የተመሰለ ምስጋና ሕግን የምታብብ ተአምርሽ፤ በየጊዜው ፍሬዋን የምትሰጥና በውሃ ዳር የበቀለች ዛፍን ትመስላለችና።ዘፍ. 49. 22. መዝ.1.3-4።በየጊዜው ፍሬዋን የምትሰጥ ዛፍ የተባለችም በሀገራቸው ለውዝ፤ በሀገራችን ሎሚ (ትርንጎ) ናት። እመቤታችንንም በየጊዜው የተነሱ የቃል ኪዳን ልጆቿ እንደ ኤልሳቤጥ የማሕፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው ሲሏት ይኖራሉና ነው። ሉቃ1. 41-43. በዳዊትና በቆሬ ልጆች ምስጋና አመሰግንሻለሁ ማለቱም ለንጉሥ ዳዊት ከ288 በላይ መዘምራን ነበሩት፤ የነዚህ አለቆችም ቆሬ፤ ኤማን፤ አሳፍ፤ ኤዶትም (ኤታን) ይባላሉ፤ እነዚህም የዳዊትን መዝሙር ከአራት ተካፍለው ይጸልዩ፤ በከበሮና በጽናጽል፤ በዜማም ያመሰግኑ ነበር፤ ከመዘምራን አለቆችም አንዱ ቆሬ ነበረና፤ መዝ.41፤ 1ኛ.ዜና.መዋ. 15.16-19።

ጃ፰-55 የኀዝነኒ ማርያም ዘረከበኪ ድክትምና፤
አመ ቤተ መቅደስ ቦእኪ እንዘ ትጠብዊ ሐሊበ ሐና፤
ወያስተፌሥሐኒ ካዕበ ትእምርተ ልሕቀትኪ በቅድስና፤
ምስለ አብያጺሁ ከመ አብ እንዘ ይሴስየኪ መና፤
ፋኑኤል ጽጌ ነድ ዘይከይድ ደመና።

*ማርያም ሆይ የሐናን ወተት እየጠባሽ ወደ ቤተ መቅደስ በገባሽ ጊዜ ያገኘሽ ድህ አደግነት (ብቸኝነት) ያሳዝነኛል፤ በደመና የሚመላለስ የእሳት አበባ የሆነ ፋኑኤል ከመላእክት ጋር መናን እየመገበሽ በንጽሕና የማደግሽ ተአምር ግን ደስ ያሰኘኛል።*

ፋኑኤል፤ የእሳት አበባ ነው ማለቱ፤ የመላእክት ተፈጥሮ እምኀበ አልቦ ኀበቦ፡ (ምንም አይነት ተጨማሪ ምክንያት ከሌለበት

(4) በመንፈስ ተመላለሱ (የነፍስ ፈቃድ፤ በጎ ሥራ ነውና፤ በነፍስ ፈቃድ ኑሩ) ገላ.5.16-18።



ከአምላካዊ ብርሃን ነው። ስለርቀታቸውና ስለ ፍጥነታቸውም፤ በእሳትና በነፋስ ይመስላቸዋልና ነው። መዝ.103.4-5።

## መናፍቃን ሴቶች ቤተመቅደስ አይገቡምና፤ ማርያም እንዴት ገባች ለሚሉት ማስረጃ

መናፍቃን፤ ሴቶች ቤተመቅደስ አይገቡምና፤ ማርያም ቤተመቅደስ ገብታ ኖረች ማለት አይቻልም ለሚሉት ትሩፋ መልስ፤ ቤተመቅደስ የመግባትና ያለመግባት ጉዳይ በእግዚአብሔር የመመረጥና ያለመመረጥ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ድንግል ማርያም (ቤተመቅደስ) ገብታ እንደምትኖር እርሷ ከመወለዷ በፊት፤ጌታ ምሥጢሩንና ምሳሌውን አስቀድሞ ገልጿል። ይህም ጌታ በሙሴ አማካኝነት ብዙ ብትሮች በድንኳኑ (ቤተመቅደስ) ገብተው እንዲወጡ ባደረገ ጊዜ የአሮን ብትር ውሃ ሳትጠጣ በተአምር ለምልማና አብባ፤ መልካም ፍሬንም አፍርታ እንድትታይ ማድረጉ እና ለሚያምፁብኝ ልጆች ምልክት ሆና ትጠበቅ ዘንድ፤ ብትሯ በቤተ መቅደስ ትኑር ማለቱ ነው፤ ዘኍ.17.1-12። ስለዚህ የእግዚአብሔር ይቅርታው በደረሰ ጊዜ፤ መዝ. 68.13-14፤ 118.126፤ ወተወልደ እምብእሲት ‹‹ከሴት ተወለደ ብሎ›› ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረና ገላ. 4.4. ይህንንም ቃል ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ድጓ በተባለ ድርሰቱ ዘእንበለ ዘርዕ ሠረፀ፤ ወኢኀፈረ ተወልደ እምብእሲት፤ እንዘ አኃዜ ኃይል ኃይል ለኩሉ ፍጥረት፤ ‹‹የፍጥረት ሁሉ ጌታ ኃይልን ሁሉ የያዘ ሆኖ ሳለ ያለዘር ከሴት›› ተገኘ፤ ከሴት (ከድንግል ማርያም) መወለድንም አላፈረም ብሎ እንደተረጎመው፤ የመቅደሱ ባለቤት የሆነ ጌታ ከሴቶች ሁሉ ብቻዋን ለይቶ እናት ትሆነው ዘንድ የመረጣት ድንግል ማርያም፤ በቤተ መቅደስ እንድታድግ እና በቤተ መቅደስ በንጽሕና፤ በቅድስና ያደገ ሥጋዋን እስኪለብስ ድረስ በቤተ መቅደስ ኖረች። ጌታ ለሚያምፁብኝ ልጆች ምልክት ሆና ትጠበቅ ዘንድ ብትሯ በቤተ መቅደስ ትኑር ማለቱም፤

(5) የሥጋን ምኞት ሁሉ አትፈጽሙ፤ነፍስ [illegible] ይሠራልና ገላ.5.16-22፤ሲራ.17.31።

www.ethiopianorthodox.org

ገጽ-57 እምገነተ መጽሐፍ እቀሥም ተአምረኪ ለነቢብ፣
ለገቢረ መዓር ጽጌ በከመ ይቀሥም ንህብ፣
በአሳዕንኪ ማየ ዘአስተይኪዮ ለከልብ፣
ታስትዩኒ እምሮማንኪ ጊዜ ሰዓተ ጽምዕ ዕፁብ፣
ተራኅርኒ ማርያም የዋሂት ርኅብ።

[illegible] ውሻን በጫማሽ ውሃ ያጠጣሽው መልካሟ ርግብ ማርያም ሆይ [illegible] ማርን ለመሥራት አበባን እንደሚቀስም (እንደሚሰበስብ) [illegible] ቦታ መጽሐፍ፣ ተአምርሽን ለመናገር እቀስማለሁ (እሰበስባለሁ)፣ በሚያስጨንቅ ውሃ ጥም ጊዜም ከመዓዛ ረድኤትሽ [illegible] ዘንድ ራሪልኝ።

## [illegible]ን፣ ማርያም የተበሠረች በዮሴፍ ቤት እንጂ በቤተ መቅደስ አይደለም ለሚሉት ማስረጃ

[illegible] እመቤታችን፣ በዮሴፍ ቤት ሳለች ውሃ ለመቅዳት ወደ ወንዝ [illegible] መለስ የተጠማ ውሻን አይታ በጫማዋ ውሃ ባጠጣቺው [illegible] የነበሩ ሴቶች፣ አምላክ ይወለዳል የሚባል ከአንቺ [illegible] አያሉ ሲዘባበቱባት እና ከብዙዎችም አንዷ ሴት፣ ማድጋሽን [illegible]) አጎደልሽ፣ መቅጃም የለሽ፣ ውሃውም የጉድጓድ ውሃ ነው [illegible] እመቤታችን ግን ውሃስ ከጉድጓድ የሚወጣ አይደለም፣ [illegible] እግዚአብሔር እንጂ አለች፣ በዚህ ጊዜ ጌታ ማድጋዋን [illegible] ሞልቶላታል፣ ይህን የትሕትና ቃልም ምክንያት አድርጎ፣ [illegible] ብርኤል ትፀንሻለሽ ብሏታል፣(19 ተአምረ ማርያም)። [illegible] ገብርኤል ማርያምን ያበሠራት በዮሴፍ ቤት እንጂ [illegible] ውሃ ስትቀዳ እና ውሃውን ስታወርድ፣ [illegible]ስም፣ ተበሠረች ማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ [illegible]ሚሉት ትፋቂ ግን፣ ታሪኩ ከላይ እንደተገለጸው

[illegible]



1ኛ. ድንግል ማርያም ከቀዳችው ውሃ ለተጠማ ው[illegible]
ትጸንሻለሽ ብሎ አብሥሯታል፣

2ኛ. የቀዳችውን ውሃ ከቤት ስታወርድ ትጸንሻለሽ ብሎ
አብሥሯታል፣

3ኛ. ነገር ሁሉ በሁለት (በሦስት) ምስክሮች ይፀና[illegible] የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ታውቅ ነበርና፣ ዘዳ.[illegible] ነገረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ እንደተናገረው፣ [illegible] ደጋገመኝ እናቴ ሔዋንን ያሳተ ሰይጣን ዘፍ.3.1-8. [illegible] መጥቶ ይሆን? እስቲ ከቤተመቅደስ ሄጀ ልረዳው (ላረጋግጥ) ብላ፣ ከቤተመቅደስ ሄዳ ለቤተመቅደስ የሚሆን መጋረጃን ስትፈትል አብሥሯታል። እሷም በዚህ በ3ኛው ቃል፣ ቅዱስ ገብርኤልን እንደ ቃልህ ይሁንልኝ ስትል፣ ወዲያው አካላዊ ቃል በማህፀኗ አደረ። ስለዚህ ውሃ የቀድታ ስትመለስ፣ ውሃውን ከቤት ስታወርድ፣ ከቤተመቅደስ አስሠራት የሚሉት እነዚህ ሦስት ታሪኮች የተለያዩ አይደሉም፣ ምክንያቱም

1ኛ. ውሃ ልትቀዳ ወደ ወንዝ የወረደች፣ ከዮሴፍ ቤት ነውና፣

2ኛ. ውሃውን ያወረደች፣ ከዮሴፍ ቤት ነውና፣

3ኛ. በቤተመቅደስ የተበሠረችው ነገሩን ለማረጋገጥ ስትል ወደቤተመቅደስ የሄደች፣ ከዮሴፍ ቤት ነውና። ሦስት ጊዜ ስመበሠሯም በቂ ማስረጃ የሚሆነን ደግሞ፣

1ኛ. መልአኩ ገብርኤል ደስ ይበልሽ ጌታ ከአንቺ ጋር ነውና ሲላት፣
ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው ማለቷ፣

2ኛ. መልአኩ ገብርኤል ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ
ሲላት፣ ወንድ ሳላውቅ ይህ (መጽነስና መውለድ) እንዴት
ይሆንልኛል ማለቷ፣

(9) ሥጋውንና ደሙን ስንቀበል ይህ ሥጋና ደም፣ ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው ብለን በማመን ነው፣ ደም ከአለ ዘንድ ነፍስ አትለይምና ጥሬውን (ቀዩን ሥጋ) አትብሉ ከሚለው ከዘጸ.12.9-10. እንደምታ ትርጓሜ የተወሰደ።

www.ethiopianorthodox.org

3ኛ. መልአኩ ገብርኤል መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል (መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል) ሲላት፣ ነገሩን በዚህ በ3ኛው ብሥራት አረጋግጣ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ (ይደረግልኝ) ማለቷና ጌታ፣ (3) ጊዜ የተናገረችውን ይህን ቃሏን ምክንያት አድርጎ በማሕፀኗ ማደሩ ነው፣ ሉቃ.1.28-39። እመቤታችን እጮኛዋ ዮሴፍ አብሯት እያለ፣ ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል ማለቷ የዘለዓለም ድንግልናዋን መግለጿ ነው።

ሂ፰-58 ከመ ጽጌረዳ በምድር ምስለ መዓዛ ወቅያሔ፣
ወከመ ፀሐይ በሰማይ ምስለ ሞቅ ወሡራሄ፣
እርእየኪ ማርያም ወእረክበኪ ውስተ ኵለሄ፣
(እርአይኪ ማርያም ወእርከብኪ ውስተ ኵለሄ)፣
ይቅጽባኒ አዕይንትኪ እለ ምሉዓት ርኅራኄ፣
ፈልፈለ ረባሕ ተአምርኪ ኀበ ይትቀዳሕ ርሄ።

ማርያም ሆይ ከመቅላትና (ቀይ ከመሆንና) ደስ ከሚያሰኝ መዓዛ ጋር በምድር እንደሚታይ አበባ፣ ከሙቀትና ከብርሃን ጋርም በሰማይ እንደአለ ፀሐይ ሆነሽ፣ በሁሉ ቦታ እንዳይሽ እና እንዳገኝሽ (አይሽና አገኝህ ዘንድ)፣ መዓዛ ያለው የክብር ምንጭ ተአምርሽ ወደ ሚቀዳበት ሥፍራ ርኅራኄን የተመሉ ዐይኖችሽ ያመልክቱኝ።

ሂ፱-59 ኀበ ይቀውም ፀሐይ ለሕልቀተ ወርቅ በማዕከላ፣
(ለኅልቀተ ወርኀ በማዕከላ)፣
በአርአያ ድንግል ነአስ ማርያም ርግበ ገሊላ፣
እንዘ ተሐቅፊ ሕፃነ ዘይፀድል እምሥነ ዕብላ፣
መንገለ ሰማይ አዕይንቲሃ አልዒላ፣
ተአምረኪ ነጸረት ሳቤላ።

የገሊላ ርግብ ማርያም ሆይ ፀሐይ በሰማይ ቆሞ በሚያበራበትና

(10) መጥምቁ ዮሐንስ፣ የነቢያት መጨረሻ ነቢይና የሐዲስ ኪዳን የመጀመሪያ መንገድ ጠራጊ (ሰባኪ) ነው ሚል.3.1-4፣ ማር.1.1-9።



የጨረቃ ብርሃን በማይታይበት በቀትር ጊዜ፣ በወርቅ ቀለበት መካከል ሆነሽና ሕፃን የሆነች ድንግል ሴትን በምትመስል መልክ፣ ከጨረቃ ብርሃን ይልቅ እጅግ የሚያበራ ሕፃንን ታቅፈሽ፣ ሳቤላ ዐይኖቿን ወደ ሰማይ አቅንታ ተአምርሽን አየች። (ሐተታ) እመቤታችንን የገሊላ ርግብ ማለቱ፣ ገሊላ ማለት ገለልተኛ መንደር፤ ዙሪያ ማለት ሲሆን እመቤታችን፣ በገሊላ በነበሩ ሕፃናት ሞት ምክንያት ከገሊላ ተነሥታ በረሃ ለበረሃ በስደት መንገላታቷን መናገር ነው።

## የወርቅ ቀለበት በሰማይ (የሳቤላ ራእይ)፣

(ታሪክ) ሮሜ በሚባል አገር የነገሠ ብልህ እና ደግ ንጉሥ ነበር፣ ሰዎችም እሱን ከመውደዳቸው የተነሳ ልንሰግድልህ እንወዳለን አሉት፣ እሱም እኔ ፈራሽና በስባሽ ሰው ነኝና፣ ይህ ለእኔ አይገባም አለ። በዚያው በሮሜ አገርም የምትኖር ሳቤላ የምትባል ብልህና ደግ ሴት ነበረችና፣ ወደ እርሷ ሄዶ ሰዎች ልንሰግድልህ ይገባል ያሉትን ሁሉ ነገራት፣ ሳቤላም ንጉሥ ሆይ እስከ (3) ቀን ድረስ ታገሠኝ፣ የሚሆነውን ሁሉ እኔ እነግርሃለሁ አለችውና፣ ጌታ ስለሚገልጽላት ነገር ሁሉ በጾምና በጸሎት ተጸምዳ (3) ቀን ቆየች። በ3ተኛው ቀንም ከቀኑ በ6 ሰዓት (በቀትር ጊዜ) ፀሐይ በሰማይ መካከል ቆሞ የወርቅ ቀለበት በንጉሡ እጅ ተይዞ፣ በወርቅ ቀለበቱ ላይም እንደ ፀሐይ የምታበራ ድንግል ሕፃን ሴት ተሥላበት፤ በክንድዋም ፊቱ ከብርሃናት ሁሉ የሚያበራ ሕፃንን ታቅፋ ራእይ አየች፣ ሳቤላም ንጉሡን ና! ወደ ሰማይ ተመልከት፣ አለችው፣ ንጉሡም ወደ ሰማይ ሲመለከት ሳቤላ እንዳየችው ሁሉ አየ፣ በዚህ ጊዜ ንጉሡ፣ ድንግሊቱ እና ሕፃኗ ምንድን ናቸው ብሎ ጠየቃት፣ ሳቤላም ድንግሊቱ ሕፃን እመቤታችን ናት፤ ሕፃኑም ሰማያዊ ንጉሥ

(11) ዮሐንስ፣ ፈጣሪውን በማጥመቁ ካህን ነው ማር.1.9-12።

www.ethiopianorthodox.org

ነው፤ ስለዚህ ሰማያዊ ንጉሥም ስግደት ይገባል ብላ ተረጉመችለት፤ ይህ ንጉሥም በዚህ የራእይ ተአምር እጅግ ተደንቆ ለፈጣሪ ዕጣንን አቀረበ፤ መሥዋዕትንም ሠዋ፤ ያን ጊዜ ንጉሡ መሥዋዕት ያቀረበበት ቦታም፤ እስከዛሬ ድረስ በሮም አገር የሰማያዊ ንጉሥ መሠዊያ እየተባለ ይጠራል፤ (182 ተአምረ ማርያም)::

ጽ-60 እግዚአብሔር ነጸረ ኵሎ ዓለመ፤
ወኢረከበ ማርያም ዘከማኪ እመ፤
ኪያሁሰ ጽጌ ዘእምከርሥኪ ተቀስመ፤
ዳዊትኒ አመረኪ እንዘ ይብል ቅድመ፤
ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ዳግመ፤
እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ አዳመ::

ማርያም ሆይ እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ አየ፤ (ተመለከተ) ነገር ግን እንደአንቺ ያለች እናትን አላገኘም፤ ዳዊትም ንጉሥ ክርስቶስ የማረ ደም ግባትሽን ወዷልና፤ (ከሥጋሽ ሥጋን ከነፍስሽ ነፍስን ነሥቶ ከአንቺ ይወለዳልና)፤ ልጄ ሆይ ትምህርቴን ፈጽመሽ ስሚ ቢል፤ ከማሕፀንሽ የሚገኘውን ጌታ ፀንሰሽ እንደምትወልጂ አስቀድሞ ትንቢትን ተናገረልሽ:: መዝ. 44.10-11:: ዳዊት፤ ከአባቱ ከእሴይና ከእናቱ ከሁብሊ ዓለም በተፈጠረ በ4253 ዓመት ሚያዝያ (3) ቀን ለአባቱና ለእናቱ (7ኛ) ልጅ ሆኖ ተወለደ መዝ. 50. ንባቡና ትርጓሜው:: 2ኛ. ዜና. መዋ. 2.15:: ዳዊት ማለት የተወደደና የተመረጠ ልበ አምላክ ማለት ሲሆን፤ መዝ.88.19-21 ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ነው፤ በተወለደ (በ30) ዓመቱም ጥቅምት (12) ቀን በእስራኤልም ነግሦ፤ (150) መዝሙርን ደረሰ፤ በዚህ መዝሙር ውስጥም የዘመኖቻችን መጠን (የሰው እድሜው) (70) ዓመት ነው ብሎ ትንቢት ተናግሮ ነበርና፤ መዝ. 89.10. በተናገረው ትንቢት መሠረት፤ በተወለደ (በ70) ዓመቱ ዐረፈ:: 1ኛ ነገ. 2.10-12):: (ሐተታ) ንጉሥ ዳዊትን ልበ አምላክ ከአሰኙት ትንቢቶችም አንዱ፤ የዘመኖቻችን መጠን (የሰው እድሜው) 70 ዓመት ነው ብሎ እንደተናገረ፤ (በ70) ዘመኑ ማረፉ ነው::

(12) ዮሐንስ፤ እውነተኛ መምህር (ሰባኪ) ሆኖ፤ በሰይፍ በመቆረጡ ሰማዕት ነው ማቴ.14.1-13::



ጽ፩- 61 ስብሐተ ፍቅርኪ ማርያም ኵሎ አሚረ፤
በልሳነ ኵሉ ይጸጊ ወኢይፈርሕ አባረ፤
ዘያረጥብ የብሰ ወያየብስ ባሕረ፤
እስመ ብኪ ጠለ ተአምር እንተ ርደቶ ነጸረ፤
ጌዴዎን ኀበ ሰፍሐ አምሳለኪ ፀምረ::

ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ምስጋና ሁል ጊዜ በሁሉ አንደበት ያብባል፤ ድርቅንም አይፈራም ፤ የብሱን ርጥብ፤ የሚያደርግና ባሕሩን የሚያደርቅ ነው፤ ጌዴዎን የአንቺ ምሳሌ የሆነ ፀምርን (ነጭ ባዘቶን) በዘረጋበት ሥርዓት፤ መውረዱን ያየው የተአምር ጠል (የሰማይ ካፊያ) አለሽና፤ (በአንች አለና)::

(ሐተታ) የእመቤታችን ምስጋና ድርቅን አይፈራም ማለቱ፤ ድርቅ እህሉንና ተክሉን፤ ቆርጦ ያስቀራል፤ የእመቤታችንን ምስጋና ግን ውዳሴ ከንቱ አይቀላቀለውም፤ ባሕርም አይገድበውምና ነው፤ ጌዴዎን የአንቺ ምሳሌ የሆነ ፀምርን (ነጭ ባዘቶን) ዘረጋ፤ የተአምር ጠልም (የሰማይ ካፊያ) በአንቺ አለ ማለቱም፤ ጌዴዎን የጌታን ተአምር ለመረዳት ፀምር በአውድማው ላይ ልዘርጋ፤ ጠልም በፀምሩ ላይ ይውረድ ዙሪያውም (ምድሩ) ደረቅ ይሁን ብሎ ጌታን በጠየቀ ጊዜ እንደተመኘው ተፈጽሞለታልና:: ጠሉ፤ በፀምሩ ላይ ብቻ መውረዱም፤ የጠሉ ምሳሌ የሆነ ጌታ ኢሳ.26.19-20 ከሌሎች ሴቶች በንጽሕና፤ በቅድስና የተለየች በሆነች በእመቤታችን ብቻ የማደሩ ምሳሌ ነው፤ መሳ.6. 37-40::

ጽ፪-62 ፈትለ ወርቅ ወፈትለ ሜላት አመ በአጽባዕትኪ ተባየጹ፤
አምሳለ መለኮት ወትስብእት እንዘ ኢየሐፁ፤
ተአምረ ብርሃን ማርያም ለፀሐየ ጽድቅ አንቀጹ፤
ጸገይኪዮ እንበለ አብ በሰሚዐ ቃሉ ወድምፁ፤
ለገብርኤል መልአክኪ ዘፍሡሕ ገጹ::

(13) መጽሐፍ ቅዱስ፤ ትርጓሜውም ቢሆን ዮሐንስን በሰይፍ ያስቆረጠችውን ወለተ ሄሮድያዳ (የሄሮድያዳ ልጅ) ብሎ ከመጥራት በቀር፤ ልዩ መጠሪያ ስሟን አልገለጸም ማቴ.14.6-13. ሆኖም የሄሮድያዳ ልጅ ልዩ ስሟ ማነው? ⟶

www.ethiopianorthodox.org

እውነተኛ ፀሐይ ለሆነ ጌታ፣ እናቱና የብርሃን ምልክት የሆንሽ ማርያም ሆይ እንደ መለኮትእና እንደ ትስብእት (እንደ እግዚአብሔርነት እና ሰው እንደመሆን) ምጆጢር፣ ተዋሕዶን (አንድነትን) ሳያጎድሉ፣ የሐርና የወርቅ ፈትሎች በጣቶችሽ በተፈተሉበት ጊዜ፣ ፊቱን ደስ ብሎት የተላከልሽ የገብርኤል ቃሉንና ድምፁን በመስማት ያለ አባት ጸነስሽው ሉቃ.1.26-39። (ሐተታ) የሐርና የወርቅ ፈትሎች፣ እንደ መለኮትእና እንደ ትስብእት ምሥጢር፣ አንድነትን ሳያጎድሉ በጣቶችሽ ተፈተሉ ማለቱ፣ ሐርና ወርቅ (ሁለቱ) በአንድነት ተፈትለው፣ አንድ ልብስ ሲሆኑ እንደሚስማሙ ሁሉ፣ መለኮትና ሥጋ፣ ተዋሕደው (ሁለቱ አንድ ሆነው) አምላክ ሰው ሆነ፤ሰው አምላክ ሆነ የሚለውን ምሥጢረ ሥጋዌ መግለጹ ነው። የቃልና የድምፅ ልዩነትስ ምን አይነት ነው ቢሉ? ቃል የነገሩን ፍሬነት ሲያመለክት፣ድምፅ ደግሞ ከቃል (ከአንደበት) የሚወጣውና በጆሮ የሚሰማው ነው። ታሪኩም እመቤታችን፣ በቤተመቅደስ ሐርንና ወርቅን እያስማማች ስትፈትል ቅዱስ ገብርኤል ትፀንሻለሽ ብሎ ያበሠራትና ጌታን የፀነሰችበት ነው።

ጃ፫-63 ዐቢይ ውእቱ ተአምር (ዐቢይ ውእቱ
ስብሐተ ተአምር) ጸግዮትኪ በድንጋሌ፣
ወፈርዮትኪ በንጽሕ ቍርባነ አምልኮ መጥለሌ፣
ማዕጠንተ ሱራፌ ዘወርቅ ወጽዋዐ ኪሩብ ዕንቈ ቢረሌ፣
አልቦ ጸሎት ወአልቦ ትንባሌ፣
እንበሌኪ ማርያም ዘየዐርግ ሉዓሌ።

ሱራፌ ለሚባል መልአክ የወርቅ ማዕጠንት፣ ኪሩብ ለሚባል መልአክም ቢረሌ የሚባል የዕንቍ ጽዋ የሆንሽ ማርያም ሆይ ራእ. 9.4. በንጽሕና መጽነስሽና የሚያስመልም የአምልኮ ቍርባንን (ሥጋውንና ደሙን) የሰጠ ጌታን መውለድሽ፣ (ምስጋና የሚገባው) ታላቅ ተአምር ነው፣ ያለ አንችም ወደ ፈጣሪ የሚያርግ ጸሎትና

(14) ዮሐንስን፣በሰይፍ ያስቆረጠችው የሄሮድያዳ ልጅ፣ ልዩ መጠሪያ ስሟ፣ ቅምጥራ እንደምትባል በገድለ አባ ሳሙኤል ዘወገግ፣ ግእዝና አማርኛ በምዕራፍ (33) ተገልጿል እትም 1998 ዓ.ም።



ምልጃ የለም። (ሐተታ) እመቤታችንን፣ ያለ አንቺ ወደ ፈጣሪ የሚያርግ ጸሎትና ምልጃ የለም፣ (ዐያርግም) ማለቱ፣ በብሉይ ኪዳን ድኅነት አለመገኘቱንና ጌታ ከእርሷ ከተወለደ በኋላ (በሐዲስ ኪዳን) ድኅነት መገኘቱን ለመግለጽ ነው፣ የሱራፌል (የካህናተ ሰማይ) ቍጥራቸው 24 ሲሆን፣ የጌታን ዙፋን እያጠኑ የሚያመሰግኑ መላእክት ናቸው፣ ኢሳ.6.3-5. ራእ.6.10. ኅዳር (24) ቀንም ይከብራሉ። ሱራፌ ማለት፣ የመልአክ ስም ሲሆን፣መጽሐፈ አክሲማሮስ እንደተናገረውም ሱራፌል ለሚባሉ መላእክት አለቃ ነው ኢሳ.6.2-6። ኪሩብ ማለትም፣የመልአክ ስም ሲሆን፣ ኪሩቤል ለሚባሉ መላእክት አለቃ ነው ሕዝ.10.1-20።

ጃ፬-64 ኦ፡ ዝ. መንክር በዘኪአኪ አምሳል፣
ኮከበ ትንቢት ዘቦቱ መልክአ ሕፃን ሥዑል፣
ሠረቀ ያርኢ ተአምረኪ ድንግል፣
ወመርሆሙ ለሰብአ ሰገል እምርኁቅ ደወል፣
ጽጌኪ ኀበ ሀሎ ይሰክብ (ሰኪቦ) በኀል።

ድንግል ሆይ የንጋት ኮከብ የተባለ ጌታ ከአንቺ በተወለደ ጊዜ ራእ.22.16 ምን አይነት ድንቅ ነገር ነው! በአንቺ አምሳል የተሣለና የሕፃን መልክ ያለበት የትንቢት ኮከብ፣ ዘኍ. 24.27. ተአምርሽን ይገልጥ ዘንድ ታየ፣ ሰብአሰገልንም ከሩቅ አገር ልጅሽ ተኝቶ ወዳለበት (ወደተወለደበት) በረት መርቷቸዋልና፣ ማቴ. 2.9-12።

## የትንቢቱ ኮከብ በስንት ዓመት ተገለጸ?

(ታሪክ) እመቤታችን ከመወለዷ ከ1520 እና ከጌታ ልደት (ከ1536) ዓመት፣ በፊት በለዓም የሚባል ፈላስፋ (ተመራማሪ) ነበር፣ ከዕለታት አንድ ቀን ከአዳም እስከ ሙሴ ዘመን ያሉትን ሰዎች የትውልድ ቍጥርንና ትንቢትን የያዘ መጽሐፍ አቅርቦ ሲመረምር፣ እመቤታችንን ባያት ጊዜ እርስዋ ድንግል ስትሆን ልጅዋ ክርስቶስን

(15) ሰዶምና ገሞራ፣ በዝሙት ምክንያት ዓለም በተፈጠረ በ3152 ዓመት በሐምሌ ወር በእሳት ተቃጠሉ፣ ኩፋ.12.51-53።

www.ethiopianorthodox.org

ታቅፋ፣ በአጠገቧም ታላቅና ብሩህ የሆነ ኮከብ ነበር፣በዚያን ጊዜ ከእሱ በታች ያሉትን ፈላስፎችና ዘረደሽት የሚባል ደቀ መዝሙሩን ሰበሰባቸው፣ ከዚያም በተዳመጸ ብራና ላይ የተሣለውን እና እመቤታችን ልጇን ታቅፋ በአጠገቧ ያለውን የኮከብ ሥዕል አሳያቸው። ፈላስፋውም በእሱ ዘንድ ለተሰበሰቡት፣ ይህ ኮከብ በእናንተ (በልጆቻችሁ) ዘመን ምልክትን ቢያሳይና ቢገለጥ፣ የዚያን ጊዜ ድንግል ከነልጇ ወዳለችበት ቦታ መርቶ ያደርሳችሁ ዘንድ እሱን (ኮከቡን) ተከተሉት፣ ለሕጻኑም እጅ መንሻን አቅርቡለት አላቸው፣ ይህንን የትንቢት ምልክት ከነገራቸው በኋላም ፈላስፋው በለዓምና ተከታዮቹ ሁሉ ሞቱ፣ ነገር ግን ከእነሱ በኋላ የተነሱት ሰዎች፣ ያቺን ሥዕል በቤተ መዛግብት (በዕቃቤት) አኖሯትና ለሚኅበኞት ሁሉ አባቶቻቸው የተናገሩትን ትንቢትና በኋላ ዘመን የሚደረገውን ይነግሯቸው ነበር፣ (ከ1534) ዓመት በኋላም ጌታ፣ ከድንግል ማርያም ሲወለድ (2) ዓመት ሲቀረው) «ያ» ኮከብ በሀገራቸው በግልጽ ታየ፣ በዚያን ጊዜ ያንን ሥዕል ከቤተ መዛግብት አውጥተው በሥዕሉ አጠገብ ያለውን የኮከብ ሥዕል ቢመለከቱ በአየር (በሕዋ) ላይ ከተገለጸላቸው ኮከብ ጋር በትክክል አንድ አይነት መልክ መሆኑን አረጋገጡ፣አባታቸው ዘረደሽትም ቀድሞ እንደ ነገራቸው የሀገሩ ፈላስፎችና መኳንንቶች ሁሉ፣ ከሰራዊቶቻቸው ጋር እጅ መንሻቸውንና ሥዕሉን ተሸክመው ለመሄድ ተነሡ። የኮከቡ ርቀትም ከሰው ቁመት (75) ሜትር በሆነ ከፍታ ላይ ሆኖ በፊት በፊታቸው እየሄደ መንገዱን ይመራቸው ነበር፣ በመሸ ጊዜም በመልካም ማደሪያ ቦታ ያደርሳቸውና ከእነሱ ይሠወር ነበር፣ እነሱም በሰላም ያድራሉ በዚህ አይነት ጉዞም፣ እየተጓዙ ጌታ ከተወለደበት ቦታ (በ2) ዓመት ደረሱ፣ ሕፃኑንም ድንግል እናቱ በክንዷ እንዳቀፈችው አይተው ተደስተውና ሰግደው እጅ መንሻቸውን አቅርበውለታል ማቴ.2.1-13።

(16) እግዚአብሔር ማለት፣ ዓለምን ፈጥሮ የሚገዛ የዓለም ጌታ ማለት ነው።



## የሰብአ ሰገል ቁጥር ስንት ነው?

የሰብአ ሰገል ቍጥራቸው (ብዛታቸው) ስንት ነው ቢሉ ሠላሳ ሺህ ሦስት ሲሆን፣ ሦስቱም ማንቱሲማር፤ በዲዳስፋና ሜልኩ የሚባሉ ነገሥታት ናቸው፣ እነዚህ ሦስቱ ነገሥታትም ለእያንዳንዳቸው ዐሥር፣ ዐሥር ሺህ፣ ሰራዊትን ይመሩ ነበር፣ ማቴ. 2.1-13. ንባቡና ትርጓሜው (28 ተአምረ ማርያም)። መጀመሪያ በታተመው የማኅሌተ ጽጌ መጽሐፍ (የ1534) ዓመት የትንቢት ኮከብ ታሪክ የተባለው የዘመን ቍጥር (1536) ዓመት ተብሎ በዚህ መጽሐፍ ተስተካክሏል፣ እመቤታችንም ጌታን በወለደችበት ሰዓት የብርድ ሰዓት ነበርና ነቢዩ ኢሳይያስ፣ ላም (አህያ) የገዥዋን በረት አወቀ፣ ኢሳ.1 3፤ነቢዩ ዕንባቆም በበኩሉ በሁለት እንስሳ መካከል አየሁህ፣ ብለው አስቀድመው ትንቢት እንደተናገሩ ትን.ዕን. 3.2. ይህ የተወለደ ሕፃን ፈጣሪያቸው መሆኑን አውቀው ዘፍ. 1.24. እንስሳ (አህያና ላም) ሰግደው ትንፋሻቸውን ገብረው አሙቀውታል፣ (62 እና 213 ተአምረ ማርያም)። ዕንባቆም ማለት አዋቂና አስተዋይ ማለት ሲሆን፣ አባቱ ዳኮር (ናኮር) እናቱ ሬፋ ይባላሉ፣ ነገዱም ከነገደ ስምዖን ነው፣ (መጽሐፈ አዕናቍ የብርሃና)። በነቢይነት የተጠራውም ዓለም በተፈጠረ በ4892 ዓመት (ከጌታ ልደት በፊት ከ608-507 ዓመት) ነው።

፳፭-65 እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ ጽጌ ፀዓዳ ወቀይሕ፣
አመ ቤተ መቅደስ ቦእኪ በዕለተ ተአምር ወንጽሕ፣
ንዒ ርግብየ ትናዝዝኒ እምላህ
ወንዒ ሠናይትየ ምስለ ገብርኤል ፍሡሕ፣
ወሚካኤል ከማኪ ርኅሩኅ።

*ጌታ፣ ከወፎች ሁሉ በመረጣት ርግብ የተመሰልሽ መልካሚቱ ርግብ ማርያም ሆይ ዕዝ.ሱቱ.3.26. ነጭና ቀይ መልክ ያለው (በአምላክነቱ ነጭ፣ በሰውነቱ ቀይ የተባለ) አባባ ልጅሽን መኃ.5.10. ታቅፈሽ፣ በ40 ቀን ወደ ቤተ መቅደስ እንደገባሽበት ጊዜ ሁሉ፣ ደስ ካለው ከገብርኤልና እንደ አንቺ ርኅሩኅ ከሆነ ከሚካኤል ጋር፣*

(17) ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ድረስ እግዚአብሔር የሚል (7464) ይገኛል።

www.ethiopianorthodox.org

ከኀዘን ታረጋጊኝ ዘንድ ነዪ። (ታሪኩ) እንደ ኦሪቱ ሕግ ጌታን በተወለደ (በ40) ቀኑ ከርግብና ከዋኖስ ጋር ወደ ቤተ መቅደስ የወሰዱበትና ዘሌ.12.6-7. ካህኑ ስምዖን የካቲት (8) ቀን የታቀፈበት ነው፣ ሉቃ.2.22-25። እንደ ርግብ የዋህ ሆና የተፈጠረች ሔዋን፣ የዲያብሎስን ተንኮል ባለማዋቋ ተሳስታለች 3ኛ. መቃ.2.18። ዳግሚት ሔዋን የተባለች ድንግል ማርያም ግን፣ በንጽሕና፣ በቅድስና ተሸልማ መልካሟ ርግብ እየተባለች ትመስገናለች። (ሐተታ) ቅዱስ ገብርኤል ደስተኛ መልአክ ነው መባሉ፣ ጌታ ማርያምን ሂድ አብሥራት ሲለው ደስ እያለው መጥቶ፣ እሷንም ደስተኛይቱ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ እያለ በማብሠሩ ነው ሉቃ.1.26-29። ቅዱስ ሚካኤልም እንደ አንቺ ርኅሩኅና አዛኝ ነው መባሉ እመቤታችን የምሕረት እናት (አዛኝ) እንደሆነች ሁሉ፣ ወሚካኤል አሐዱ እመላእክት እምቅዱሳን ቀደምት እስመ በዲበ ሠናይቱ ለሰብእ ተአዛዚ፣ "ቅዱሳን ከተባሉ መላእክት አንዱ የሆነው ቅዱስ ሚካኤል፣ ከጌታ በተሰጠው ቸርነት ለሰው ሁሉ ታዛዥና ምሕረትን የሚለምን ስለሆነ ነው። ሄኖ.1.6 እና 5-6 እና ሠለስት የተባለ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት።

## በ፲ቱ ወ፬ቱ ትንብልናከ (የቅዱስ ሚካኤል የ14ቱ ምልጃዎች) ታሪክና ምሥጢር

ቅዱስ ያሬድ፣ ድጓ በተባለ ድርሰቱ እና በየዓመቱ ኅዳር (12) ቀን በማኅሌት በሚዘመረው ቃለ እግዚአብሔር ላይ፣ሚካኤል እመላእክት መኑ ከማከ ልዑል፣ አስተምህር ለነ ስአልናከ በ፲ቱ ወ፬ቱ (በዐሠርቱ ወአርባዕቱ) ትንብልናከ፣ማለትም ከመላእክት እንደ አንተ ከፍ ያለ ማን ነው? የተባለልህ ሚካኤል ሆይ (በ14ቱ) ምልጃዎችህ ማልድልን የሚል ኃይለ ቃል ይገኛል።

(18) ከዕዝራ ሱቱኤል እስከ መጽሐፈ ሄኖክ (በ81 መጽሐፍ ቅዱስ ከገጽ 723 እስከ 853) በአሉት ብሉያት መጻሕፍት፣እግዚአብሔር የሚል (2028) ይገኛል።



ቅዱስ ሚካኤል (በ14ቱ) ምልጃዎችህ ማልድልን ለምን ተባለ? ቢሉ የእሑድ መጽሐፈ አክሲማሮስ እንደተናገረው፣

1ኛ. አለቃቸው ሳጥናኤል (ዲያብሎስ) የነበረ፣ ኢዮር በተባለ በ1ኛው ከተማ ያሉ እና አጋዕዝት የሚባሉ መላእክት፣

2ኛ. አለቃቸው ኪሩብ የሚባል፣ መልአክ እና በኢዮር በ2ኛው ከተማ ያሉ ኪሩቤል፣ የተባሉ መላእክት ሕዝ.10፤1-20.

3ኛ. አለቃቸው ሱራፌ የሚባል መልአክ እና በኢዮር በ3ኛው ከተማ ያሉ ሱራፌል፣ የሚባሉ መላእክት፣ ኢሳ.6-2-6.

4ኛ. አለቃቸው ሚካኤል እና በኢዮር በ4ኛው ከተማ ያሉ ኃይላት የሚባሉ መላእክት፣ ሄኖ.10.2-6.

5ኛ. አለቃቸው ገብርኤል እና ራማ በተባለ በ1ኛው ከተማ ያሉ አርባብ የሚባሉ መላእክት፣ ሄኖ.10-78.

6ኛ. አለቃቸው ሩፋኤል የሚባል መልአክ እና ራማ በተባለ በ2ተኛው ከተማ ያሉ መናብርት የሚባሉ መላእክት ፣ሄኖ.10-6-7.

7ኛ. አለቃቸው ሱርያል የሚባል መልአክ እና በ3ኛው የራማ ከተማ ያሉ ሥልጣናት የሚባሉ መላእክት፣

8ኛ. አለቃቸው ሰዳክያል የሚባል መልአክ እና ኤረር በተባለ በ1ኛው ከተማ ያሉ መኳንንት የሚባሉ መላእክት፣ ማቴ.24-30-32.

9ኛ. አለቃቸው ሰላትያል የሚባል መልአክ እና በኤረር በ2ኛው ከተማ ያሉ ሊቃናት፣የሚባሉ መላእክት፣

10ኛ. አለቃቸው አናንያል የሚባል መልአክ እና በኤረር በ3ኛው ከተማ ያሉ መላእክት የተባሉ አገልጋዮች (በጠቅላላ እነዚህ መላእክት) (100) ነገድ ነበሩ፣ (የእሑድ መጽሐፈ አክሲማሮስ

(19) ከማቴዎስ ወንጌል እስከ ራእየ ዮሐንስ (በሐዲስ ኪዳን) እግዚአብሔር የሚል (1191) ይገኛል።

www.ethiopianorthodox.org

ክፍል ሁለት እና መጽ.ኩፋ. 2-6-8)። **ከነዚህ መላእክትም አንዱ እና ዋና** የነበረው ዲያብሎስ፣ በትዕቢቱ ሲወድቅ 3ኛ. *መቃ*.8-11፣ (99) ነገደ መላእክት ተባሉ። ቅዱስ ሚካኤልም ለነዚህ መላእክት ሁሉ አለቃ ሆኖ አብሮ ያመሰግናል። ስለዚህ (በ14ቱ) ምልጃዎችህ ማልድልን ተባለ። አሁንም ቅዱስ ያሬድ ድጓ በተባለ ድርሰቱ እና ጥር 11 ቀን (በጥምቀት በዓል) በሚፈጸመው ምስጋና ላይ፣ ስለ (99ኙ) ነገደ መላእክት ሲናገር፣ ኀዲጎ፡ ፺. (ተስዓ) ወ፱ተ. (ወተስዓተ) ነገደ ቆመ ማእከለ ባሕር፣ ‹‹ጌታ (99ኙ) ነገደ መላእክትን ትቶ በዮሐንስ እጅ ሊጠመቅ በባሕር መካከል ቆመ›› ብሏል ማቴ. 3-13። ይህ ታሪክም (ኃይለ ቃል) የሚያስረዳን እኔ ፈጣሪ ነኝ ብሎ በፈጣሪው ላይ በታበየውና (ከ100) ነገደ መላእክት ተለይቶ በወደቀው በዲያብሎስ ምትክ (ከ99ኙ) ነገደ መላእክት ጋር ፈጣሪውን ሊያመሰግን የተፈጠረ አዳም! በተፈጠረ (በ7) ዓመቱ የፈጣሪን ትእዛዝ አፍርሶ ከገነት በወጣና 3ኛ *መቃ*.2.9-20. (ከ99ኙ) ነገደ መላእክት በተለየ (በ5526) ዓመት (በ33) ዓ.ም ጌታ (የ99ኙ) ነገደ መላእክትን ባሕርይ ትቶ (ሰውን ወዶ እና አክብሮ) ማዳኑን ነው። ይህንንም ታሪክ ጌታ፣ መቶ በጎች ያሉት ሰው ቢኖር፣ ከመቶ በጎች መካከል አንዱ በግ ቢጠፋበት (99ኙን) በበረሃ ትቶ አንዱን በግ ሊፈልግ ይሠማራ የለምን? ባገኘው ጊዜስ ደስ ይለው የለምን? ሲል ከመላእክት የተለየ አዳምን ለማዳን የመጣ መሆኑን በምሳሌ ተናግሯል ማቴ.18.11-15።. ስለዚህ (በ14ቱ) ምልጃዎችህ ማልድልን የሚለው ኃይለ ቃል በምሥጢር ሲዘረዘር:

<u>1ኛው</u> ምክንያት፣ እስራኤል ተማርከው በባቢሎን ሳሉ፣ቅዱስ ሚካኤል መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሀሎሙ "አቤቱ ሕዝብህን ማራቸው፤ ይቅርም በላቸው" እያለ ይጸልይ ነበረ ዘካ.1.12። መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሀሎሙ የሚለውን ፊደልም እያንዳንዱ ቢቈጥሩት (14) ይሆናልና።

(20) በጠቅላላ (በ81) መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር የሚል (10,683) ይገኛል።



<u>2ኛው</u> ምክንያት፣ በወር፣ በወር የሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል በዓል (12) ሆኖ የአእላፍ (ስፍር ቊጥር የሌላቸው) መላእክት በዓል የሚውልባቸው ኅዳር (13) እና ሰኔ (13) ቀን እንደ አንድ ቀን ተቈጥረው፣ የታኅሣሥ (19) ቀን የቅዱስ ገብርኤል በዓልም፣ ከነዚህ ጋር ተቈጥሮ በመከበሩ ነው፣ይህም ቢቈጠር (14) ይሆናልና።

<u>3ኛው</u> ምክንያት፣ 99ን ለ14 ቢያካፍሉት 14.14 ይደርሳል። ስለዚህ ቅዱስ ሚካኤል የ99ኙ ነገደ መላእክት አለቃ ሆኖ ስለ ሰው ምሕረትን ይለምናልና ነው። (የድጓ ባህል የእጅ ጽሑፍ)

፷፮-66 ሶበ ዴገነኪ አርዌ በሊዐ ሕፃንኪ ዘነለየ፣
በዘትሠርሪ ገዳመ ወታፈጥኒ ጕዩየ፣
እመ ጸገይኪ አክናፈ ከመ ዮሐኒ ጸገየ፣
ብእሲተ ሰማይ ማርያም ዘትለብሲ ፀሐየ፣
ተአምረኪ ጸሐፈ ዮሐንስ ዘርእየ።

*ፀሐይን የምትለብሺ (እውነተኛ ፀሐይ የተባለ ጌታን የወለድሽ) የሰማይ እመቤት ማርያም ሆይ ልጅሽን ለመግደል ያሰበ አውሬ ሄሮድስ በተከተለሽና ወደ በረሀ ፈጥነሽ በምትሸሺበት ጊዜ፣ ራእ. 12.1-7. ክንፍን እንዳወጣ እንደ ዮሐኒ ክንፍን ስታወጪ ያየ ዮሐንስ፣ ተአምርሽን ጻፈ።* (ሐተታ) አውሬ (ዘንዶ) የተባለ በጨካኝ ባሕርዩ ንጉሥ ሄሮድስ ነው።ራእ.12.4-5. በተቃራኒው ግን፣ እመቤታችን ከቤተልሔም ወደ ግብጽ ስትሸሺ ባደረችበት ቦታ አውሬ የሚያድን የነበረ አንድ ሰው ውሾቹን ይዞ ወደ እመቤታችን ሲመጣና ውሾቹ እመቤታችንን ሲያዩ የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ ለሆነ እናቱ የሆንሺ እመቤታችን ሆይ ለአንች ምስጋና ይገባሻል እያሉ የበለዓም አህያ በሰው አንደበት እንደተናገረች ሁሉ ዘኍ.22.24-31 በሰው አንደበት አመስግነዋታል፣ (32 ተአምረ ማርያም)።

21) ጻድቅ ማለት፣ ጻድቀ እውነተኛ ሆነ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን፣ ጻድቃን ማለት ደጎች፣ እውነተኞች፣ ቅኖች ማለት ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## አባ ዮሐኒ በክንፍ ስለመብረሩ፤

(ታሪክ) የዓመተ ምሕረት አቈጣጠርን በተመለከተ፣ ከ145-147. ባለውና ተአምረ ኢየሱስ በተባለው መጽሐፍ፣ ታሪኩ እንደ ተገለጸ፣ በየመን አውራጃ በምትገኘው ናግራን (ሳባ) በምትባል ቦታ መሪያቸው የሆነ ቅዱስ ኂሩትን ጨምሮ፣ በከሐዲው ንጉሥ በፊንሐስ (በማገዙሩቅ) ሃያ ሺህ ሰማዕታት በተገደሉበት (በ525) ዓ.ም (አባ ዮሐኒ ከመወለዱ ከአንድ ዓመት በፊት) የአባ ዮሐኒ የእናቱ ባል ናግራን ወደሚባል አገር ዘምቶ (ለ7) ወር ያህል ቢዘገይ፣ ሚስቱን ትንሽ ወንድሙ ወንድሜ ዘገየ (ቆየ) ከእንግዲህ ወዲህ አይመለስም፣ ሞቷልም ይላሉና፣ ሚስት ትሆኚኝ ዘንድ ነዪ ቃል ኪዳን እንግባ አላት፣ እሷም የባሏ ትንሽ ወንድምና በቤቷ ውስጥ ያሳደገችው በመሆኑ እንዴት ደፈርከኝ ብላ ተቈጣች፣ እሱም ወንድ ነውና፣ በጉልበት አሸንፎ ቢደርስባት ጸንሳ (በ526) ዓ.ም ሚያዝያ (5) ቀን ዮሐኒን ወለደች፣ በወለደችበት በዚሁ ቀንም ከብዙ ምርኮ ጋር ባሏ ወደ አገሩ ተመልሶ ወደ ቤቱ ቢገባ ሚስቱ ከቤት የለችም ነበርና፣ ሚስቴ ወዴት ሄደች ብሎ ጠየቀ፣ በዚህ ጊዜ በቤት ውስጥ ያለ አንድ ሕፃን ልጅ ባለቤትህ ታማለች አለው።እርሱም በሽታዋ ምንድነው አለው፣ ሕፃኑም ዛሬ ልጅ ወለደች ሲለው ፈጽሞ ተቈጣና ሕፃኑ እየመራው ሚስቱ ወዳለችበት ገብቶ ይደበድባት ጀመር፣ በዚሁ በትግራይ ክፍል በሚገኝና ተራራው የዓሣ ቅርጽ ስላለው ደብረ ዓሣ ተብሎ በተሰየመው ገዳምም (ለ20) ዓመታት ያህል የቆየ ስሙ አባ አሞኒ የተባለ ገዳማዊ ሰው ነበር፣ የጌታ መልአክም አባ አሞኒን ተነሥና የተንቤን ሹም ወደ ሆነው ሰው

ቤት ሂድ! ከዚያም ጌታ የወደደውን ነገር ታገኛለህ፣ (ታያለህ) አለው፣ አባ አሞኒም የጌታ መልአክ እንዳዘዘው ከገዳሙ ወጥቶ ወደ ተንቤን ሹም ቤት ደረሰ፣ ሚስቱም በቤቱ በር ፊት ለፊት አባ አሞኒን ቆሞ ስታየው፣ ውስጡ ጥበበ እግዚአብሔር ነበርና፣ ከዚህ

(22) የሰው ባሕርይ ከኃጢአት ስለማይነጻ፣ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ጻድቅ ሊባል አይችልም፣ኢሳ.59.7-9፣ ሮሜ. 3.11-21 ነገር ግን ጻድቅ ሊባል ይችላል።



መነኩሴ ጸነስኩ አለችው። ያን ጊዜ ባሏ በቍጣ ወጥቶ አባ አሞኒን መታውና ልጅህን ይዘህ ሂድ ሲለው፣ እሺ ስጠኝ ብሎ ሕፃኑን በልብሱ (በአጽፉ) አቅፎ ወደ ገዳሙ ወስዶ እኔ ጡት የለኝ! አሳጠባህ ብሎ ወደ ጌታ ጸለየና ከገደሉ ጀርባ በመቃብር አምሳያ (መሬቱን መቃብር አስመስሎ) ቆፍሮ የዘንባባና የእንስት ቅጠልን አንጥፎ፣ በዚያም አኑሮ፣ ድንጋይንም ከድኖ ጌታ ከወደደ ያድንህ፣ ይህቺ ጉድጓድም እናትህ ትሁን ብሎ ትቶት ወደ ገዳሙ ሄደ። በነጋውም ማልዶ ወደዚያ ሕፃን ገሠገሠ፣ ፌቆዋ (ሚዳቋዋ) ከጉድጓዱ አፍ ድንጋዩን አስወግዳ ተንበርክካ ስታጠባው፤ ዝንጀሮዎችም ሲያጫውቱት፤ የሰማይ ወፎችም በደስታ ሲያጅቡት፤ ሕፃኑም ደስተኛ ሆኖ አየና ይህን ዕፁብ ድንቅ ሥራ ያሳየኸኝ ጌታ ስምህ ይመስገን ብሎ ወደ ገዳሙ ተመለሰ፣ አባ አሞኒም ሕፃኑን ጠዋትና ማታ እየጎበኘውና ፌቆ፣ እንደ እናት ሆና ጡት እያጠባችው (3) ዓመት ከኖረ በኋላ የፌቆዋን ጡት መጥባት ተወ፣ አባ አሞኒም ወደ ገዳሙ ወስዶ (ከ7) ዓመቱ ጀምሮ የዳዊትን መዝሙር፣ የነቢያትንና የሐዋርያትን መጻሕፍት አስተምሮ (12) ዓመት ሲሆነው፣ ዲያቆን ይሆን ዘንድ በአክሱም ከተማ ወደ አለው ጳጳስ ሲወስደውና ልዩ ስሙ <<ሲህታ>> ከሚባለው ቦታ ሲደርሱ፣ ዮሐኒ ውሃን በእንስራ ተሸክመው የራሳቸው ጸጉር ረጅም፣ ጡቶቻቸው ታላላቅ ሆነውና ከልብስ ተራቁተው (10) ሴቶችን በመንገድ አየ። ዮሐኒም ከዚህ በፊት የሴት መልክን አይቶ አያውቅም ነበረና፣ አባ አሞኒን ከደረታቸው ቀንድ ቀንድ ያላቸው ጡታቸውን ማለቱ ነው! ጡታቸውን አይቶ እነዚህ ምንድን ናቸው? አለው፣ አባ አሞኒም እነዚህ ሰውን የሚያስቱ ናቸው አለውና፣ ዮሐኒ ሴትንና ወንድን ይለይ ዘንድ ልጁ አምን እንደነዚህ ያለ ጡታቸው በደረታቸው የወደቀና ጺም የሌላቸውን ሰዎች ባየህ ጊዜ፣ ተወርውረህ ወደ ገደል ግባ ብሎ ወደ ገዳሙ መለሰው፣በዚሁ አካባቢም አባ አበይዶ የሚባል

(23) ሰዎች፣ በእግዚአብሔር ሕግ ፀንተው ሲኖሩ፣ ጻድቅ (ጻድቃን) ይባላሉ ለምሳሌ ኖህ ጻድቅ፣ ካህኑ ዘካርያስ እና ሚስቱ ኤልሳቤጥ ጻድቃን ተብለዋል ዘፍ.6.9፣ሉቃ.1.1-20።

www.ethiopianorthodox.org

መነኰሴ ነበርና፣ የአባ አሞኒን እና የዮሐኒን የተጋድሎ ዜና ሰምቶ
ረድእ (አገልጋይ) ለመሆን አብሯቸው ተጨመረ፣ ዮሐኒም (በ14
ዓመቱ መነኰሰ፣ አባ አሞኒና አባ ዮሐኒም ከተራራ ላይ እየወጡ
መጽሐፍ እየጻፉ፣አባ አበይዶ መጽሐፍ እየሸጠ ራሳቸውን እየረዱ
በብሕትውና ሲኖሩ፣ አባ አሞኒ በገዳሙ (40) ዓመት ኖሮ ዐረፈና
በገዳሙ ቀበሩት፣ ይህን ጊዜ አባ ዮሐኒ (20) ዓመቱ ነበር፣ ከዚህ
በኋላ አባ ዮሐኒ (12) ዓመት ኖሮ ኅዳር (5) ቀን ከቀኑ (3) ሰዓት
እንደ ልማዱ ከተራራ ላይ ወጥቶ ሲጽፍ እናትና ልጅ በተለያዩ
(በ32) ዓመት ወላጅ እናቱ መጥታ እንደምን አደራችሁ አለች፣ አባ
ዮሐኒም በወንዶች ገዳም ስላደገ የሴት ድምጽን መለየት አይችልም
ነበርና፣ አንተ ማነህ፣ አለ እናቱም በክርስትና ስሟ እኔ አመተ
መንፈስ ቅዱስ ነኝ አለች። በዚህ ጊዜ አባቱ (አሳዳጊው) አባ አሞኒ
ሴት ስታይ ወደ ገደል ተወርወር ብሎ አስቀድሞ የነገረው
አስታውሶ፣ አንገቱን አቅንቶ ከሩቅ አያትና መጽሐፉንና የቀለም
መጻፊያ ብዕሩን ጥሎ ወደ ገደሉ ተወረወረ። በመንገድህ ሁሉ
ይጠብቁህ ዘንድ፣ እግርህም እንዳትሰናከል መላእክቱን ስለ አንተ
ያዝዛቸዋል እንደተባለም መዝ.90.11-13. ጓደኛው አባ አበይዶ
እያየው በክንዶቹ ግራና ቀኝ ክንፍ አውጥቶ፣ የእግዚአሔር መልአክ
ከእርሱ ጋር ሆኖ በተወለደ (በ32) ዓመቱ በመቃብር ውስጥ
መፍረስና መበስበስ ሳይኖርበት ሄኖክና ኤልያስ፤ ዕዝራ ሱቱኤልና
ደጋግ ሰዎች ወዳሉበትና ብሔረ ሕያዋን ወደ ተባለው የቅዱሳን ቦታ
ዕዝ.ሱቱ.13.49. በሕይወት ገባ፣ ድርሳነ ኤልያስ የተባለ መጽሐፍም
አባ ዮሐኒ፣ ወደ ገደል መወርወሩ እንደ ሞትና እንደ መቃብር፤
ክንፍ አውጥቶ ብሔረ ሕያዋን መግባቱ እንደ ትንሣኤ ሙታን
ተቈጥሮለት፣ ሁለተኛ ሞት የለበትም ይላል፣ (ድርሳነ ኤልያስ
ግእዝ እትም 1964 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ። አንዳንድ ሊቃውንት
ደግሞ አባ ዮሐኒ፣ ወደ ገደል ተወርውሮ ዐርፎ ሰማዕትነትን ተቀበለ
ይላሉ። በጻድቁ በአባ ዮሐኒ ስም የተሠራው ገዳምም ትግራይ

(24) ሰዎች፣ የተጣላን ሲያስታርቁ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው መንግሥተ ሰማያትን ይውርሳሉ፣ ማቴ .5.3-11።



ንቤን ውስጥ ሲሆን፣ ዕረፍቱ ኅዳር (4) ቀን ነው (የቅዱሳን ታሪክ
ሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ 1998 ዓ.ም)።

## ስለ እመቤታችን የክንፍ ምሥጢር፣

ታሪክ) ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ምሥጢር ያልተከፈለበትና
ስቀድሞ ቃል ነበረ ብሎ የመለኮትን ምሥጢር የተናገረ ዘፍ 1.1፣
ሐ.1.1. የጌታ ባለሟል ነው፣ ከዕለታት አንድ ቀን ፀሐይን የለበሰች
ፃን ሴትን አይቶ ሲተረጕም እንዲህ አለ፤ ሕፃኗ እመቤታችን
ት፣ ፀሐዩም ልጅዋ ክርስቶስ ነው፣ በፍጥረት ሁሉ ስሟ
ሚጠራበትና የልጅዋ ምስጋና ከሚነገርበት ቦታ ሁሉ፣ በረድኤት
ጥና የምትደርስባቸው ረቂቃን ክንፎች አሏት አለ፣ በለበሰችው
ፀሐይ ብርሃን ሙቀትም በኃጢአት ብርድ ውስጥ ያሉ ሁሉ
ሙቀትን (ንስሓን) አገኙ ብሎ ያየውን ራእይ ጻፈ። ስለዚህ
መቤታችንን ክንፍን ያወጣሽና ፀሐይን የለበስሽ የሰማይ እመቤት
ማርያም አላት፣ (ራእ.12.1-7. እና 87-89 ተአምረ ማርያም)።
፷፮-67 ተአምረ ግፍዕኪ ለአርእዮ እምገጸ ሄሮድስ መስቴማ፣
አመ ጕየይኪ ማርያም በሐዊረ ፍኖት እለ ደክማ፣
ምስለ እግረ ጽጌኪ ልምሉም ኀበ አእጋርኪ ቆማ፣
ለምድረ ገዳምኪ ቅድስት ቍስቋም ስማ፣
እምፈተውኩ በጺሕየ በሰጊድ እስዐማ።
*ማርያም ሆይ ከጠላት ሄሮድስ ፊት በሸሸሽ ጊዜ፣ ማቴ. 2.13-18.*
*በኖር ኖሮ ከለመለመ ከልጅሽ እግር ጋር መንገድን በመሄድ የደከሙ*
*እግሮችሽ የቆሙባትንና ልዩ ስሟ፣ ቍስቋም የተባለችው ገዳምሽን*
*(ቦታሽን) ደርሼ፣ በመሳለም የግፍሽን ተአምር ለመግለጽ በወደድኩ*
*በር ። ቍስቋም፣ እመቤታችን በስደቷ ጊዜ ከኅዳር (6) ቀን ጀምሮ*
*3) ወር ከ10 ቀን ከድካሟ ያረፈችባት ቦታ ስትሆን፣ እመቤታችን፣*
*ሀገሪቱ ስም ቍስቋም ማርያም ተብላለች።(48 ተአምረ ማርያም)*

25) በነቢይ፣በጻድቅ፣ ስም ቀዝቃዛ ውሃን የሰጠ፣ ዋጋው እንደማይጠፋበት ጌታ ተናግሯል ማቴ.10.40-42።

www.ethiopianorthodox.org

፷፰-68 አፊወ አሮን (አፊወ ሮማን) ማርያም ጽጌ ቀናንሞ ወአበሜ፣
እስከ ተጸምሐየየ በጾም ዘመልክእኪ ልምላሜ፣
ተአምረ ብካይ ወስደት ዘበጽሑኪ (ዘበጽሐኪ) ጊዜ ድክታሜ፣
እምተመነይኩ ተሳትፎ ከመ እኅትኪ ሰሎሜ፣
ወፍሥሐኪ ዘአልቦ ፍጻሜ። ወፍሥሐየ ዘአልቦ ፍጻሜ የሚሉ ሊቃውንትም አሉ)።*ቀናንሞና አበሜ ከሚባሉ ሽቱዎች ይልቅ የተዋብሽ፣ የአሮን የክህነቱ ክብር (መዓዛ ክህነቱ) ዘጸ.28. 31-44 የሆንሽና ሮማን ከሚባል የተክል መዓዛም ፣መዓዛ ረድኤት ያለሽ ማርያም ሆይ. የመልክሽ ልምላሜ (ደም ግባትሽ) በጾም እስከ ጠወለገ ድረስ በጭንቀትሽ ጊዜ ብኖር ኖሮ የደረሱብሽ መከራዎችን፤ (ያገኘሺን የስደትና የልቅሶ ጊዜን) እንደ እኅትሽ እንደ ሰሎሜ ብሳተፍ ደስታሽ (ደስታዬ) ወሰን የለውም ነበር።*

## ስለ ሰሎሜ እጅ መፈወስ፣

(ታሪክ) ሰሎሜ፣ የምትባል አንዲት ሴት፣ ድንግል ማርያም በድንግልና ወለደች ሲባል ሰምታ ሄጄ ካላየሁ አላምንም ብላ በመጠራጠር የእመቤታችንን ማሕፀን ስትዳስስ፣ እጇ እሳት እንደገባ ጅማት (እንደ ፈትል) እርር ኩምትር አለ፣ በዚህ ጊዜ ሰሎሜ ስትጸልይ የጌታ መልአክ ሕፃኑን አንሥተሽ ታቀፊው አላት፣ እሷም በሰለለው እጇ አንሥታ ብትታቀፈው ወዲያው ተፈወሰች። እሷም ይህ ሕፃን የእስራኤል እውነተኛ አምላክ ነው ብላ አመነች። በጥርጥር የሰለለ እጅም መለኮታዊ እሳትን ዳሶ መዳኑ ልዩ ቸርነትና ተአምር ነው፣(29 ተአምረ ማርያም)። ሰሎሜ፣ ከእመቤታችን ጋር አብራ ከመሰደዷ ባሻገር፣ ጌታ እስከ ተሰቀለበትና እስከ ተነሣበት ጊዜ ድረስ ስታገለግል ኖራ ማር.15. 40-42፣16.1-2 ግንቦት (25) ቀን ዐረፈች። (የግንቦት 25 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)

(26) ኃጢአትን በንስሐ ማስወገድ እንጂ፣ለኃጢአት ምክንያት ማቅረብ ከፍርድ እንደማያድን ይመልከቱ ⟶



፷፱-69 የበስኩ እንክ (አንሰ) ተክለ ቤትኪ በነፋሰ ሐሩር ዘኃጣውእ፣
ከመ ጽጌ መንግሥት የበስኪ በዋዕየ ረኃብ ወጽምዕ፣
ማርያም ንዝኀኒ በዘዚአኪ አንብዕ፣
ወአጽግዪኒ ጽድቀ በተአምርኪ ቀውዕ፣
እንተ ፀቱ ይጸጊ ወይፈሪ ቆዕ።
የመንግሥት አበባ የሆንሺ ማርያም ሆይ በረሀብና በጽምዕ ሐሩር እንደጠወለግሽ፣ የቤትሽ ተክል የሆንኩ እኔ በኃጢአት ሐሩር ነፋስ ደርቄአለሁና፣ እንግዲህ ምሕረት ያለበት እንባሽን ረጭተሽ የንስሓ ፍሬን ገና ያላፈራ ቡቃያ ሥራዬ፣ አብዐ በሚያፈራበት በተአምርሽ አዝመራ እንዳብብና የጽድቅ ፍሬን እንዳፈራ አድርጊኝ።
(ሐታታ) ነፋስ የመታው እህል፣ፍሬ እንደሌለው ሁሉ ኃጢአትም ሰውን ከፍሬ ጸጋ ይለያልና በኃጢአት የሐሩር ነፋስ ደረቅሁ አለ።

፸-70 ነጋድያነ ቊስቋም ለእንስሳ እለ ተጽዕንምሙ በፍኖት፣
ዘኢያስተትኪ እግሮሙ ትቅብዒዮሙ (ከመ ትቅብዒ)
ቅብዐ በረከት፣
ቅብዐ ጽጌኪ ቅብዕኒ ተአምረ ምሕረት መርዐት፣
አኮ ለሰብእ ባሕቲቱ ማርያም ሠናይት፣
እስመ ርኅርኀተ ልብ አንቲ ለኩሉ ፍጥረት።
*የቊስቋም ነጋዴዎች በመንገድ የተጫኑባቸው እንስሶችን (ፈረስና በቅሎን)፣ የበረከት ቅባትን እግራቸውን ትቀቢ ዘንድ ያልናቅሽና አዲስ የምሕረት ምልክት የሆንሽ ማርያም ሆይ የልጅሽን መዓዛ በረከት ቀቢኝ፣ ደግነትሽ ለሰው ብቻ አይደለም፣ አንቺ ለፍጥረቱ ሁሉ የልብ አዛኝ ነሽና።*

## የእመቤታችን ርኅራኄ በእንስሳት ላይ፣

(ታሪክ) በየዓመቱ ደብረ ቊስቋምን ለማክበር ምእመናን በፈረስና በበቅሎ ተጭነው ሲሄዱ፣(እንስሶች) ደክመው በአለንጋ እንዳይገረፉ

(27) አዳም በሔዋን፣ ዕፀ በለስን አበላችኝ ፣ ሔዋን እባብ አሳተችኝ ብለው ለጌታ ያቀረቡት ምክንያት ከፍርድ አላዳናቸውምና ዘፍ.2.10-20።

www.ethiopianorthodox.org

እመቤታችን የበረከት ሽቱን ስትቀባቸው እጅግ ይበረቱ ነበር፣ ስለዚህ መራራትሽ ለሰው ብቻ አይደለም ለፍጥረቱ ሁሉ ነው እንጅ አለ፣ (ግብረ ሕማማት ገጽ 171 ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1996 ዓ.ም):: (እንስሳት ሁሉ) አሁን የሚጠሩበት ስም የወጣላቸው ሚያዝያ (6) ቀን እሑድ ነው ዘፍ.2.19-21):: እንስሳ የጌታውን ቤት አወቀ፣ እስራኤል (ሰው) ግን ክቡር (ባለ አእምሮ) ሆኖ ሳለ አላወቀም ኢሳ.1.3-4፣ መዝ.48.12::

፩1-71 አመ አተውኪ ውስተ ታቦት ምስለ ቈጽለ ዘይት ሐመልሚል፣
ከመ አብሠርኪዮ ለኖኅ ትእምርተ ጊዜሁ ለሣህል፣
አብሥርኒ ጽድቀ በጸዊረ ጽጌ ጽዱል፣
ማርያም ርግበ ቊስቋም ዘአክናፍኪ መስቀል፣
ሃሌ ሉያ ፋሲካየ ማዕዶት እምኀጒል::

*ክንፎችሽ መስቀል (4) የሆኑ የቊስቋም ርግብ ማርያም ሆይ ከለመለመ የወይራ ቅጠል ጋር ወደ መርከብ በገባሽ ጊዜና ለኖህ የይቅርታ ጊዜው የሆነ ምልክትን እንደ ነገርሽው ዘፍ. 8.8-12. ንጹሕ አበባን (የሚያበራ መስቀልን) ይዘሽ ጽድቅን አብሥሪኝ፣ ከጥፋትም የምድንብሽ የደስታዬ መሸጋገሪያ፣ ነሽና ምስጋና ይገባሻል::* (ታሪኩ) ኖህ በመርከብ ውስጥ እያለ ርግብን ልኮ፣ የወይራ ቅጠልን ይዛ ወደ ኖህ ስትመለስ፣ የጥፋት ውሃ መጉደሉን ኖህ እንደተረዳ ሁሉ፣ ጌታ ከእመቤታችን በነሣው ሥጋ ተሰቅሎ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ማንጻቱን የሚገልጽ ነው፣ *የቊስቋም ርግብ ማርያም* ሆይ ክንፎችሽ መስቀል ናቸው ማለቱም የርግብ ክንፍ (4) አቅጣጫ ሲሆን፣ የእመቤታችንም ንጽሕና ቅድስና (በ4ቱ) መዓዝን (በመላው ዓለም) መነገሩን የሚያስረዳ ነው:: የርግብ ክንፍ አራትነትስ እንዴት ነው ቢሉ፣ ርግብ ስትበር ከክንፏ እስከ ክንፏ፣

(28) የሞተ ሰውን፣ንስሓ እንደኢምንት (እንደዋዛ) አለፈው ሲራ.17.28-29::



(የራሷ ቀኝ ያለው ክንፏና ከእግር እስከ አፏ ያለው አካል) አራት መዓዝን ሆኖ የመስቀል ምልክትን ይሠራልና ነው::

## የሃሌ ሉያ ትርጉም እና የሃሌታ፡ ምንነት?

ሃሌ ሉያ የሚለው ቃል፣ ሀለወ ኖረ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን፣ ሃሌ. ማለትም ዓለም ሳይፈጠር የነበረ አምላክ ማለት ነው፣ ሉያ ማለት ደግሞ እስከ ዘለዓለም የሚኖር አምላክ ማለት ሲሆን፣ ሃሌ፡ ሉያ ተብሎ በአንድ ሲነገርም ምስጋና፣ ማኅሌት ማለት ነው፣ እግዚአብሔርን አመስግኑ ተብሎም ይተረጐማል መዝ.105.1:: በዚህ መሠረትም ሃሌ፡ ሉያ ሲል ከዓለም አስቀድሞ ለነበረ፣ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ላለ፣ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር አምላክ ምስጋና ይገባል ማለት ነው:: በማንኛውም ምስጋና ጊዜ፣ ሃሌ፡ ሉያ ብለን የም[illegible]ር፣ ከአንድ ሃሌ፡ ሉያ (ከአንድ ሃሌታ) እስከ 10 ሃሌ፡ ሉያ (እስከ 10 ሃሌታ) ብቻ ነው:: የምክንያቱን ምሳሌ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሥጢሩን ደግሞ አሁን ይመልከቱ፡-

### የሃሌ፡ ሉያ (የሃሌታ) ዝርዝር ምሥጢር፣

- ሃሌታ፣ በአንድ መሆኑ፣የሰማይና የምድር ፈጣሪ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ለመሆኑ ምሳሌ ሲሆን፣ ዘፍ.1.1.ዮሐ.1.2-4. ይህም በአንድ አምላክ እናምናለን ለማለት ነው፣
- ሃሌታ፣ በሁለት መሆኑ፣
  1ኛ. የአዳምና የሔዋን፣
  2ኛ. የመለኮትና የትስብእት (አምላክ ሰው፣ ሰው አምላክ የመሆኑ)፣
  3ኛ. በዕለተ ዓርብ ከጌታ ቀኝ ጎን ለፈሰሰው ደምና ውሃ፣ ዮሐ.19.28-35 እንዲሁም የቅዱስ ሥጋው እና የክቡር ደሙ፣
  4ኛ. የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ነው፣

(29) ለሰው ልጅ ንስሓ ያስፈለገው፣ ሰው በሕይወት እንዲኖር እንጂ፣እንዲሞት ያልፈጠረውን ጌታ ስለበደለ ነው ጥበ.1.13-14::

www.ethiopianorthodox.org

❖ <u>ሃሌታ፣ በሦስት መሆኑ፣</u>

1ኛ. የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ፣

2ኛ. የሦስቱ ዜማ (የግእዝ፣ የዕዝል፣ የዓራራይ ዜማ) ምሳሌ ነው፣

❖ <u>ሃሌታ፣ በአራት መሆኑ፣</u>

1ኛ. የአራቱ እንስሳ (የኪሩቤል)፣

2ኛ. ሰው የተፈጠረባቸው የአራቱ ባሕርያተ ሥጋ፣ማለትም የነፋስ፣ የእሳት፣ የመሬትና የውሃ፣

3ኛ. የማቴዎስ፣የማርቆስ፣የሉቃስ፣ የዮሐንስ፣

4ኛ. ወንጌል በአራት ክፍል ሆና ለመጻፏ ምሳሌ ነው፣

❖ <u>ሃሌታ፣ በአምስት መሆኑ፣</u>

1ኛ. የ5,500 ዘመን፣

2ኛ. የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር፣

3ኛ. ጌታ እጁንና እግሩን የተቸነከረባቸው የአምስቱ ቅንዋት ምሳሌ ነው፣

❖ <u>ሃሌታ፣ በስድስት መሆኑ፣</u>

1ኛ. ጌታ በ6ኛው ሺህ ዘመን የመወለዱና የ6ቱ ቃላተ ወንጌል ምሳሌ ነው ማቴ.25.3-45፣

❖ <u>ሃሌታ፣ በሰባት መሆኑ፣</u>

1ኛ. የ7ቱ ሰማያት ማለትም፣

የኢዮር፣ የራማ፣ የኤረር፣ 2ኛ.ቆሮ.12.1-3፣ **የሰማይ ውዱድ፣** የሰማያዊት ኢየሩሳሌም፣ ገላ.4.26፣ ዕብ.12.22፣ ራእ.21.2-4፣ የመንበረ-መንግሥት፣ ኢሳ.6.1፣ ሕዝ.1.26፣ ራእ.4.2፣ **የጽርሐ** አርያም ምሳሌ ነው ዘዳ.10.14፣1ኛ.ነገ.8.27፣

(30) ጻድቃንን ከበጎ ሥራቸው የተነሳ ትምራቸዋለህና፣ ጌታ ሆይ እኛን ኃጥአንን ይቅር በለን አለ፣ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በቅዳሴው።



2ኛ. ሰው ማለት ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ፣ ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ የተፈጠረና፣ (7) ነገር ያለው ማለት ነውና፣ የዚህ ምሳሌ ነው፣

3ኛ. ጌታ፣ሙሴን ባዘዘው መሠረት አሮን እንደ ሊቀጳጳስ፣የአሮን ልጆች አልዓዛር እና ኢታምር እንደ ጳጳስ፣ ናዳብና አብዩድ እንደ ቄስ ገበዝ፣ ዘጸ.28.1-6፣ ዘኍ.3.1-5፣ 1ኛ ዜና 24.1-4፣ የሌዊ ታላቅ ልጅ የሆነ የጌድሶን ልጆች እንደ አናጉንስጢስ፣ የሌዊ ታናሽ ልጅ የሆነ የሜራሪ ልጆች እንደ አጻዌ ኆኅት (የቤተክርስቲያን በር እንደሚከፍት አገልጋይ) ሆነው፣ በደብተራ ኦሪት ሲያገለግሉ ለተሾሙ የእነዚህ (የ7ቱ) ልዑካን ምሳሌ ነው፣ዘፍ. 46.11. ዘኍ.3.21-37፤7.7-8። ቅዱስ ያሬድም ድጓ በተባለ ድርሰቱ እምደቂቀ ሌዊ አርአየ ፯ተ (ሰብዓተ) ሥርዓታተ፣ "ጌታ ከሌዊ ልጆች (ከሌዊ ነገድ) 7 ሹሞችን ሾመ" ያለው ይህንን ሲሆን ዘጸ.28.1-6 እንዲሁም (የ7ቱ) ዕለታት፣ (የ7ቱ) ሊቃነ መላእክትና (የ7ቱ) ኪዳናት ምሳሌ ነው።

<u>(የ7ቱ) ኪዳናት ዝርዝርና ምሥጢር፣</u>

*(7ቱ) ኪዳናት የሚባሉ ማን ማን ናቸው ቢሉ?*

1ኛ. ምእመናን ሥጋውንና ደሙን ከመቀበላቸው በፊት በቅዳሴ ጸሎት ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ የእግዚአብሔር ወልድ ሥጋ፣ ወይኑ ተለውጦ የእግዚአብሔር ወልድ ደም እንደሚሆን፣ ለምእመናን ተተርጉሞ ሲነገራቸው ስለሚገባ የሚናገርና ትምህርተ ኅቡዓት የሚባለው ጸሎት ነው፣

2ኛ. ጌታ ሞቶ ከተነሣ በኋላ ያስተማራቸውና እንደ አንድ ሆነው የተቈጠሩት ዘጠኙ ኪዳናት ናቸው።

(31) መናፍቃን፣ ቤተ መቅደስ መግባት የተፈቀደ ለወንዶች እንጂ፣ለሴቶች አይደለምና፣ ማርያም (12) ዓመት በቤተ መቅደስ ኖረች ማለት አይቻልም ሲሉ ይጠራጠራሉ ይበሉ እንጂ? ⟶

www.ethiopianorthodox.org

3ኛ. አዲስ አማኝ (ያልተጠመቀ) ሰው ከመጠመቁ በፊት ለሦስት ዓመት ያህል የሃይማኖት ትምህርትን ሲማር ቆይቶ በመጨረሻ፣ ይህ ጸሎት ሊጸለይለት የሚገባ መሆኑን የሚናገረውና እግዚአብሔር ዘብርሃናት (እግዚአብሔር የብርሃናት ፈጣሪ ነው) የሚለው ጸሎት ነው::

4ኛ. ስለ ሀገርና አጠቃላይ ስለ ፍጥረታት መጸለይ እንደሚገባ የሚናገረውና በእንተ ቅድሳት የሚባለው ጸሎት ነው::

5ኛ. ልቡናችሁ ሰማያዊ ነገርን በማሰብ ፀንቶ ይኑር የሚል ትርጉም ያለውና ዲያቆኑ በጌታ ቅዳሴ ጊዜ የሚያውጀው በሰማይ የሀሉ ልብክሙ የሚለው ጸሎት ነው::

6ኛ. ቅዳሴ እግዚእ (ጌታ ራሱ የተናገረው የራሱ ቅዳሴ)፣ነው::

7ኛ. ሥጋውን እና ደሙን የሚቀበል ሁሉ፣ ሥጋውንና ደሙን እንደተቀበለ ወዲያው በኀሊና ሊጸልየው እንደሚገባ የሚናገረውና ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ፣ስሉስ ዘኢይትነገር (ይህ የሥጋውና የደሙ ምሥጢር ልዩና የማይመረመር ነው) የሚለው ጸሎት ነው::

<u>ሃሌታ፣ በስምንት መሆኑ፣</u>

1ኛ. ሰው ፈጣሪውን በድሎ ጌታ ዓለምን በጥፋት ውሃ ሲመታትና ሲያጠፋት መጽሐፈ ምሥጢር በምዕ.17 ቍ.34 ላይ እንደተናገረው ስምንት ነፍሳት ማለትም ኖህ፣ ሚስቱ አሙዛራ (አምዛራ)፣ ሴም፣ ሚስቱ ሴዴቄቴልባብ፣ ካም፣ ሚስቱ ነኤለማዱክ፣ ያፌት፣ ሚስቱ አዴተነሶስ የሚባሉ (8) ሰዎች ድነው ነበርና የዚያ ምሳሌ ነው ዘፍ.7.13-22:: 1ኛ.ጴጥ.3.20-21

2ኛ. ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ መጽሐፈ ሩት ያሉ (የ8ቱ) ብሔረ ኦሪት መጻሕፍት ምሳሌ ነው ::

(32) ጌታ፣ በሐዲስ ኪዳን ሲያስተምር፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የነበረውን በምሳሌ እንዳስተማረ ሁሉ፣ ማቴ.13. 3-44. እመቤታችን፣ (12) ዓመት በቤተ መቅደስ እንደምትኖር አስቀድሞ የገለጸውን ምሥጢር ይመልከቱ →



3ኛ. ጌታ የሚመጣበትን ቀን ራሱ ብቻ የሚያውቅ ቢሆንም ማቴ.24.29-40፣ ይህን ዓለም (በ8) ሺህ ዘመን ወስኖታልና፣ የዚያ ምሳሌ ነው ዕዝ.ሱቱ.5.37::

❖ <u>ሃሌታ፣ በዘጠኝ መሆኑ፣ የዘጠኙ የቤተ ክርስቲያን መዓርጋት ማለትም</u>

1ኛ. መላእክት የተባሉ አገልጋዮች፣ 1ኛ.ጴጥ.3.22 ምሳሌያቸው ለሆኑ የመዘምራን ምሳሌ፣

2ኛ. መኳንንት የተባሉ መላእክት፣ ምሳሌያቸው ለሆኑ የአናጉንስጢሶች (የቅዱሳት መጻሕፍት አንባቢዎች) ምሳሌ፣

3ኛ. ሊቃናት የተባሉ መላእክት፣ ምሳሌያቿው ለሆኑ የንፍቀ ዲያቆናት ምሳሌ፣

4ኛ. ሥልጣናት የተባሉ መላእክት፣ 1ኛ.ጴጥ.3.22 ምሳሌያቸው ለሆኑ የዲያቆናት ምሳሌ፣

5ኛ. መናብርት የተባሉ መላእክት፣ ምሳሌያቸው ለሆኑ የቀሳውስት ምሳሌ፣

6ኛ. አርባብ የተባሉ መላእክት፣ ምሳሌያቸው ለሆኑ የቆሞሳት ምሳሌ፣

7ኛ. ኃይላት የተባሉ መላእክት፣1ኛ.ጴጥ.3.22. ምሳሌያቸው ለሆኑ የኤጲስ ቆጶሳት ምሳሌ፣

8ኛ. ሱራፌል የተባሉ መላእክት፣ ምሳሌያቸው ለሆኑ የጳጳሳት ምሳሌ፣

9ኛ. ኪሩቤል የተባሉ መላእክት፣ ምሳሌያቸው ለሆኑ የሊቃነ ጳጳሳት እና የሚያዝያ መጽሐፈ ስንክሳር እንደተናገረው፣(በ9) ሰዓት ከገነት ወጥቶ፣ በዚህ ዓለም 930 ዓመት ኖሮ (በ9) ሰዓት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ወደ ሲኦል የወረደ አዳምን ወደ

(33) ቤተ መቅደስ ከገቡ ብትሮች ሁሉ፣ ያለ ውሃ በተአምር ለምልማና አፍርታ የተገኘች አንዲት የአሮን ብትር ናት ዘኍ.17.1-9. እሷም →

www.ethiopianorthodox.org

ገነት ለመመለስ፣ ጌታ በዕለተ ዓርብ (በ9) ሰዓት ነፍሱን ከሥጋው የመለየቱ፣ ማቴ.27.46-51፣ እንዲሁም ቅዱስ ያሬድ፣ (9) ሰዓት የሰው ሥራ ሁሉ ወደ ክርስቶስ የሚደርስበት ሰዓት መሆኑን፣ጸመ ድጓ በተባለ ድርሰቱ፣ጊዜ ፱ቱ (ተስዓቱ) ሰዓት የዐርጉ መላእክት ምግባሮ ለሰብእ ኀበ ክርስቶስ ‹‹በዘጠነኛው ሰዓት መላእክት የሰው ሥራውን ወደ ክርስቶስ ያሳርጋሉ (ያደርሳሉ) የሚለው (የ9) ሰዓትን ምሥጢር የገለጸበት ምሳሌ ነው::

❖ ሃሌታ፣ በዐሥር መሆኑ፣

1ኛ. የዐሥሩ ቃላተ ኦሪት ምሳሌ፣ ዘጸ.20.3-18፣

2ኛ. ዐሥር አውታር ባለው መሰንቆ እና በገና እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው ተብሎ ተጽፏልና፣ የዚህ ምስጋና ምሳሌ ነው:: መዝ.32.2-4፤91.1-4.:: ሃሌታ ማለትም መንፈሳዊ እልልታ፣ (ምስጋና) ማለት ነው:: ቀጥሎ ግእዝ ኪዳን የሚደረስባቸው ቀኖችን እንጽፋለን::

## ግእዝ ኪዳን የሚደረስባቸው ቀኖችና ምሥጢራቸው፣

ግእዝ ኪዳን የሚደረስባቸው ቀኖች ስንት (ማን ማን) ናቸው ቢሉ (9) ናቸው እነሱም:-

1ኛ. የአማኑኤል (ታኅሣሥ 28 ቀን)፣

2ኛ. ዘወረደ የሚባለው የዓቢይ ጾም መግቢያ እሑድ መነሻ ሆኖ ሲቈጠር የ6ኛው ሳምንት (ገብር ኄር የሚባለው) ሰኞ፣

3ኛ. የገብር ኄር ማክሰኞ፣

4ኛ. የገብር ኄር ረቡዕ፣

5ኛ. የገብር ኄር ሐሙስ፣

(34) 1ኛ. የአሮን ብትር ወደ ምስክሩ ድንኳን ከገቡት (12) ብትሮች መካከል ወደ ምስክሩ ድንኳን በገባች (በ12ኛው) ሰዓት የበሰለ የለውዝ ፍሬን እንዳስገኘች ዘኍ.17.1-9 ምሳሌዋ የሆነች ድንግል ማርያም በቤተመቅደስ (12) ዓመት ኖራ የሕይወት ፍሬ የሆነ ጌታን አስገኘች::



6ኛ. የገብር ኄር ዓርብ፣

7ኛ. የሆሣዕና ዋዜማ ቅዳሜ፣

8ኛ. የዕርገት፣

9ኛ. የደብረ ታቦር (ነሐሴ 13) ቀን ናቸው::

በእነዚህ ቀኖች ግእዝ ኪዳን የሚደረስበት ምክንያትም ጌታ በሰማይ ባሉ በ9 ከተሞች፣ (የ99ኙ) ነገደ መላእክትን ቃል ኪዳን በማፅናቱ እና በነዚህ ቀኖች እንደ ሌሎች በዓላት የዕዝሉ ሥርዓተ ዜማ፣ ዕዝል ዜማ መሆን ሲገባው ግእዝ ዜማ በመሆኑ ነው::

፸፪-72 እስመ ብዙኃን ድንግል ተአምረ ወልድኪ ዘነሠሡ፣
ኢፈጸሙ ኵሎ እንዘ ይዌድሱ፣
ትቤ በሜሮን ዘተኀትመት ቤተ መቅደሱ፣
ኀበ ተተክሉ ወጸገዩ አብትረ ዮሴፍ ዘየብሱ፣
(ኀበ ተከለ ወአጽገየ አብትረ ዮሴፍ ዘየብሱ)፣
ወልድ እኁየ ወሪዶ በጊዜ ናእሱ፣
አፈወ መዓዛ (አፈዋተ) አውኀዘ እምልብሱ::

*ድንግል ሆይ የልጅሽን ተአምር የፈለጉ እኮ ብዙዎች ናቸው፣ ነገር ግን ሁሉን አመስግነው አልጨረሱም፣ በሜሮን የተቀደሰች (ሜሮንን የተቀባች) የልጅሽ ቤተ መቅደሱም ልጅ ወንድሜ የተባለ ልጅሽ መኃ.6.1-2. በታናሽነቱ (የሁለት ዓመት ሕፃን ሳለ) የተሰበሩና የደረቁ የዮሴፍ ብትሮች ወደተተከሉበትና ወደአበቡበት (የተሰበሩና የደረቁ የዮሴፍ ብትሮችን ወደ ተከለበትና ወደ አሳበበበት) ቦታ ወርዶ፣ መዓዛ ያለው ሽቱን ከልብሱ አፈሰሰ (አመነጨ) አለች::*

(35) 2ኛ. እመቤታችን፣ (12) ዓመት በቤተ መቅደስ እንደምትኖር ጌታ፣ምሥጢሩን ቀድሞ በምሳሌ የተናገረው፣ ሙሴን ለሚያምፁብኝ ልጆች ሁሉ ምልክት ሆና ትጠበቅ ዘንድ የአሮንን ብትር ወደ ቤተ መቅደስ መልሳት ማለቱ ነው ዘኍ.17.9-12::

www.ethiopianorthodox.org

አንዳንድ ሲቃውንት፣ ደግሞ እስመ ብዙኃን ድንግል የሚለውን ንባብ፣ እመ ብዙኃን ድንግል ይላሉ። ይህም ድንግል ሆይ የልጅሽን ተአምር የፈለጉ ብዙዎች ቢሆኑም፣ ሁሉን አሙስግነው አልጨረሱም "ለማለት" ነው።

## የተሰበረው ብትር ሜሮን ስለ መሆኑ፣

(ታሪክ) እመቤታችን፤ ዮሴፍ እና ሰሎሜ ጌታ በተወለደ (በ2) ዓመቱ ግንቦት (24) ቀን ጌታን ይዘው ወደ ግብጽ ሲሰደዱ፣ ዮሴፍ ስለ ሽመገለ የሚመረኮዘው የወይራ ብትርን ይዞ ነበር፣ ጌታም የዮሴፍን ብትር አንሥቶ (ከ7) ሰብሮ (7ቱን) ስብርባሪዎች በዚያ ቦታ ተክሎ ጉድጓድ ቢቆፍር፣ መዓዛው ደስ የሚያሰኝና ጣዕሙ እጅግ የሚጣፍጥ ውሃ ፈልቆ ፈሰሰ። ከዚያም ውሃውን በመሐል እጁ እየዘገነ የተከላቸው (7) የብትር ስብርባሪዎችን አጠጣቸው። ወዲያውም በቅለውና አድገው ታላላቅ ዛፎች ሆኑ፣ ከእነርሱም ከሽቱ ሁሉ ይልቅ ደስ የሚል መዓዛ ወጣ፣ በለሳንም ብሎ ጠራቸው። እናቱንም እናቴ ሆይ የተከልኩት ይህ በለሳን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከዚህ ይኖራል፣ ከእርሱም የተቀደሰ ቅብዓት ይገኛል አላት። ሜሮን በዘመነ ብሉይ ካህናት ሲሾሙና ነገሥታት ሲነግሡ የሚቀቡት የነበረ ሲሆን፣ ዘፀ.29.7-10.1ኛ ሳሙ.16.11-14። በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ምእመናን በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም፣ ማቴ. 28.-19. ተጠምቀው የጸጋ ልጅነትን የሚያገኙበት ነው ዮሐ.1-3። በሜሮን ሲታተሙም (ሲቀቡ) ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ፣ ሜሮንም የተቀደሰ ቅብዓት ነው። ራእ.18.13. አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትና ንዋየ ቅድሳትም፣ ይከብሩበታል። በለሳን ማለትም የሽቱ ዕንጨት ስም ሲሆን፣መገኛውም በገሊላና በይሁዳ፤

(36) ጌታ፣ የሚያምሁበኝ ልጆች ያላቸው፣ ዘኍ.17.9-12። ስጊዜው የእስራኤል ልጆች ቢሆኑም ፍጻሜው ግን በየጊዜው የሚነሱ መናፍቃን ናቸው።



በኢያሪኮ አገር ነው፣ የዕጣን ዕንጨት ከሚባሉት ዕፀዋትም አንዱ ይህ በለሳን የተባለው ዕፅ ነው፣ የግንቦት 24 እና 25 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር (219 ተአምረ ማርያም)።

ፎ፫-73 ስፍነ ድንግል ለጽጌኪ ተአምሪሁ እዜኑ፣
ወትሕትናሁ እኄሊ ሶበ ረፈቀ ለስምዖን በውስተ
ሕፅኑ (ውስተ ሕፅኑ)፣
ከመ ቆመኑ ቅድመ ዮሐንስ ድኑኑ፣
ወሚመ ከመ በረቀ በደብረ ታቦር ብርሃኑ፣
ወከደነ ሰማያተ ሥኑ።

*ድንግል ሆይ የልጅሽን ተአምር ስንቱን እናገራለሁ? ትሕትናውንስ ስንቱን አስባለሁ? በስምዖን እቅፍ ውስጥ በተያዘ ጊዜ ነውን? ሉቃ 2÷27-29 ወይስ በዮሐንስ ፊት አንገቱን ዘንበል አድርጎ እንደቆመ ነውን፣ ወይስ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን እንደገለጸ ነውን! ማቴ. 3. 13-17 ፣17. 1-3፣ ጌትነቱ (የአምላክነቱ ክብር) ሰማያትን እንደሞላ (ሥልጣኑ ሰማያትን እንደፈጠረ) ሳስብ ነውን! ትን. ዕን. 3.3-5።* (ታሪኩና ምሥጢሩ) ጌታ በተወለደ (በ40) ቀኑ በቤተ መቅደስ በካህኑ በስምዖን እቅፍ መያዙን፣ (በ30) ዘመኑ በዮሐንስ እጅ መጠመቁን፤ በደብረ ታቦር፣ ብርሃነ መለኮቱን መግለጹንና ትሕትናን ገንዘብ ማድረጉን የሚያስረዳ ነው፣ ሉቃ. 2.29-36፣ (የየካቲት (8) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር እና 215 ተአምረ ማርያም)።

ፎ፬-74 በላዕሌኪ ወበዮርዳኖስ ወበታቦር ሥልሰ ጊዜያተ፣
ዘአልቦ ተውሳክ ወኢ ሕፀተ (ዘአልቦ ተወሳከ ወአልቦ ሕፀተ)፣
ለውሉደ ሰብእ ያርኢ ዘሥላሴሁ ገጸተ፣
ጽጌኪ ድንግል ተአምሪሁ ከሠተ፣
ወበሀዳሉ አብርሀ ጽልመተ።

(37) መና፣ ማለት ጌታ ለእስራኤል ልጆች ከሰማይ ያወረደላቸው መና፡ (ምግብ) ማለት ነው ዘፀ.16.13-17።

www.ethiopianorthodox.org

ድንግል ሆይ ልጅሽ በአንቺ፣ በዮርዳኖስና በደብረ ታቦር ምንም ጭማሪና ጉድለት የሌለውን የሦስትነቱን አካላት ለሰው ልጆች ሦስት ጊዜ ይገልጽ ዘንድ ተአምሩን አሳየ፣ በብርሃኑም ጨለማን አራቀ::

## ጌታ፣ 9ኙን ትቶ 3ቱን ይዞ፣ ወደ ደብረታቦር ለምን ወጣ?

ጌታ፣ ማቴዎስና ማርቆስ፣ ከ6 ቀን በኋላ ኢየሱስ፣ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ወደ ረጅም ተራራ ወሰዳቸው ማለታቸው፣ ማቴ.17.1-2፣ ማር.9.2-3. ቂሣርያ በሚባል አገር ጌታ እኔን ሰው ማን ይሉኛል፣ እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ ብሎ ደቀመዛሙርቱን ከጠየቀ ከ6 ቀን በኋላ (በ7ኛው ቀን) ማለታቸው ሲሆን፣ ማቴ.16.13-18፣ ሉቃስ በበኩሉ፣ በ8 ቀን ወደ ተራራ ወጣ ማለቱ ሉቃ.9.27-29. እንደዚሁ ጌታ በዚህ ከሚቆሙ ሰዎች፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት እስኪያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ ብሎ ለደቀመዛሙርቱ በተናገረ (በ8ኛው) ቀን ማለቱ ነው ሉቃ. 9.27-28:: ጌታ በጋብቻ የተወሰነ ሙሴን የነቢያት አለቃ፣ እንዲሁም በጋብቻ የተወሰነ ጴጥሮስን የሐዋርያት አለቃ ማድረጉ ስለምንድነው? የደናግልንስ ክብር አቅልሎ ነውን ቢሉ? በድንግልናው ከሚመካ ድንግል ይልቅ፣ጌታ ስለ ኃጢአቱ በንስሓ የሚያለቅሰውን ዘማዊ (አመንዝራን) ይወዳልና ነው::ደናግልም በአገቡት ሰዎች ላይ እየተመኩ ዋጋ እንዳያጡ ነው እንጂ፣ በክብርስ ደናግል ይበልጣሉ:: ሁለቱን ከነቢያት፣ ሦስቱን ከሐዋርያት አድርጎ በደብረታቦር ላይ ብርሃነ መለኮቱን መግለጹም የተራራ ምሳሌ በሆነች ቤተክርስቲያን፣ የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕፍት፣ እንዲነገሩባትና በዚህ ዓለም የተወሰኑ፣ ደናግልም መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ ብሎ ለማስረዳት ነው:: እነዚህ (5ቱ) የጌታ ባለሟሎችም፣ የዛሬ (የ5ቱ) ቀዳስያን ምሳሌ ናቸው::

(38) እስራኤል፣ ከሰማይ የወረደላቸው ምግብ፣ አዲስ ነገር ስለሆነ ይህ፣ ነገር ምንድነው? ለማለት መና ብለው ጠሩት ዘፀ.16.32::



ይሁዳን ጨምሮ ሌሎች (8) ሐዋርያት ወደ ተራራው እንዳይወጡ ያደረገበት ምሥጢርም፣ ያአትትዎ ለኃጥእ ከመ ኢይርአይ ስብሐተ እግዚአብሔር፣ ማለትም የእግዚአብሔርን ብርሃን (ክብሩን) እንዳያይ ኃጥእ ይሁዳን ከደብረታቦር ያርቁታል ተብሎ በይሁዳ ትንቢት ተነግሮ ነበርና ነው:: ኢሳ.26.10-11:: ጌታ፣ወደፊት በሚመጣበት ጊዜም፣ እናንተ! የአባቴ ብሩካን ኑ-ብሎ ጻድቃንን ወደ መንግሥተ ሰማያት፣ እናንተ! ርጉማን ሂዱ ብሎ ኃጥአንን ወደዘለዓለም እሳት፣ ፍርድ የሚሰጥበት ምሳሌ ነውና:: ማቴ.25.31-46:: ይሁዳን ትቶ ደቀመዛሙርቱን በሙሉ ወደ ተራራ ይዞ ቢወጣ ኖሮም፣ ይሁዳ ከመለኮቱ ምሥጢር ቢለየኝ፣ ከሞቱ ገባሁበት ይል ነበርና፣ (8ቱ) ሐዋርያት በይሁዳ ምክንያት፣ ወደ ተራራው ሳይወጡ ቀርተዋል:: ነገር ግን ለሦስቱ ደቀመዛሙርት፣ በደብረ ታቦር የተገለጸው ምሥጢር (ለ8ቱም) ተገልጾላቸዋል:: ልክ! በደብረሲና (በድንኳን ውስጥ) በቍጥር (70) ሆነው በተሰበሰቡ በእስራኤል ሽማግሌዎች ላይ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ሲያድር፣ ወደ ደብረሲና ላልወጡት እና በከተማ ለነበሩ ኤልዳድ፣ ሞዳድ ለተባሉ ሁለት ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳደረባቸው ማለት ነው:: ዘኁ.11.24-27፣ ማቴ.17.1 ንባቡና ትርጓሜው:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ ታሪክም ጌታ፣ ሁለቱን (ማቴዎስንና ዮሐንስን) (ከ12ቱ) ሐዋርያት፣ ሁለቱን (ማርቆስንና ሉቃስን) (ከ72ቱ) አርድእት አድርጎ ወንጌልን ማስጻፉ ስለምንድነው ቢሉ?፣ቀኖናቸው ከሐዋርያት የሆኑት ማቴዎስና ዮሐንስ ብቻ ቢጽፉ፣ይህ (የ72ቱ) አርድእት ትምህርት አይደለምና፣ ትምርታችሁን አንቀበልም ብለው አይሁድ፣ እንዳያሰናክሉ ነው:: እንደዚሁም ቀኖናቸው (ከ72ቱ) አርድዕት የሆኑት ማርቆስና ሉቃስ ብቻ ቢጽፉ፣ ይህ የሐዋርያት ትምህርት አይደለምና፣ትምህርታችሁን አንቀበልም ብለው አይሁድ፣ እንዳያሰናክሉ ነው::

(39) እስራኤል፣ ዓለም በተፈጠረ ከ3844 ዓመት፣ (ከሚያዝያ 21) ቀን ጀምሮ እስከ 3884 ዓመት ግንቦት 14 ቀን ድረስ (40) ዓመት መናን ተመገቡ ዘፀ.16.1-17፣ መጽ.ኢያ.5.10-12::

www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፍ፣ ሙሴና ኤልያስ፣ በደብረታቦር ከጌታ ጋር ተነጋገሩ ያለ! እነሱ መሆናቸው በምን ታወቀ?

መጽሐፍ፣ ሞቶ የነበረውና መቃብሩን ማንም የማያውቀው ሙሴ፣ ዘዳ.34.5-7፣ ከሞት ተሠውሮ ወደ ብሔረ ሕያዋን በሰረገላ ያረገው ኤልያስም፣ 2ኛ.ነገ.2.7-12. ከጌታ ጋር በደብረታቦር ተነጋገሩ ያለ! እነሱ መሆናቸው በምን ታውቆ ነው ቢሉ ማቴ.17.2-4. ሙሴ ቀድሞ ጌታን ፊትህን ላየው እወዳለሁ ቢለው ፊቴን ማየት አይቻልም። በኋላ ዘመን (ሥጋ ለብሼ) ግን እገለጽልሃለሁ ብሎ በሰጠው ተስፋ ዘጸ.33.17-23. ሙሴ ከመቃብር ተነሥቶ ወደ ደብረታቦር ተራራ መጥቶ ጌታ ሆይ በአንተ ኃይል ባህር ከፍዬ፣ እስራኤልን በደረቅ አሻገርኩ፣ ጠላት አጠፋሁ ዘጸ.14.21-31፣ ዕብ.15.21-26፣ ከሰማይ መናን (እንጀራን) አውርጄ መገብኩ፣ ከጭንጫ ድንጋይ ላይም ውሃን አፈለቅሁ! ዘጸ.16.4-19፣ ዘኍ.20.2-10፣ ኤልያስ በበኩሉ ከብሔረ ሕያዋን መጥቶ ጌታ ሆይ ሕግህን ያልጠበቁ ሰዎች ሕግህን ያውቁ ዘንድ (3) ዓመት (ከ6) ወር በ[illegible] ኃይል ዝናብ ከሰማይ እንዳይወርድ ከለከልኩ፣ በኋላም [illegible] እንዲወርድ አደረግሁ 1ኛ.ነገ.17.1-9 እና 18.1-46፣ [illegible].25-27፣ [illegible]ል.ያዕ.9.17-19፣ እሳትንም ከሰማይ አውርጄ ሕግህን የዘነጉ ሰዎችን አስፈጀሁ 2ኛ.ነገ.1.5-15፣ እያሉ ከጌታ ጋር ሲነጋገሩ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ሰምተዋልና ነው። ለዚህም ነው ቅዱስ ጴጥሮስ እነሱ (ሙሴና ኤልያስ) መሆናቸውን አረጋግጦ በዚያው በደብረታቦር ጌታ ሆይ ብትወድስ ለአንተ አንድ ለሙሴ አንድ፣ ለኤልያስ አንድ ሦስት ዳስን እንሥራ ያለው። ማቴ.17.4-5

## አራቱ ወንጌላውያን፣ ወንጌልን መቼና በምን ቋንቋ ጻፉ?

(ታሪክ) ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ ወንጌልን መቼና በምን ቋንቋ ጻፉ ቢሉ፡-

[illegible] እስራኤል፣ (40) ዓመት የተመገቡት መና፣ለምን ተቋረጠ? →



<u>ማቴዎስ</u>፣ ጌታ በዐረገ በ9ኛው ዓመት፣ ፍልስጥኤም በምትባል አገር በዕብራይስጥ ቋንቋ ጻፈ። እርሱ እና ዮሐንስም በኢየሩሳሌም ወደ ዕርዕ ቋንቋ ተረጐመ።

<u>ማርቆስ</u>፣ ጌታ በዐረገ በ12ኛው ዓመት አፍርንጊ ውስጥ በምትገኝ በሮም አገር በሮማይስጥ ቋንቋ ጻፈ። ጴጥሮስም በዕርዕ ቋንቋ ተረጐመ።

<u>ሉቃስ</u>፣ ጌታ በዐረገ በ22ኛው ዓመት መቄዶንያ በምትባል አገር ወንጌሉንና የሐዋርያትን ሥራ በዮናኒ ቋንቋ ጻፈ።

<u>ዮሐንስ</u>፣ ጌታ በዐረገ በ30ኛው (በ35ኛው) ዓመት ኤፌሶን በምትባል አገር በዮናኒ ቋንቋ ጻፈ። በዕርዕ ቋንቋም ተረጐመ። የእያንዳንዳቸው የወንጌል ትርጓሜ መጨረሻ እና መጽሐፈ ምሥጢር ምዕ.30.ቍ.32-35።

፸፭-75 እምትእምርተ ሞቱ ለጽጌኪ ዓለም ጽልመተ ድኅረ ተከድነ፣
ገይሠኪ በአስቆቅዎ ኀበ ሥጋሁ ተደፍነ፣
አመ ርኢኪዮ ድንግል እንዘ ይትአጸፍ ብርሃነ፣
ወልድየ ብህልኪዮ ተንሣእከኑ እሙነ፣
ወሰዐምኪ በአፉኪ አፉሁ ቍርባነ።

*ድንግል ሆይ ከልጅሽ ሞት ድንቅ ተአምር የተነሣ (በልጅሽ ስቅለት ጊዜ) ዓለም ጨለማን ከለበሰ በኋላ፣ ማቴ.27.45 ሥጋው ወደተቀበረበት መቃብር እያለቀስሺ ገሰግሰሺ ፣በመሄድ፣ ብርሃንን ተጐናጽፎ ባየሽው ጊዜ ልጄ! በእውነት ተነሣህን? ብለሽ በአፍሽ፣ ቍርባንም አፉን ሳምሽ፡*

(ታሪክ) ጌታ፣ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ ጊዜ እመቤታችን ከመቃብሩ ሄዳ ተነሥቶ ስለ አገኘችው ልጄ! ተነሣህን ያለችው ነው (98 ተአምረ ማርያም) ስለ መልክአ ቍርባን ደራሲም (3) አስተያየቶች አሉ። እነሱም

(41) ዓለም በተፈጠረ በ3884 ዓመት፣ ግንቦት (14) ቀን የእስራኤል መና የተቋረጠበት ምክንያት፣ እስራኤል ጌታ ያልፈቀደላቸውን እህል (ሸንብራ) ጌልገላ (ፊንቆን) በምትባል ቦታ ሰርቀው ስለበሉ ነው መጽ. ኢያ.5.10-12 እና ትጻሴ ኢጲፋንዮስ፣ ምዕ.2 ቍ.40 ንባቡና ትርጓሜው። —

www.ethiopianorthodox.org

1ኛ. መጽሐፈ ምሥጢር እንደተናገረው፣ መልክአ ቍርባንን የደረሰ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ነው::
2ኛ. አዬ በእደማርያም ነው የሚሉ ሊቃውንት ሲኖሩ፣
3ኛ. ደግሞ መምህር ወልደጊዮርጊስ ዘአንኮበር ሚካኤል ነው የሚሉ ሊቃውንትም አሉ::

ፎ፮-76 ስፍነ (እስፍንተ) ነፍሳተ ሰብእ ኃይለ ተአምርኪ ዘመሠጠ፣
እምአፈ ሲኦል ወሞት እለ ለመዱ ውኂጠ፣
እንዘ ይብል አቡኪ አሜሃ መሰንቆ ትንሣኤ ዘበጠ፣
እስመ ሰበረ ኆኃተ ብርት ወመንሠገ ሐዊን ቀጥቀጠ፣
ጽጌኪ ማርያም ፄዋነ ዘሜጠ::

ማርያም ሆይ የተአምርሽ ኃይል (ልጅሽ) መዋጥን ከለመዱ ከሞትና ከሲኦል አፍ መዝ.88.48 ያወጣቸው የሰዎች ነፍስ መጠን ምን ያህል ነው? (ከሲኦል ያወጣቸው ስንቶችን የሰዎች ነፍሳት ነው?) ምርኳችንን የመለሰ ልጅሽም የብረቱን በር ሰብሮአልና፤ የነሐሱንም ቁልፍ ቀጥቅጦአልና፣ (መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስ ዘፍ.3.10-20. በአንቺ ጠፋልን) እያለ ያን ጊዜ አባትሽ ዳዊት የትንሣኤ መሰንቆን መታ (ደስ ብሎት ዘመረ)፣ መዝ.106 ፤ 15-17 ::

ፎ፯-77 ለጽጌኪ ማርያም ከመ ይጠይቅ ትእምርቶ፣
በድንግልና ልደቶ ወውስተ ሰማያት ዕርገቶ፣
እመ ኢአምነ ሰሚዖ እሙታን ተንሥኦቶ፣
ኅበ መቃብሩ ለለዓመ ለብርሃነ ሰማይ ርደቶ፣
ይባእ ወይርአይ ዘይነብብ ከንቶ::

*ማርያም ሆይ ከንቱ ነገርን የሚናገር ሰው የልጅሽን ተአምሩን ይረዳ ዘንድ ማለትም በድንግልና መወለዱን፣ማቴ. 1.18 ከሙታን ተለይቶ መነሣቱንና ማር 16. 6. ወደ ሰማይ ማረጉን፣ ሉቃ.24.50-53 ሰምቶ፣ ካላመነ በየዓመቱ ወደመቃብሩ የሚወርደውን ብርሃን ገብቶ ይመልከት::*

(42) እስራኤል፣ (40) ዓመት በምድረ በዳ ከሰማይ የወረደላቸውና የበሉት መና፣ ከሞት አላዳናቸውም ዮሐ.6.48-50::



## ስለ ኢትዮጵያዊው ሰው የወረደ ብርሃን፣

(ታሪክ) ከዓመታት በአንዱ ዓመት የጌታን ትንሣኤ በኢየሩሳሌም ሊያከብሩ ሰዎች ከየሀገሩ ተሰበሰቡ:: ከኢትዮጵያም አንድ ሰው ብቻ ተገኝቶ ነበር፣ እሱንም አንተ ፊትህ የጠቆረ ነውና ከጉባኤያችን ተለይ ብለው ለዩት:: እርሱም እመቤታችን በስቅለት ጊዜ ለልጇ ባለቀሰችበት በቀራንዮ ቆሞ እየጸለየ ሳለ፣ ብርሃን ከሰማይ ወርዶ ሲያርፍበት ሁሉም አዩ:: በእውነትም የኢትዮጵያ ሰዎች ሃይማኖታቸው የቀና ነው ብለው ይቅርታ ጠየቁት:: እሱም ይቅር ብሏቸው ሰላምና ፍቅር በመካከላቸው ሰፈነ:: (133 ተአምረ ማርያም):: ፍጡርን መንቀፍ ፈጣሪን መንቀፍ ነውና፣ ፍጡርን መንቀፍ እንደማይገባ:: "መጽሐፍ" በውኑ ሥራ ሠሪውን አልሠራኸኝም ይለዋልን ኢሳ. 29.15-17. "ሸክላስ ሠሪውን" እንዲህ አድርገህ አትሠራኝም ሊለው ይቻለዋልን ሲል ያስተምረናል ሮሜ 9.19-21::

ፎ፰-78 ጽጌ-ደመና ማርያም ሥጋኪ ዘገብረ ግልባቤ፣
ትእምርተ-መዊዕ ምሕርካ ነሢኦ እምድረ-ምንዳቤ፣
እመ ዐርገ ወልድ ውስተ ደብረ ስሂን
(ውስተ ወግረ ስሂን) ወደብረ ከርቤ፣
አርኅዉ ኆኃተ መኳንንት ለንጉሠ ስብሐት ዘይቤ፣
ተሰምዐ ቃለ ቀርን ወደምፀ ይባቤ::

የደመና አበባ ማርያም ሆይ ሥጋሽን የለበሰ ወልድ ከመከራ ቦታ (ከሲኦል) የድል መንሣት ምልክት የሆነ ምርኮን ይዞ ወደ ሰማያት ባረገ ጊዜ፣መኳንንት! ለክብር ንጉሥ በርን ክፈቱ የሚል የመለከትና የዕልልታ ድምፅ ተሰማ:: መዝ. 23.7-10፣ ሉቃ. 24. 50-51፣ የሐዋ 1.6-11::

(43) ሰው፣ ከእርሱ (ከመናው) በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ የወረደና አማናዊ መና የተባለ ጌታ የሰጠን ሥጋውና ደሙ የዘለዓለም ሕይወት ነው ዮሐ.6.49-52::

www.ethiopianorthodox.org

(ታሪኩ) ጌታ መላእክት እያመሰገኑት ወደ ሰማይ የማረጉ ታሪክ ሲሆን እመቤታችንን የደመና አበባ ማለቱም፣ አበባ በደመና ጊዜ ፈክቶና ጎልቶ ይታያል። ስለዚህ ነቢዩ ኤልያስና ነቢዩ ኢሳይያስ በደመና ከመሰሏት ከእመቤታችን፣1ኛ.ነገ.18.41-46፣ኢሳ.19.1. አበባ በምድራችን ተገለጸ ተብሎ ትንቢት የተነገረለት ልጇ፣ መኃ. 2.12. መወለዱን የሚያስረዳ ነው።

## የጌታ፣ መግደላዊት ማርያምን የአትንኪኝ ምሥጢራት፣

(ከ12) ዓመት ጀምሮ ደም የሚፈስሳትን (ደም መፍሰስ ከጀመራት (12) ዓመት የሆናትን ሴት) በእጇ ተዳሶ የፈወሰ፣ በተወለደች (በ12) ዓመቷ የሞተች የኢያኤሮስን ልጅ በእጁ ዳስሶ ከሞት ያስነሣ፣ ማር.5.35.43፣ የዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ እንደገለጸውም፣ በሰንበት ቀን ፈውሶኛል ብሎ በዕለተ ዓርብ ከአይሁድ ጋር አብሮ፣ በጥፊ የሚመታውንና (የ38) ዓመት በሽተኛ የነበረውን ሰው ከደዌ ሥጋ ፈውሶ፣ ደዌ ነፍስ እንዳያገኘው ዳግመኛ ኃጢአትን አትሥራ በማለት ያስተማረ ዮሐ.5.5-15፣ በስቅለቱ ጊዜም ከጠዋቱ (3) ሰዓት ላይ የመለኮቱን ባሕርይ ለመግለጽ ከአይሁድ ሲሠወር እንዳትናገሪ ቢላት እንኳ በዓይኗ ጠቅሳ የምታስይዘውን እና በአመንዝሪነቷ እንደ ሙሴ ሕግ ዘሌ.20.10-27. በድንጋይ ልትወገር የነበረች ሴትን እኔ አልፈርድብሽም። ነገር ግን ደግመሽ ኃጢአትን አትሥሪ ያለ የምሕረት ጌታ፣ ዮሐ.8.5-12. (7) አጋንንትን ያወጣላትንና ታገለግለው የነበረች መግደላዊት ማርያምን ሉቃ.8.2. በትንሣኤው ቀን፣ ገና ወደ አባቴ ዐላረግሁምና አትንኪኝ ለምን አላት? ቢሉ ዮሐ.20.11-19፣

1ኛ. ጌታ፣ ትንሣኤውን ከሐዋርያት አስቀድሞ ለእርሷ በመግለጹ ምክንያት፣ ደንግጣ አትክልት ጠባቂ እንጂ ጌታ አልመሰላትም ነበርና፣ በፍጹም ልብ ገና ባለማመኗ አትንኪኝ አላት።

(44) ጻድቁ ኢዮብ እና ቅዱስ ያሬድ፣ ጌታ በደመና ስለሚያደርገው ድንቅ ሥራ ምን አሉ? →



2ኛ. ትንሣኤውን ከተረዳች በኋላ ወዲያውኑ የሚያርግ (የመሰናበቻው ጊዜ የደረሰ) መስ[illegible]ት፣ ወደ እርሱ ስትቀርብ ወደላከኝ ወደ አባቴ እሄዳለሁ ብሎ ቀድሞ ለሐዋርያት ብዙ ተናግሮ የነበረውን የዕርገቱን ምሥጢር ዮሐ.16.1-12. ለመግለጽ እና በእርግጥ የሚያርግበት ጊዜ ገና መሆኑን ሲያስረዳት ነው።

3ኛ. በዮሐንስ የወንጌል ትርጉም ምዕ. 20.11-18 እና በመጽሐፈ ምሥጢር፣ ምዕ. 20.ቁ.61-67. እንደተገለጸው ካህናት፣ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ሳሉ ሊነኳቸው እንደሚይገባ ለማስረዳት፣ እንዲሁም ካህናት ሸንጂ፣ ምእመናን ወደ ክህነት ምሥጢር ገብተው ሥጋዬንና ደሜን መንካት (መዳሰስ) አይችሉም ሲል፣ የምእመናንና የካህናትን ሥርዓት ለመለየት፣ አትንኪኝ አላት።

ይህም ይታወቅ ዘንድ እርሷን እሑድ ጠዋት አትንኪኝ ከአላት በኋላ፣ እሑድ ማታ በተዘጋ ቤት ገብቶ ሐዋርያትን ሰላም ለእናንተ ይሁን፣ ባላቸው ጊዜ ሲደነግጡ አይቶ እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፣ ዳስሱኝም ብሎ የዛሬ ካህናት ምሳሌ የሆኑ ሐዋርያት እንዲዳስሱት መፍቀዱ ነው። ሉቃ.24.36-40፣ ዮሐ.20.18-21። ከሞት እንደተነሣ ወዲያው ዐለማረጉ እና በምድር (40) ቀን ቆይቶ ማረጉም መናፍቃን፣ ዕርገቱ ምትሐት (ውሸት) ነው እንዳይሉና ለዕርገቱ የጥርጥር ምክንያት እንዳያደርጉ ነው። ጥንተ ዕርገቱም ግንቦት (8) ቀን ሐሙስ ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረደላቸውም ግንቦት (18) ቀን እሑድ ነው (የሐዋ.2.1-5፣ የግንቦት 8 እና 18 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)

(45) ጻድቁ ኢዮብ እና ቅዱስ ያሬድ፣ የአቍር ሰማይ ዲበ ደመና፣ ወኢይሠጠጥ ደመናሁ፣ ውሃውን በደመና ቋጥሮ ከሰማይ የሚያመጣውና ደመናው እንዳይቀደድ የሚያደርግ ጌታ፣ ሥራው ዕፁብ ድንቅ ነው አሉ መጽ.ኢዮ.26.8-10 እና የክረምት ዝማሬ።

www.ethiopianorthodox.org

ሯ፱-79 መዓዚ፡ ጥዑም ዘኤርምያስ ጽጌ-ከርሥኪ ጽርስፎራ፣
አመ መሠጠኪ ድንግል በዒና ተአምር ነከራ፣ ዘነከራ የሚሉም አሉ
ተቀበሉኪ በስብሐት ሥርግዋነ መብረቅ ሐራ፣
ቦ፡ ዘይዘብጥ ከበሮ ወቦ፡ ዘይነፍሕ እንዚራ፣
እስከ አብኡኪ ለንግሥት ዘብርሃን ደብተራ፡፡

*ድንግል ሆይ የሕይወት ኅብስት የተባለና ሥጋውን የሰጠን ዮሐ. 6.49-50. ደስ የሚያሰኝ የኤርምያስ መዓዛ የሆነ የማሕፀንሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መዓዛ በአለውና በሚያስደንቅ ተአምር በዐሳረገሽ ጊዜ፣ ብርሃንን የለበሱ መላእክት በክብርና በምስጋና ተቀበሉሽ፣ ንግሥት! አንቺን ወደ ብርሃን ድንኳን እስከ አስገቡሽ ድረስም ከበሮን የሚመታ ነበር፣ እንዚራንም የሚነፋ ነበር፡፡ (ታሪክ) ጌታ፣ ደስ የሚያሰኝ የኤርምያስ መዓዛ ስለምን ተባለ ቢሉ ነቢዩ ኤርምያስ ጌታ እንደገለጸለት፣ የኢየሩሳሌም ሰዎች በባቢሎን ንጉሥ ይማረካሉ፣ ኢየሩሳሌምም ትጠፋለች ብሎ ሲናገር በንጉሡ ትእዛዝ ቆሻሻ ካለበት ጉድጓድ ተጣለ፣ የጉድጓዱ ቆሻሻም እንዳይሸተው የእግዚአብሔር መልአክ ፊላሳን (ፒላሳን) የሚባል ዕንጨትን ከገነት አምጥቶ ሰጥቶታል ኤርምያስም በዚህ ዕንጨት መዓዛ ደስ ተሰኝቶአል የትንቢተ ኤርምያስ የትርጓሜ መቅድም እና ኤር.38.1-7፡፡ ስለዚህም የማኅሌተ ጽጌ ደራሲ አባ ጽጌ ብርሃን (አባ ጽጌ ድንግል)* እመቤታችን፣ መዓዛሆሙ ለቅዱሳን (የቅዱሳን መዓዛ ረድኤታቸው) የሚባል ጌታን በድንግልና ፀንሳ፣ በድንግልና ወልዳለችና፣ ጌታን መዓዛ፡ ጥዑም ዘኤርምያስ (ደስ የሚያሰኝ የኤርምያስ መዓዛ) አለው፡ ፡ በሌላ በኩልም ነቢዩ ኤርምያስ ለሰው መዓዛ በረከት የምትሆን ጌታ ሆይ ስለ ወገኖችህ እስራኤልና መዓዛ

(46) ዘኢተገብረ ለመላእክት ተገብረ ለካህናት፣ ‹‹ለመላእክት ያልተደረገ (ያልተሰጠ ሥልጣነ ክህነት) ‹‹የአዳም ልጆች ለሆኑ ለሐዋርያት (ለካህናት) ተሰጠ››ማቴ.18 እና18፣ቅዳሴ አትናቴዎስ ምዕ.5.ቍ 29 ንባብና ትርጓሜው፡፡



ስላለው ስለ ኪሩቤል ዕጣን እለምንሃለሁ እያለ የጸለየውን ጸሎት የሚያስረዳ ምሥጢር ሲሆን፣ ተረ.ኤር.11.37-39. ሱራፌልና ኪሩቤልም በማዕጠንት እያጠኑ ድንግል ማርያምን በምስጋና ማሳረጋቸውን የሚገልጽ ኃይለ ቃል ነው፡፡ የኤርምያስ አባቱ ኬልቅያስ፣ እናቱ ማርታ ይባላሉ፣ አናቶት በሚባል አገር ተወለደ ኤር.1.1-2. ኤርምያስ ማለት ከእግዚአብሔር የተላከ ብርሃን (እግዚአብሔር ከፍ ያደርጋል) ማለት ነው በነቢይነት የተጠራውም ዓለም በተፈጠረ በ4874 ዓመት ነው፡፡

<u>አደራዋን ያልበላችና የማትበላ ታማኝ ፍጥረት፣</u>

(ታሪክ) በኢየሩሳሌም ምርኮ ጊዜ፣ ኤርምያስ ስለ ንዋየ ቅድሳት ምን ላድርግ ብሎ ጌታን ቢጠይቅ፣ ጌታ ለምድር አደራ ስጣት አለውና ጌታ እንደነገረው አደረገ፡፡ ምድርም የፈጣሪዋን ቃል ተቀብላ ንዋየ ቅድሳቱንም ውጣ (አደራዋን ሸሽጋ) ኖራ (በ46) ዓመት የታነጸውን ቤተ መቅደስ አፍርሼ (በ3) ቀን እሠራዋለሁ እንዴት ይላል ብለው አይሁድ ጌታን የተቃወሙበትን ቤተ መቅደስ፣ ንጉሥ ዘሩባቤል ሠርቶ ሲጨርሰ ዮሐ.2.19-20 ዘሩባቤል እስኪመጣ ድረስ ገንዘብሽን ጠብቂ ተብሎ እንደተነገራት፣ ካህኑ ዮሴዕ (ኢያሱ) ልብሰተክህኖውን ለብሶ ሳለ፣ እስራኤል ከተማረኩበት ጊዜ ጀምሮ ዘሩባቤል ቤተ መቅደሱን ሠርቶ እስከጨረሰበት ጊዜ ድረስ የነበረው ዘመንም (117) ዓመት ነበርና፣ (በ117) ዓመቱ ንዋየ ቅድሳቱ፣ ቀድሞ ከነበረበት ቦታ በተአምር ተገኝቷል፡ ምድርም ከፈጣሪ የተቀበለችውን አደራ አስረክባለች፣ ተረ.ኤር. 8.5-21. ጌታ በክብር ሲመጣም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ያረፉትን ሰዎች ሁሉ፣

(47) ከዕዝራ ሱቱኤል እስከ መጽሐፈ ሄኖክ (በ81 መጽሐፍ ቅዱስ ከገጽ 723 እስከ 853) በአሉት ብሉያት መጻሕፍት፣ መልአክ (መላእክት) የሚል (305) ይገኛል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ከነሥሮቻቸው ሲነቅሉ አቀርባ አደራዋን ትወጣለች፣ኢሳ.26.19-20፤ ዕዝ.ሱቱ.6.33።

## ድንጋዩ ግንባሩ መብሳት ተመታ?

(ታሪክ) ነቢዩ ኤርምያስ ሲያስተምር ኖሮ በመጨረሻ እስራኤል በድንጋይ ሊወግሩት ሲሉ፣ ጌታዬ ሆይ የገለጽክልኝን ምሥጢር ሁሉ ለደቀ መዛሙርቴ (ለባሮክና ለአቤሜሌክ) እስክነግራቸው ድረስ ድንጋዩን እንደ ሰው አድርግልኝ ብሎ ሲጸልይ፣ ድንጋዩ ፍጹም ሰው (ኤርምያስን) መስሎ ቆመ። በዚህ ጊዜም አሕዛብ ኤርምያስ መስሏቸው ድንጋዩን በድንጋይ ሲወግሩ ኤርምያስ ከጌታ የተገለጸለትን ምሥጢር ለባሮክና ለአቤሜሌክ ገልጾ፣ ከጨረሰና ሰማዕትነትን ለመቀበል ከተዘጋጀ በኋላ፣ ሄዶ በሕዝቡ መካከል ቆመ፣ እነሱ የሚወግሩት ድንጋይም እናንተ ሰነፎች (አላዋቂዎች) ስለምን በድንጋይ ትወግሩኛላችሁ፤ ኤርምያስ እኮ! በመካከላችሁ ቆሟል ብሎ ሲጮህ፣ ኤርምያስን አይተው በድንጋይ ወገሩት፣ እሱም ሰማዕትነትን ተቀበለ። ያንን ድንጋይም የኤርምያስ ረዳቱና ምስክሩ ነው የሚል በውስጡ ጽፈው፣ በመቃብሩ አፍ እንደ መዝጊያ አድርገው አኖሩት፣ ተረ. ኤር. 11. 53-62. ግንቦት (5) ቀን።

፹80 እግዚአብሔር ጽጌ ትንቢት ለቢሶ ሥጋኪ ሥጋ ዚአነ፣
ከመ አስተርአየ በምድር ወተአምረ ለነ፣
ንዌድሰኪ እንዘ ንብል ምክሐ ዘመድነ፣
ዮም በፍሥሓ ለማርያም እምነ፣
አስተርአዮ በሰማይ ከነ።

የባሕርያችን መመኪያ የሆንሽ እመቤታችን ማርያም ሆይ አበባ በምድራችን ተገለጸ (ታየ) ተብሎ ትንቢት የተነገረለት ጌታ መኃ. 2.12. የእኛ ሥጋ የሆነ ሥጋሽን ለብሶ በምድር እንደታየና

(48) እንደ አባብ ብልህ፣ እንደ ርግብ የዋህ ሁኑ አለ ጌታ/ማቴ.10.16።



እንደታወቀልን ሁሉ፣ ዛሬ ለእናታችን ለማርያም በሰማይ የክብር መገለጽ (ፍጹም ደስታ) ሆነ እያልን እናመሰግንሻለን። (ታሪክና ምሥጢሩ) ነቢዩ ኢሳይያስ ከእሴይ ግንድ፣ በትር ይወጣል ከሥሩም ቍጥቋጦ ያፈራል፣የተባለው ትንቢት ሲሆን፣ በትር እመቤታችን፣ ጽጌ፡ (አበባ) ጌታ መሆኑ የተገለጸበት ነው፣ ኢሳ. 11.1-2።

፹፩- 81 በብሔር በነበ ፈለስኪ ግዲግዮ ብሔረ፣
ስብሐተ አርባዕኪ ጽጌ (ስብሐተ አርብዓኪ ድንግል) ከነ መዝሙረ፣
ተአምርኪ ድንግል በከመ ነገረ፣
ጌቴ ሴማን (ሴማኒ) መቃብርኪ ከመ ትከውን ሐመረ፣
ሥመሪ ታዕድዉኒ ዘእሳት ባሕረ።

ጽጌ የተባልሽ ድንግል ሆይ አገሬን ትተሽ በሄድሽበት አገር (የ40) ቀን ምስጋናሽ መዝሙርን ሆነኝ፣ ተአምርሽ እንደተናገረ ጌቴ ሴማን (ጌቴ ሴማኒ) የምትባል መቃብርሽ መርከብን በሆነች ጊዜ፣ የእሳት ባሕርን ታሻግረኝ ዘንድ ውደጂ፣ (ፍቀጂ)። ስብሐተ አርባዕኪ ጽጌ የሚለው ንባብም፣ ሲተረጐም ስብሐተ አርብዓኪ፣ "የ40 ቀን ምስጋናሽ መዝሙርን ሆነኝ" ከሚለው ትርጉም የተለየ ትርጉም የለውም፣ ምክንያቱም አርባዕ ማለት አራት ማለት ነው። ስለሆነም በዚህ የትርጉም አነጋገር (አገላለጽ) አራቱን ዐሥር (40) ቀን ብሎ መቍጠሩ (መግለጹ) ነውና። አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ፣ ስብሐተ አርባብኪ ጽጌ ኮነኒ መዝሙረ ይላሉ፣ አርባብ ማለትም የመላእክት ስም ነው፣ ይህም መላእክት የሚያመሰግኑት ምስጋናሽ፣ መዝሙርን ሆነኝ ለማለት ነው።የ40 ቀን ምስጋናሽ መዝሙርን ሆነኝ ማለቱም፣ አባ ጽጌ ብርሃንና ጓደኛው አባ ገብረ ማርያም፣ ማኅሌተ ጽጌን ሲደርሱ የመዘመር ሀብት በተሰጠው በዳዊት መዝሙር መጠን (150) አድርገው ነበር የደረሱት። እንዲሁም በየዓመቱ ከየአገራቸው እየተዘዋወሩ ማለትም ከመስከረም (26) ቀን እስከ ኅዳር (5) ቀን ድረስ 40ውን ቀን በሰላምና በፍቅር በማኅሌት ይዘምሩ ነበርና ነው።

(49) አባብ፣ብልህ ነው የተባለባቸው ምክንያቶችን ይመልከቱ →

www.ethiopianorthodox.org

፹፪-82 አመ ነሥኡኪ እምኤዶም አእላፈ ማኅሌት ጾታ (በበጾታ)
እንዘ ይጼልሉኪ ድንግል በአክናፈ መባርቅት ከመ ወልታ፣
ሰራዊተ ሰማይ ይቤሉ ለክብረ ፍልሰትኪ ግርማ ትእምርታ፣
መኑ ይእቲ ዛቲ ዘገዳመ ጽጌ (እምገዳመ ጽጌ) ዕርገታ፣
ከመ (ወከመ) ሠርፀ ጢስ ዘስሒን ይምዕዝ ዕጥነታ።

*ድንግል ሆይ ንጉሥ ሰሎሞን፣ እስራኤል ከተማረኩ (ከ70) ዘመን በኋላ ከባቢሎን በዝተው ይወጣሉ ለማለት በሰማይ እንዳለ ደመና በዝታ የምትወጣና መዓዛዋ እንደ ከርቤና እንደ ዕጣን የሆነ ይህቺ ማናት? ብሎ እንደተናገረ፣ መኃ.3.6. የሰማይ ሰራዊት፣ የሆኑ ብዙ መላእክት፣ በየነገዳቸው በብርሃን ክንፎች እንደ ጋሻ ጋርደው እያመሰገኑ ኤዶም ከምትባል ገነት በተቀበሉሽ ጊዜ የሚያስደንቅ የባለሟልነት ክብር ለተገለጸባት ለዕርገትሽ ደስ የሚል የበረሃ መዓዛ ያላትና (አበባ ካለበት በረሃ የምትወጣና) መዓዛዋ፣ ከነጭ ዕጣን መዓዛ ይልቅ ደስ የሚያሰኝ ይህች ማናት? አሉ።*

፹፫-83 እንዘ ይጸውረኪ በሐቂፍ ወይስዕመኪ በአፍ፣
አመ ወልድኪ አፍለስኪ (አመ አፍለሰኪ ወልድ) ውስተ የማኑ ለአሪፍ፣
ጽጌ-ተአምር (ጽጌ-ዕፀ ገነት) ማርያም ዘትጼንዊ ለአንፍ፣
እንዘ ይትጋደሉ አክናፈ በክንፍ፣
ለቀበላኪ ወረዱ አእላፍ።

*መዓዛ ረድኤትሽን ለሚሻ አፍንጫ ደስ የምታሰኚ የተአምር አበባ (የገነት ዛፍ አበባ) ማርያም ሆይ ልጅሽ በክንዱ አቅፎ በአፉ እየሳመ ከአንቺ የነሣውን ሥጋ በቀኙ ለማስቀመጥ በዐሳረገሽ ጊዜ፣ ስፍር ቍጥር የሌላቸው መላእክት ክንፍ ለክንፍ እየተማቱ አንቺን ለመቀበል ወረዱ። (ታሪኩ) አባቷ ዳዊት በመዝሙሩ ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች (በስጠሃት ክብር ጸንታ ትኖራለች) ብሎ የተናገረው ትንቢት መዝ.44.9 በዕርገቷ ጊዜ መፈጸሙን የሚያስረዳ ነው።*

(50) 1ኛ እባብ፣ ከመንገድ ዳር ሲተኛ ከጠላት ለመጠበቅ ራሱን ከመሬት ቀብሮ ነውና ማቴ.10.16 ንባቡና ትርጓሜው።



፹፬ 84 ትእምርተ ፍልሰትኪ እምድረ ጽጌ ኦ፡ ድንግል በከልኤ፣
በደመና ሰማይ አርአየ ዘሐዋርያት ጉባኤ፣
ወእለ ሞቱ እንሥአ (አንቅሐ) እምከርሠ መቃብር በቀርነ ጽዋዔ (ቀርነ ጽዋዔ)፣
ለነሰ እስከ ይብሉ ሶበ ሰማዕነ ውዋዔ፣
መሰለነ ዘበጽሐ ትንሣኤ።

*በሁለት ወገን (በነፍስና በሥጋ) ድንግል የሆንሽ ማርያም ሆይ አበባ ካለባት ምድር ወደ ሰማይ የማረግሽ ተአምር፣የሐዋርያት ጉባኤን በሰማይ ደመና አሳየ፣ ሐዋርያትም ለእኛስ የምስጋና ጩኸትን በሰማን ጊዜ ትንሣኤ ዘጉባኤ፣ ማለትም ሙታን በአንድነት ተነሥተው የሚሰበሰቡበት ጊዜ፣ ዮሐ.5.28-29. የደረሰ መሰለን እስኪሉ ድረስ፣ በመላእክት የምስጋና ድምጽ የሞቱትን ከመቃብር ውስጥ አስነሣ፣ ማቴ..24. 29-32፣. 1ኛ ተሰ .4. 16-18። እምድረ ጽጌ- የሚለውን ንባብ፣ትእምርተ ፍልሰትኪ እምድኅረ ጽጌ የሚሉ ሊቃውንትም አሉ፣ ይህም ጽጌ የሚባል ልጅሽ ከዐረገ ከ14 ዓመት በኋላ የሆነ ዕርገትሽ የሐዋርያት ጉባኤን በሰማይ ደመና አሳየ ለማለት ነው።*

## ተጋቢኦሙ በደመና ሰማይ (ሐዋርያት በሰማይ ተሰብስበው ምን አዩ?)

(ታሪክ) እመቤታችን ባረገችበት (በ49) ዓ.ም ሐዋርያት ዕርገቷን በአንድነት ባለማየታቸው ሲያዝኑ፣ ጌታ አይቶ በዓመቱ (በ50) ዓ.ም ከነሐሴ 1-14 ቀን፣(2) ሱባዔን ከፈጸሙ በኋላ በነሐሴ (16) ቀን ጌታ ሐዋርያትን፣ በአንድነት፣ ወደ ሰማይ ዐሳርጎና እመቤታችንን ካለችበት ዕፀ ሕይወት ስር አምጥቶ እርሷን መንበር አድርጎ፣ ቀድሶ አቍርቦአቸዋል። ሐዋርያትም ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች ተብሎ

(51) 2ኛ እባብ፣ በኖህ መርከብ ውስጥ እፉኝ ከፍቶ ሳለ፣ ርግብ ዋሻ መስሏት ከአፉ ገብታ ዕንቁላሏን ስትጥል፣ ኖህ ይጣላኛል ብሎ ሳይበላት ቀርቷልና ማቴ.10.16 ንባቡና ትርጓሜው።

www.ethiopianorthodox.org

ትንቢት እንደተነገረ መዝ.፵፩.፱-፲ ነፍሷ ከሥጋዋ ተዋሕዳ በራሱ በጌታ ቀኝ በክብር ተቀምጣ አይተው፣ ከሰማይ በአንድነት ወደ ደብረ ዘይት ተመልሰዋል። እመቤታችን፣ ያረገች (በ49) ዓ.ም ሲሆን፣ ሐዋርያት የነሐሴን ጾም (ጾመ ፍልሰታን) የጀመሩ በዚሁ (በ49) ዓ.ም ነሐሴ (1) ቀን ነው።

፹፭ 85 ሰዊተ ሥርናዩ (ትእምርቱ) ለታዴዎስ ወለበርተሎሜዎስ ወይኑ፣

*እንተ-ጸገይኪ አስካለ በዐለተ-ተከልኪ እደ-የማኑ*

*ማርያም ለጴጥሮስ ጽጌሁ ወለጳውሎስ ለበሱ፣*

*በኪ ምዉታን ሕያዋን ኮኑ፣*

*ወሐዋርያት መላእክተ በሰማይ ኮኑ።*

*የታዴዎስ የሥንዴው (የተአምሩ) እሸት፤ በቀኝ እጁ (በቅንነት) የተከለሽ የበርተሎሜዎስ ወይኑ፤ የጴጥሮስ ጥላውና የጳውሎስ ልብሱ የሆንሽ ማርያም ሆይ ሙታን በአንቺ ሕያዋን ሆኑ፣ ሐዋርያትም መላእክትን (የምድር መኳንንትን) በሰማይ ገዙ፣ ማቴ.18.18፣(1ኛ ቆሮ 6.3)።*

## እመቤታችን፣ የታዴዎስ የስንዴ እሸት እንዴት ተባለች?

(ታሪክ) የሐዋርያው ታዴዎስ ሀገረ ስብከቱ ሶርያ ነው፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ታዴዎስን ወደሀገረ ስብከቱ ለማድረስ አብሮ ሲሄድ በከተማ አካባቢ ሲደርሱ በእርሻ ሥራ የተሠማራ አንድ ሽማግሌ ሰው አግኝተው፣ የምንበላው ስጠን አሉት እሱም ከቤት ሄዶ ምግብ አስኪያመጣላቸው ድረስ፣ በሬዎችን ጠብቁ አላቸው ታዴዎስም ሥራ መፍታት አይገባም ብሎ በተጠመዱ በሬዎች ሲያርስ ቅዱስ ጴጥሮስ ዘርን ይዘራ ጀመር፣ ገበሬውም ምግባቸውን ይዞ ቢመለስ የተዘራው ዘር (ስንዴው) ወዲያው በቅሎ አፈራ፣ ይህን ታላቅ ተአምር ያየ ገበሬም አደነቀ። ጌታም አስቀድሞ

(52) 3ኛ. አባብ፣ውሃ ሲጠጣ መርዙ በሰውነቱ ተሰራጭቶ እንዳይገድለው፣ መርዙን ከየብስ ጥሎ ይጠጣልና ማቴ.10.16 ንባቡና ትርጓሜው።



በወንጌሉ እውነት እላችኋለሁ የስንዴ ቅንጣት (ፍሬ) በምድር ወድቃ ብትሞት (በምድር ላይ ብትዘራ) ፍሬ እንደምታፈራ፣ እኔም ሞቼ ብነሣ ነፍሳት ከሲኦል ወጥተው ገነት ይገባሉ ሲል ከድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ፣ በስንዴ ቅንጣት መስሎ ተናግሮ ነበር፣ ዮሐ. 12.24-27. ስለዚህ የጌታ ደቀ መዝሙር የሆነ ታዴዎስ፣ ይህንን ተአምር ሠርቷልና፣ እመቤታችንን የታዴዎስ የስንዴው እሸት አላት፣ የሐምሌ (2) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር።

## እመቤታችን፣ የበርተሎሜዎስ ወይን እንዴት ተባለች?

(ታሪክ) ሐዋርያው በርተሎሜዎስ እልዋህ ወደሚባል አገር ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር አብረው በሚሄዱ ጊዜ፣ በመንገድ አንድ ነጋዴ አግኝተው፣ ይህን አገልጋዩን (በርተሎሜዎስን) ልሸጠው ነበር ብሎ ቅዱስ ጴጥሮስ ነጋዴውን አማከረው። ነጋዴውም የበርተሎሜዎስ ሙያ ምን እንደሆነ፣ ጴጥሮስን ጠየቀው፣ ጴጥሮስም ወይን ጠባቂ ነው ብሎ፣ በርተሎሜዎስን ሸጠለት። ነጋዴውም በርተሎሜዎስን የወይን ጠባቂዎች አለቃ አድርጎ ሾመው፣ በቅንነት ወይን እየጠበቀና እየተንከባከበ (ለ40) ቀን ያህል ከቆየ በኋላ፣ የወይኑ ባለቤት ወይኑን ለመጎብኘት ሄዶ ሳለ፣ በእባብ ተነድፎ ሞተ። በኋላም በርተሎሜዎስ አስነሣው፣ ስለዚህ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከእመቤታችን በነሣው ሥጋ ተገልጿልና።እመቤታችንም ከእርሱ በረድኤት ሳትለይ በርተሎሜዎስ የወይኑ ባለቤት የሆነውንና ሞቶ የነበረውን ይህን ሰው አስነሥቷልና የበርተሎሜዎስ ወይን አላት። መናፍቃንም ጴጥሮስ በርተሎሜዎስን ሸጠው ማለት አይቻልም ለሚሉት ኑፋቄ፣ መልሱ የሚሆነን ቅዱስ ጳውሎስ፣ በክርስቶስ አምኖ ሳለ እንዳላመነ ሆኖ፣ ጤነኛ ሳለ በሽተኛ መስሎ፣

(53) በአጠቃላይ ጌታ፣ እንደ እባብ ብልህ ሁኑ ማለቱ፣ እባብ ያን ጊዜ ርግብን እንዳልተበቀላት ሁሉ እናንተም በቀለኞች አትሁኑ ማለቱ ነው ማቴ.10.16 ንባቡና ትርጓሜው።

www.ethiopianorthodox.org

(በሁሉም ነገር አሕዛብን መስሎ) በጥበብ አስተምሮ እንዳሳመናቸው ሁሉ፣ 1ኛ ቆሮ.9.19-24፣ ቅዱስ ጴጥሮስም በርተሎሜዎስን ለነጋዴው የሸጠውና ነጋዴው በርተሎሚዎስን የወይን ጠባቂዎች አለቃ አድርጎ የሾመበት ምክንያት፣ ወይን በተተከለ (በ3) ዓመት ያፈራል፣ ጌታም (3) ዓመት (ከ3) ወር ሲያስተምር ያለምሳሌ አላስተማረም ነበር ማቴ. 13.35 ። በዚህ መሠረት ጌታ እኔ የወይን ግንድ ነኝ፣ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ ብሎ ከድንግል ማርያም የነሣውን ደም በወይን መስሎ ተናግሮ ነበርና ነው ዮሐ. 15.1-5። ስለዚህ ቅዱስ በርተሎሜዎስ በሥራ ጌታውን ለመምሰልና አሕዛብን በጥበብ ለማስተማር በራሱ ፈቃድ በብር ተሸጧል፣ ጴጥሮስም በርተሎሜዎስን የሸጠበትን ገንዘብ በሥውር ለበርተሎሜዎስ መልሶለት፣ በርተሎሜዎስ ለነዳያን (ለኔቢ.ጤ) መጽውቶታል። በመጨረሻም አሕዛብ በርተሎሜዎስን አሸዋ በተሞላ ከረጢት ውስጥ ከነሕይወቱ ባሕር ጥለውት፣ መስከረም (1) ቀን ሰማዕትነትን ተቀበለ፣ (ገድለ ሐዋርያት ግእዝና አማርኛ አዘጋጅ ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም፣ 2ኛ እትም 1998 ዓ.ም)። ማርያም የጴጥሮስ ጥላው እንዴት ተባለች? ለሚሉት ኑፋቄም መልሱ፣ ጽላሎት (ጥላ) ማለት በፀሐይ (በብርሃን) ጊዜ የሚታይ የአንድ ነገር ግርዶሽ ማለት ሲሆን፣ ይህም በብርሃን ጊዜ ብቻ የሚታይና አካል ለአለው ነገር ሁሉ፣ የምሳሌነት መገለጫ ነው። ስለሆነም ቅዱስ ጳውሎስ፣ እስመ ጽላሎታ ይእቲ ለእንተ-ትመጽእ ሠናይት ‹‹ኦሪት ለወንጌል አምሳልና መርገፍ (የምሥጢር ጌጥ) ‹‹ሆና›› መቆየቷንና ዕብ. 10.1-5 ኀለፈት ሌሊት ወመጽአት መዓልት፣ ‹‹በጨለማ የተመሰለችው ኦሪት አልፋ፣9 በብርሃን የተመሰለችው ወንጌል ተሠራች ›› ብሎ እንደተናገረ፣ ሮሜ.13.12. እንዲሁም በሞት ጥላ ስር ይኖር የነበረ ሕዝብ ብርሃንን አየ የተባለው ትንቢት የተፈጸመና ኢሳ.9.2-3፤ ማቴ.4.15-17. እመቤታችን የዓለም ብርሃን

(54) ጌታ፣ እንደ ርግብ የዋህ ሁኑ ያለበት ምክንያት ምንድነው?



የሆነ ጌታን ዮሐ.1.4-9. በመውለዷ፣ ልጇም እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ከአላቸው ደቀ መዛሙርት አንዱ ከሆነው ከጴጥሮስ በረድኤት ሳትለይ ሕሙማን በቅዱስ ጴጥሮስ ጥላ ተፈውሰዋልና ነው፣ የሐዋ 5.15-17.። ጴጥሮስ ማለት ዓለት (ጠንካራ መሠረት) ማለት ሲሆን በመጨረሻ (በ64) ዓ.ም፣ ሁለቱን መልእክታት ጽፎ (ከ64) እስከ (67) ባለው ዓ.ም ሐምሌ (5) ቀን በሮም ከተማ ቍልቍል ተሰቅሎ በሰማዕትነት ዐረፈ። ተአምረ ኢየሱስ የተባለው መጽሐፍ ግን፣ በ60ዎቹ ዓ.ም ውስጥ ማረፉን ለማስረዳት (በ60) ዓ.ም ዐረፈ ይላል የሐምሌ (5) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር እና 174 ተአምረ ኢየሱስ። ማርያም የጳውሎስ ልብስ እንዴት ተባለች ለሚሉትም ኑፋቄ መልሱ፣ ጌታ፣ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ያመነ፣ የተጠመቀ ይድናል፣ ያላመነ፣ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል ብሎ ወንጌልን ባያስተምርና ማር.16.16-17. ጳውሎስ አምኖ ባይጠመቅ ኖሮ፣ የሐዋ. 9.18. ጌታ ከዳዊት ዘር በሥጋ ተወለደ ብሎ ባልሰበከ ሮሜ.1.2፣ በልብሱ ጨርቅም ሕሙማንን ባልፈወሰ ነበር። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ በልብሱ ጨርቅ ሕሙማንን በመፈወሱ የሐዋ.19.11-13. የዓለም መድኃኒት የሆነች እመቤታችንም የጳውሎስ ልብሱ ተባለች። ቅዱስ ጳውሎስም እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ሐምሌ (5) ቀን በዚሁ ዓ.ም በሮም ከተማ በሰይፍ ተቆርጦ ሰማዕትነትን ተቀበለ። የሐምሌ (5) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር፣

## ከሞት የተነሡ ወንድማማች፣

እመቤታችንን፣ የሞቱት በአንቺ ዳኑ ያሰኘው ቃል፣ ዓለም ከተፈጠረ ከ5,533 ዓ.ም ድረስ በሲኦል የነበሩ ነፍሳትን ጌታ ከእርሷ በነሣው ሥጋ ተሰቅሎ ስለአዳነ እና ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ወደ ሮሜ ከተማ ገብቶ የሚራሩ ብፁዓን ናቸው፣ ለእነርሱም ይራሩላቸዋልና የሚለውን የወንጌል ቃል ማቴ.5.7. ሲያስተምር የሰሙ ሰዎች፣ በዚያም ያሉ የድንጋይ ምስሶዎች አሜን ይሉ ነበር፣ እናታቸው አክሮስያ፣አባታቸው ቀውስጦስ የሚባሉና፣ የተመረዘ ውሃ ጠጥተው የሞቱ (2) ወንድማማች ልጆችም ነበሩ፣ እናታቸው አክሮስያና አባታቸው ቀውስጦስም የጴጥሮስን ፈጣሪ

(55) ርግብ [illegible] የዋህ (ቅን) ናት፣ ስለ የዋህነቷስ መጽሐፍ ምን ይላል?

www.ethiopianorthodox.org

(ከድንግል ተወልዶ ዓለምን ለማስተማር ሐዋርያትን የመረጠ ኢየሱስ ክርስቶስን) እንለምነው ተባብለው፣ ጸሎት በጀመሩ ጊዜ ቀውስጦስና አክሮስያ ሆይ የደቀ መዝሙሬ የጴጥሮስን ቃል ስለሰማችሁና ስለተቀበላችሁ ልጆቻችሁን በሕይወት እሰጣችኋለሁ የሚል ቃልን ከሰማይ ሲሰሙ፣ ወዲያው ልጆቻቸው ስለተነሡ ነው። የሐዋርያት ሞገሳቸው የሆነች እመቤታችንም፣ ከእነርሱ በረድኤት አትለይምና ሞተው የነበሩ በአንቺ ዳኑ አለ። እነዚህ ከሞት የተነሡ ልጆችም ለቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዛሙርት ሆኑ፣ ከሁለቱም አንዱ ቀሌምንጦስ ሲሆን፣ ፊልጵ.4.3-4፣ ቀሌምንጦስ ከቅዱስ ጴጥሮስ ተምሮ፣ የተጠመቀና አሕዛብ በሐዋርያት ላይ ያደረሱትን መከራ ገድል ጽፎ፣ ከሐዋርያትም (81) የብሉያትንና የሐዲሳትን መጻሕፍት ተረክቦ፣ የሮም ኤጲስቆጶስ ሆኖ (10) ዓመት ከአገለገለ በኋላ ጠራብሎስ በሚባል ከሐዲ ንጉሥ አማካኝነት ታላቅ ብረት በአንገቱ ታስሮ በጥቁር ባሕር የተጣለና ኅዳር (29) ቀን (በ110) ዓ.ም ገደማ በሰማዕትነት ያረፈ የመጻሕፍት ሊቅ ነው። (የኅዳር 29 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)

## የሥልጣነ ክህነት ኃይል፣

(ታሪክ) ሐዋርያት፣ መላእክትን በሰማይ ገዙ ለሚለው ገጸ ንባብ (ኃይለ ቃል፣ ለዮሐንስ አፈወርቅ (2) ወዳጆች ነበሩት፣ እነሱም ንጉሡ አርቃድዮስና ንግሥቲቱ አውዶክስያ ናቸው ልጅ እየወለዱ ይሞትባቸው ነበር በምን ምክንያት ልጅ ይሞትብናል ብለው ራሳቸውንና መሰሎቻቸውን ጠየቁ። ያማከሯቸው ሰዎችም ልጆቻችሁን ደግ ሰው ክርስትና ባያነሣላችሁ ይሆናል የሚሞቱ አሏቸው፣ ከዚህ የተነሣም ከዮሐንስ አፈወርቅ የበለጠ ደግ ሰው አለን? ብለው፣ ሴት ልጅ በወለዱ ጊዜ መጥተህ አጥምቅልን ብለው ላኩበት። ዮሐንስ አፈወርቅም መልእክታቸውን ተቀብሎ ሲሄድ፣ መልአከ ሞትን በመንገድ አገኘው ወዴት ትሄዳለህ አለው፣ አሁን አንተ የምትሄድላትን ሕፃን ነፍሷን ከሥጋዋ ልለይ እሄዳለሁ አለው፣ ዮሐንስም ገና አልተጠመቀችምና፤ ቆየኝ ላጥምቃት ብሎት ሕፃኗን አጥምቆ በሌላ መንገድ ተመለሰ።

(56) እንደ ርግብ የዋህ ሆና የተፈጠረች ሔዋንን፣ ዲያብሎስ አሳታት 3ኛ.መጽ.መቃ.2.17-19።



የካህናት መዓርጋቸው (ሥልጣነ ክህነታቸው) ደግ እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ መልአከ ሞት ወደላይና ወደታች ሳይል (10) ዓመት ከዚያው ካለበት ቦታ ቆሞ ኖረ። ሕፃኗም (10) ዓመት ሲሆናት ለባል ታጨች ልጃችን ሀብትን አግኝታለችና (ባል ልታገባ ነውና) መጥተህ መርቃት ብለው ላኩበት፣ እሱም እሺ ብሎ በዚያ መንገድ ሲሄድ መልአከ ሞትን ቆሞ አገኘው፣ ምነው ከዚህ ቆመሃል? አለው አንተ ቆይ ካልከኝ ጀምሮ ወዲያና ወዲህ ብዬ አላውቅም አለው፣ ዮሐንስም አጥፍቻለሁ ሂድ የታዘዝከውን አድርግ አለውና ቢሄድ በአንድ ጊዜ ነፍሷን ከሥጋዋ ለይቶ ሞታ ሲያለቅሱ አገኛቸው፣ ተውት ነገሩ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነው ብሎ ታሪኩን አስረድቶ አጽናንቷቸዋል። ጌታም በምድር የምታስሩት በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድር የምትፈቱትም በሰማይ የተፈታ ይሆናል፣ የሚል ሥልጣነ ክህነትን ለሐዋርያት በመስጠቱና ሐዋርያት፣ በዕለተ ምጽአት ጊዜ በ12ቱ ነገደ እስራኤል ላይ ስለሚፈርዱ፣ ሐዋርያት መላእክትን ገዙ አለ፣ ማቴ.18.18 እና ዮሐ.19.21-24።

፹፮86 ጽጌኪ ማርያም ኮነኒ ሲሳየ ወአራዘ፣
ወጸገወኒ እምትካዝ ተአምረኪ መናዝዘ፣
ቶማስ ሎቱ አመ ገቦሁ አኀዘ፣
እንዘ ይብል ከርቤ እምእዴየ ውሕዘ፣
ረከበ (ረኪቦ) በውስተ ቍስሉ (ውስተ ቍስሉ) አፈወ ምዑዘ።

*ማርያም ሆይ ልጅሽ ምግብንና ልብስን ሆነኝ፣ ከጭንቅ የሚያረጋጋ ተአምርሽንም ሰጠኝ፣ ንጉሥ ሰሎሞን ስለ ጌታ መዓዛ ትምህርት እጆቼ ከርቤን አፈሰሱ (ሽቱ፡ ሽቱ ይሸታሉ) ብሎ እንደተናገረ* መኃ.5.5-6. ቶማስ የጌታን ጎን በዳሰሰ ጊዜ በቍስሉ ውስጥ ልዩ መዓዛን አግኝቶ ከርቤ (ሽቱ) ከእጄ ፈሰሰ አለ። ከርቤ፣ ማለትም የሽቱ ዕንጨት ስም ሲሆን፣ ከርቤ የተሰበረውን ይጠግናል (የተለያየውን አንድ ያደርጋል። ስለዚህ ቶማስ ከርቤ (ሽቱ) ከእጄ ፈሰሰ ማለቱ፣ የጌታን ትንሣኤ ተጠራጥሮ ጎኑን ሲዳስስ እጁ እሳት እንደገባ ፈትል ተኮማተረ። ጌታዬ፣ አምላኬ ብሎ ሲያምን ግን እጁ ድኖለታልና ነው። ከዚህ የተነሣም ጌታ

(57) እመቤታችን፣ በርግብ መመሰሏ ከፍጥረት ሁሉ ቅድስት (የተለየች) ርኅርኅት ስለሆነች ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ሳያዩኝ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለ ዮሐ. 20.21-30 ንባቡና ትርጓሜው። በመጨረሻም አሕዛብ የቶማስን ቆዳ ገፈው፣ ስልቻም አውጥተውና፣ በሰውነቱ ላይ ጨው ጨምረው ግንቦት (26) ቀን ሰማዕትነትን ተቀበለ። (የሚያዝያ 6 ቀን እና የግንቦት 26 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)

፹፯-87 ክበበ-ጌራ-ወርቅ ጽሩይ እምዕንቌ ባሕርይ ዘየኀቱ፣
ዘተጽሕፈ ብኪ ትእምርተ ስሙ ወተዝካረ ሞቱ፣
አክሊለ ጽጌ ማርያም ለጊዮርጊስ ቀጸላ መንግሥቱ፣
አንቲ ኵሎ ታሰግዲ ሎቱ፣
ወለኪኒ ይሰግድ ውእቱ።

የጊዮርጊስ የስሙ (የሰማዕትነቱ) ምልክትና የሞቱ መታሰቢያ የተጻፈብሽ፤ ባሕርይ ከሚባል፣ ከሚያበራ ዕንቍ ይልቅ፣ የጠራ የክብር ጌጥ የሆንሽለትና በክብር የነገሡብሽ የክብር አክሊል ማርያም ሆይ አንቺ ለጊዮርጊስ ሁሉን ታሰግጂለታለሽ፣ እሱ ግን፣ ለአንቺ ይሰግዳል። (ታሪክ) የቅዱስ ጊዮርጊስ መጽሐፈ ገድል እንደተናገረው ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአባቱ ከዘሮንቶስና ከእናቱ ከቴዎብስታ (በ277) ዓ.ም በፍልስጥኤም ውስጥ በምትገኝና ልዳ በምትባል አገር ጥር (2) ቀን ተወለደ፣ ጊዮርጊስም ፈረስ መጋለብንና ቀስት መወርወርን፤ አውሬ ማደንንም ዐወቀ፣ በተወለደ (በ20) ዓመቱም በጋብቻ እንዲወሰን ሴትን አጨሱለት፣ ጊዮርጊስ ግን የምድር ሙሽራነትን ንቆ መጽሐፍ፣ የበጉ ሰርግ (ጌታ ለቅዱሳን የሚሰጠው የጽድቅ ክብር ስለደረሰ ደስ ይበለን ብሎ እንደተናገረ) በሰማይ የጌታ ሙሽራ ለመሆን መረጠ ራእ.19.7-9. ጣዖትን የሚያመልኩ ጋለስና ጋሪስ የሚባሉ የሮም ነገሥታትንም አሸንፎ ሥልጣን የያዘው ንጉሥ ዱድያኖስ፣ ክርስቲያኖችን ሁሉ የሚያሠቃይበትና የሚያሳድድበት ጊዜ ነበርና፣

(58) ቀደም ሲል የርግብ የዋህነት እንደተገለጸው፣ ከአባቡ አፍ ገብታ ዕንቁላሏን ብትጥልም፣በየዋህነቷ እግዚአብሔር ጠብቋታል ማቴ.10.16 ንባቡና ትርጓሜው።



ሰዎችን ሁሉ ለጣዖት ሲያሰግዳቸው፣ ጊዮርጊስ አይቶ ገንዘቡን ሁሉ ለድሆች መጽውቶ በ20 ዓመቱ ተጋድሎውን ጀመረ። ዱድያኖስም ጊዮርጊስን በተለያዩ ሥቃዮች ማሠቃየቱን ጀመረ፣ ጌታ ግን ጊዮርጊስ (3) ጊዜ እንደሚሞትና (3) ጊዜ እንደሚያስነሣው፣ በ4ኛ ውም የምስክርነትን አክሊል እንደሚቀበል ነግሮት (3) ጊዜ ሞቶ ተነሥቷል። በ4ኛው ግን (በ304) ዓ.ም በተወለደ (በ27) ዓመቱ፣ ጌታ ባረፈባት ዓርብ ቀን (በ9) ሰዓት ሚያዝያ (23) ቀን በክብር ዐርፎ የክብር አክሊልን ተቀዳጅቷል።ይህ ታሪኩ ሲሆን፣ ሐተታውንና ምሥጢሩን ደግሞ ይመልከቱ።

## እመቤታችን፣ የጊዮርጊስ ምልክትና የሞቱ መታሰቢያ ለምን ተባለች?

(ሐተታ) ዘተጽሕፈ ብኪ ትእምርተ ስሙ፤ ወተዝካረ ሞቱ፤ ‹‹እመቤታችንን፣ የጊዮርጊስ የስሙ (የሰማዕትነቱ) ምልክት እና የሞቱ መታሰቢያ›› የተጻፈብሽ ለምን ተባለች ቢሉ? ታሪኩን ከላይ እንደተመለከትነው ጊዮርጊስ፣ (3) ጊዜ ሞቶ፣ (3) ጊዜ ተነሥቶ በ4ኛ ው ዐርፎአልና። ይህም ማለት ማርያም የሚለው (4) ፊደል የጊዮርጊስ (4) ጊዜ የመሞቱ ምሥጢር ምሳሌ ነውና። አንቲ ኵሎ ታሰግዲ ሎቱ፣"እመቤታችንን አንቺ ለጊዮርጊስ ሁሉን ታሰግጂለታለሽ" ማለቱም፣ መኳንንቱና መሳፍንቱ ሁሉ ይሰግዱላት የነበረች የንጉሡ የዱድያኖስ ሚስት ንግሥት እለእስክንድርያ፣ በቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት አምና፣ ለቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የጸጋ (የአክብሮት) ስግደትን፤ ለፈጣሪ የአምልኮ ስግደትን ሰግዳ በንጉሡ (በባለቤቷ በዱድያኖስ) ትእዛዝ ሚያዝያ (15) ቀን አንገቷን በሰይፍ እንድትቆረጥ በመደረጉና በሰማዕትነት ዐርፋ የክብርን አክሊል በመቀዳጀቷ ሲሆን፣ ቅዱስ ጊዮርጊስም፣ በአንድ ጊዜ ሠላሳ ሺህ

(59) በብሉይ ኪዳን፣ ገብርኤል የሚል (2) ይገኛል።

www.ethiopianorthodox.org

አሕዛብን አሳምኗል። አጽሎን በሚባለው ጣዖት ላይ ያደረ ርኩስ መንፈስንም፣ በቅዱስ ጊዮርጊስ ጸሎት ከጣዖቱ ወጥቶ ምድር ተከፍታ ውጠዋለች።

፹፰-88 ጽጌ ረዳሁ ለእስጢፋኖስ እምሥነ ጽጌያት ዘትጸድሊ፣
ተአምረ ፈውስ አንቲ ማርያም ዕብነ ናብሊስ ተጸንጸሊ፣
ወእለ ምስሌሁ ሰማዕታት ማኅበራነ ፊቅጦር ወአቦሊ፣
ለጽንጻሌ ፍቅርኪ እሙ በሰሚዐ ቃሉ መጥለሊ፣
ኢያእመርዎ ለሕማም ቀታሊ።

*ከአበባዎች መልክ ይልቅ የምታበሪ የእስጢፋኖስ ጽጌረዳው እና የጌታ እናቱ የሆንሺ ማርያም ሆይ የሚያቃጭልና የመድኃኒትነት ድምጽ ያለው ናብሊስ የሚባል ድንጋይ አንቺ ነሽ፣ ከእርሱ (ከእስጢፋኖስ) ጋር የነበሩ ብዙ (985) የፊቅጦርና የአቦሊ ማኅበር የሆኑ ሰማዕታት፣ የሚያለመልም የፍቅርሽ ጸናጽል ድምጽን በመስማት ገዳይ የሆነ ሕማምን አላወቁትም።*

## ሁለት እስጢፋኖሶች የመጀመሪያ ሰማዕታት እንዴት ተባሉ?

(ታሪክ) "የ" ዓ.ም አቈጣጠርን የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ እንደገለጸው በ296 ዓ.ም ገደማ የአንጾኪያ የመጀመሪያ ሰማዕት የሆነው ይህ እስጢፋኖስ፣ ንጉሡ ዲዮቅልጥያኖስ ቤተ ክርስቲያን እንድትዘጋና የጣዖት ቤት እንዲስፋፋ ሕዝቡን ሰብስቦ የአዋጁን ደብዳቤ በጉባኤ ሲያስነብብ፣ ሰምቶ ስለ ሃይማኖት ልቡ በክርስቶስ ፍቅር እሳት ነደደና፣ ያችን ደብዳቤ ከአንባቢው ወታደር ነጥቆ ቀደዳት፣ በዚህ ምክንያትም ዲዮቅልጥያኖስ ሰይፉን መዝዞ እስጢፋኖስን መትቶ ለሁለት ከፈለው፣ የቅዱስ እስጢፋኖስ ራስም ወደ ፊት የንጉሡ ዓይኖች እንደሚጠፉና ፍጹም ደሀ ሆኖ ምጽዋትን እንደሚለምን እየጮኸች ትዘልፈው ነበር፣ በኋላም ንጉሡ የእስጢፋኖስን ራስ እንዲቀብሯት አዝዞ ቀበሯት፣ እንደገና (ለ3) ቀን

(60) ከዕዝራ ሱቱኤል እስከ መጽሐፈ ሄኖክ (በ81 መጽሐፍ፡ ቅዱስ ከገጽ 723 እስከ 853) በአሉት ብሉያት መጻሕፍት፣ ገብርኤል የሚል (10) ይገኛል።



ያህል ንጉሡን ስትዘልፍ በብረት ሳጥን ውስጥ ጨምረው ከባሕር እንዲጥሏት አደረገ፣ ከጌታ የታዘዘ መልአክም ከባሕር ውስጥ ሳጥኑን አውጥቶ ከባሕሩ ዳር አኖረው፣ የቅዱስ እስጢፋኖስ እናትም መጥታ ሣጥኑን ወደ ቤቷ ወስዳ የመከራው ዘመን እስኪያልፍ ድረስ በሥውር ቦታ፣ አኑራ መብራትን ታበራለት ነበር፣ የመከራው ዘመን ሲያልፍ ግን፣ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶለት ብዙ ተአምር ተደርጓል። ይህ እስጢፋኖስም፣ የኢየሩሳሌም የመጀመሪያው ሰማዕት ከሆነው ከሊቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስ በኋላ፣ የአንጾኪያ የመጀመሪያ ሰማዕት ተብሏል፣ የጥቅምት (9) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር።

## ሰውንና ወፍን ስለሚያስወልድ ቷአምረኛው ድንጋይ፣

(ታሪክ) ድምጹ እንደ ብረት የሚጮህ፤ እንደ መስታወት ሰተት ያለና እንደ ዕንቍ የሚያበራ ናብሊስ የሚባል ድንጋይ አለ፣ መልኩ ዕብነ በረድን ይመስላል፣ የታመመ ሰው ጭንቅ ሲበዛበት ይህን ድንጋይ በጆሮው አጠገብ የመቱለት እንደ ሆነ ቶሎ ያለ ጭንቅ ያርፋል፣ ሴትም ምጥ በፀናባት ጊዜ እሱን ስትነካ በፍጥነት ትወልዳለች፣ ወፍም እንደዚሁ ምጥ ሲፀናባት በእግሯ ስትቆምበት ፣ፈጥና ትወልዳለች፣ ስለዚህ ናብሊስ የተባለ ይህ ድንጋይ፣ መድኃኒትነት ያለው የምሕረት ድንጋይ ነው። እመቤታችንም፣ ለነፍስና ለሥጋ፣ መድኃኒት ናትና፣ የምሕረት ድንጋይ (የምሕረት ማዕድን) አንቺ ነሺ አለ፣ መጽሐፈ ትልቄ አዕባን፣ (የከበሩ የድንጋዮችን፣ የዕንቍዎችን (የማዕድናትን) አይነት የሚገልጽ የእጅ ጽሑፍ (ያልታተመ)።

## ስለ ሰማዕቱ ፊቅጦር፣

(ታሪክ) "የ" ዓ.ም አቈጣጠር፣ ቀደም ሲል በገጽ 64 ላይ እንደተገለጸው ሰማዕቱ ቅዱስ ፊቅጦር፣ እንደ አንጾኪያዊው እስጢፋኖስ በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት በ296 ዓ.ም ገደማ የተነሣ (የተጋደለ) ሰማዕት ነው፣

(61) በሐዲስ ኪዳን፣ ገብርኤል የሚል (2) ይገኛል።

www.ethiopianorthodox.org

አባቱ ኅርማኖስ፣ እናቱ ማርታ ይባላሉ በተወለደ (በ20) ዓመቱ በዲዮቅልጥያኖስ ቤተ መንግሥት (የ3ተኛ) የሹመት ደረጃ የነበረው ነው፣ ሥጋን አይበላም ወይንንም አይጠጣም ነበር፣ ንጉሡ የሚያመልከውን ጣዖት አላመልክም ብሎ እንደ ወርቅ በእሳት የተፈተነ ሰማዕት ነው ላሜዳዎችን (የአውድማ እህል መገልገያዎችን) እየሸጠ ራሱንና ነዳያንን ይረዳ ነበር፣ ዘቅዝቀው ሲሰቅሉትም ታይ የነበረች አንዲት (የ15) ዓመት ብላቴና መላእክት በፊቅጦር ራስ ላይ አክሊልን ሲያስቀምጡ አይታ ለአሕዛብ ነገረቻቸው፣ ብዙዎችም አምነው ሚያዝያ (27) ቀን በሰማዕትነት ዐርፈዋል:: የሚያዝያ 27 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር::

## በተገፈፈ ቆዳው ሙት ስላስነሣው ሰማዕት፣

(ታሪክ) ሰማዕቱ ቅዱስ አቦሊ፣ አባቱ ዮስጦስ እናቱ ታውክልያ ይባላሉ፣ ከነገሥታትም ወገን ነበር፣ ዓላውያንን ወግቶ ሲመለስ ዲዮቅልጥያኖስ ፈጣሪን ክዶ ቢያገኘው ከሌሎች የመንግሥት ልጆች ጋር የዲዮቅልጥያኖስን ሥልጣን ለመቀማት አሰበው፣ ከዚህ ከሚያልፈው ዓለምስ አዲሲቱንና የማታልፈው ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ራእ. 21.1-3. መውረስ ይሻላል ብለው፣ በሰማዕትነት ለመጋደል ወሰኑ:: አቦሊም እንደ ሐዋርያው ቶማስ ቆዳው እስኪገፈፍ ድረስ ተጋድሏል፣ የአንድ ባለጸጋ ቤት ሲሠራም የቤቱ ግድግዳ ፈርሶ የባለጸጋው (2) ልጆችና በቤቱ ሥራ ላይ የተሰማሩ (16) ሰዎች ሞቱ፣ አቦሊም የተገፈፈ ቆዳውን ወስዶ በሞቱ ሰዎች ላይ ዘርግቶ፣ በሕያው በእግዚአብሔር ስም ተነሡ ቢላቸው (18ቱ) ሰዎችም ሁሉ ተነሥተዋል፣ ጌታም አቦሊን የገድልህን መጽሐፍ የሚጽፈውንና የሚያነብበውን፣ የሚሰማውንም ሁሉ ስሙን በኪሩቤል ክንፍ ላይ እጽፈዋለሁ ብሎ ቃል ኪዳን የሰጠውና ነሐሴ (1) ቀን ያረፈ ሰማዕት ነው:: የነሐሴ (1) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር::

(62) በአጠቃላይ (በ81) መጽሐፍ ቅዱስ ገብርኤል የሚል (14) ይገኛል::



፹፱-89 ተአምረ ፍቅርኪ ማርያም ይገብር መንክረ፣
እንዘ ፃዕረ ሞት ያረስዕ ወያስተጥዕም መሪረ፣
በመዓዛ ጽጌኪስ (ሰመዓዛ ጽጌኪስ) ለዘበዓውደ ስምዕ ሰከረ፣
ውግረተ እዕባን ይመስሎ ኀሠረ፣
እሳትኒ ማየ ባሕር ቆሪረ::

*ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ተአምር የሞት ጣርን አስረስቶ፣ መራራውንም አጣፍጦ ድንቅ ተአምርን ያደርጋል፣ በልጅሽ መዓዛ (ከልጅሽ መዓዛ የተነሣ) በሰማዕትነት አደባባይ ለተመሰጠ ሰው፣ በድንጋይ መወገር ገለባን፣ እሳትም የቀዘቀዘ የባሕር ውሃን ይመስለዋል::* ሰማዕቱ እስጢፋኖስ፣ (ከ7ቱ) አገልጋይ ዲያቆናት አንዱ ሆኖ፣ ጥቅምት (17) ቀን የተሾመና ከጌታ ዕርገት በኋላ (2) ዓመት ክርስትናን አስተምሮ በተወለደባት ጥር (1) ቀን (በ35) ዓ.ም በወጣትነት እድሜው ከጌታ ቀጥሎ፣ከሐዋርያት ቀድሞ ሰማዕትነትን የተቀበለና በኢየሩሳሌም የክርስቶስ የመጀመሪያው ሰማዕት ነው፣ የሐዋ.7.54-60. እስጢፋኖስ ማለት፣ በግሪክ ቋንቋ አክሊል ማለት ነው አባቱ ስምዖን፤ እናቱ ሐና ይባላሉ (ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን 1988 ዓ.ም እና የቅዱሳን ታሪክ በሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ 1988 ዓ.ም::

፺-90 አንብርኒ ማርያም ውስተ ልብኪ ከመ ኀልቀት፣
ወከመ ማዕተብ ዘትእምርት (ወከመ ማዕተብ ፀርኒ) በመዝራዕትኪ ልዕልት፣
በእንተ ርስሐትየሰ ኢትመንንኒ ንግሥት፣
እስመ ወሀብኩ ንብረትየ ለፍቅርኪ ሞት፣
ዘአሠርገዎሙ ለሰማዕት በጽጌሁ ሕይወት::

*የሰማይ ንግሥት የሆንሽ ማርያም ሆይ መዝ.44.9. ቀለበትን በጣት፣ አይከልን (መስቀልን) በደረት እንዲይዙ ምልክት እንዳለው ቀለበት (እንደ መስቀል) በልቡናሽ ጻፊኝ፣ ስለ ኃጢአቴም አትናቂኝ፣ ሰማዕታትን በሕይወት አበባው (ደስ በሚያሰኛቸው ሕይወት) ለአስጌጣቸው ለፍቅርሽ፣ እስከ ሞት ድረስ ሕይወቴን ሰጥቻለሁና::*

(63) በብሉይ ኪዳን፣ ሚካኤል የሚል (3) ይገኛል::

www.ethiopianorthodox.org

፺፩-91 ተአምረ ፍቅርኪ ማርያም በማኅበረ ጻድቃን ተወደሰ፣
ወፈድፋደሰ በላዕለ ኃጥአን ነግሠ፣
እስመ እንሥአ (አሕየወ) ሙታነ ወሕሙማነ ፈወሰ፣
ቦ፡ ዘይቤ አጽገየ ዘየብሰ፣
ወቦ፡ ዘይቤ አድባረ አፍለሰ፡

ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ተአምር በብዙ ጻድቃን ዘንድ ተመሰገነ፣ ይልቁንም በኃጥአን ላይ ከፍ ከፍ አለ፣ ሙታንን አስነሥቷልና ሕሙማንንም ፈውሷልና፣የደረቀውን አለመለመ (አሳበበ) ያለ፡ አለ፣ (ነበረ)፣ ተራራንም አፈለሰ ያለ፡ አለ (ነበረ):: (ሐተታ) ተአምርሽ በኃጥአን ላይ ከፍ ከፍ አለ ማለቱ፣ ጻድቃን በመልካም ሥራቸው ዋጋ ያገኛሉ፣ ኃጥአን ግን በጎ ሥራ ስለሌላቸው ለእመቤታችን በተሰጣት ቃል ኪዳን በመማፀንና በስሟ በጎ ነገር በማድረግ፣ የመዳን ተስፋ ስላላቸው ነው:: ቦ፡ ዘይቤ አጽገየ ዘየብሰ ‹‹የደረቀውን አለመለመ ያለ፣ (ነበረ)›› የሚለው ምሥጢርም የቅዱስ ጊዮርጊስ መጽሐፈ ገድል እና የኅዳር 7 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር እንደተናገረው ቅዱስ ጊዮርጊስ በጸሎቱ (70) ነገሥታት የተቀመጡበትን ወንበርንና የመበለቷን (የደሃዋን) የደረቀ የቤት ምሰሶን ያለመለመውን ተረክ ያስረዳል::

## በሃይማኖት ተራራን ስለማፍለስ፣

(ታሪክ) ወቦ፡ ዘይቤ አድባረ አፍለሰ፣ (ተራራን አፈለሰ) ስለሚለው ኃይለ ቃል ደግሞ በሊቀ ጳጳሱ በአባ አብርሃም ዘመን በግብጽ አገር የነገሠ ስሙ ለማዝ የሚባል የአሕዛብ ንጉሥ፣ አባ አብርሃምን በወንጌላችሁ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል ሃይማኖት ቢኖራችሁ፣ ይህን ተራራ ተነሥተህ ሂድና ወደ ባሕር ግባ ብትሉት ይደረግላችኋል ይላል:: ይህ እንዴት ይሆናል? ብሎ ቢጠይቀው፣ አባ አብርሃምም ቃሉ ትክክል ነው አለው፣ ማቴ. 17.20-21፣ ንጉሡም ይህ ከሆነስ

(64) ከዕዝራ ሱቱኤል እስከ መጽሐፈ ሄኖክ (በ81 መጽሐፍ ቅዱስ ከገጽ 723 እስከ 853) በአሉት ብሉያት መጻሕፍት፣ ሚካኤል የሚል (30) ይገኛል::



ምልክትን አሳዩኝ አለ፣ አባ አብርሃምም ንጉሡን (3) ቀን እንዲሰጠው ለመነውና (3) ቀን ሰጠው አባ አብርሃምም መነኰሳቱንና ኤጲስቆጶሳቱን ሰብስቦ (3) ቀንና (3) ሌሊት እንዲጸልዩ ነግሯቸው ሲጸልዩ፣ በ3ተኛው ቀን ከእመቤታችን ሥዕል ተማፀነ:: እመቤታችንም፣ አንዲት ሴት መጥታ በዝሙት ልታሰናክለው በቀረበች ጊዜ፣ ቀኝ ዐይንህ ብታሰናክልህ፣ (የስህተት ምክንያት ብትሆንብህ)፣ ከአንተ አውጥተህ ጣላት ሁለት ዐይን ኖሮህ በገሃነም ከምትጣል ከአካላትህ አንዱ አካል ቢጠፋ ይሻልሃል የሚለውን የወንጌል ቃል ለመፈጸም፣ ማቴ.5.28-31. አንድ ዐይኑን በጫማ መስፊያው አውጥቶ የሰጠ፣ ውሃም በመቅዳት ደካሞችን የሚረዳ፣ ጫማ ሰፊው ስምዖንን ጠይቀው አለችው:: አባ አብርሃምም እመቤታችን እንደነገረችው አደረገ፣ ስምዖንም ለአባ አብርሃም አንተ እኔን፣ ሕዝቡ አንተን እያዩ ኪርያላይሶን (አቤቱ ጌታ ሆይ ይቅር በለን) እያላችሁ (40) ጊዜ ጸልዩ አለው፣ አባ አብርሃምም ስምዖን እንደነገረው አድርጎ ንጉሡና ሕዝቡ በተሰበሰቡበት አደባባይ (3) ጊዜ ሰግደው ተራራውን በመስቀል ምልክት ቢባርከው፣ ተራራው በሰው ሁሉ ፊት ተነሥቶ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ፣ ሊቀጳጳሱና ምእመናኑም ሲሰግዱ "ያ" ተራራ (3) ጊዜ ወደ ቦታው ተመለሰ ሕዝቡና ንጉሡም ይህን ተአምር አይተው እጅግ አድንቀው አመኑ:: (የታኅሣሥ 6 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር እና 150 ተአምረ ማርያም::)

፺፪-92 ሃይማኖትየ ማርያም ዘአጥረይኩኪ እምኬፋ፣
አፍለስኪ ደብረ ወሣረርኪ ለኢያሪኮ በጽንፋ፣
እንዘ ያቴክዘኒ ሊተ ዘጌጋይየ ዘለፋ፣
ለእምየ መርዓተ ጽጌ ተአምርኪ መጽሐፋ፣
ያብሥረኒ ሊተ ኑዛዜ ወተስፋ::

(65) [illegible] የሚል (2) ይገኛል::

www.ethiopianorthodox.org

*ከጴጥሮስ የተማርኩሽ ሃይማኖቴ ማርያም ሆይ ተራራን ነቅለሽ በኢያሪኮ ዳርቻ ላይ ተከልሽ፣ (ሠራሽ)፣ በበደሌ የሚመጣብኝ ዘለፋ እኔን ባሳዘነኝ ጊዜ፣ ደስ የሚያሰኝ የአንቺ የእናቴ ተአምርሽ፣ መጽናናትንና ተስፋን ያበሥረኝ::* (ሐተታ) እመቤታችንን ከጴጥሮስ የተማርኩሽ ሃይማኖቴ ማለቱ፣ ጌታ የሰውን ልጅ ማን ይሉታል ብሎ ደቀ መዛሙርቱን በጠየቀ ጊዜ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ ሲል፣ *ከሥጋዋ ሥጋን*፣ ከነፍሷ ነፍስን የነሣ ጌታም ጴጥሮስን ብፁዕ (የተመሰገንህ) ነህ፣ በዚህች ዓለት ላይም ሃይማኖት የምትፀናባት ቤተ-ክርስቲያኔን እሠራለሁ ያለውን መናገር ነው፣ ማቴ.16÷15-21. ሃይማኖት፣ አንዲት ብቻ ስትሆን ይህችም ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ መሆኑን አምኖ በአብ፤ በወልድ፤ በመንፈስ ቅዱስ (በአንድ አምላክ) ስም መጠመቅ ናት ማቴ.28.18፣ ኤፌ.4-5::

## እመቤታችን፣ በኢያሪኮ ስላደረገችው ተአምር፣

(ታሪክ) በጽርዕ አገር (ልዩ ስሟ ዕቆና በምትባል ሰፈር) ባለና ርቀቱ ከኢያሪኮ ግማሽ ኪሎ ሜትር በሚሆነው በአንድ ተራራ፣ በእመቤታችን ስም የተሠራች ቤተ ክርስቲያን ነበረች:: እመቤታችንም ለአንድ ቄስ በኢያሪኮ ዳርቻ ሌላ ተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን ሥራልኝ ብላ በሕልሙ በተደጋጋሚ ነገረችው ካህኑም ይህን ነገር ለሕዝቡ ነገራቸው፣ ሕዝቡም ለብዙ ዓመታት የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥራ ችላ በማለታቸው እና የመነኰሳቱ ቤት ከነአጥሩ ነሐሴ (23) ቀን ፈልሶ፣ *ምንም* ጉዳት ሳይደርስበት ኢያሪኮ ወደ ምትባል አገር ዳርቻ በእመቤታችን ተአምር እንደሄደ ተነገረ፣ (234 ተአምረ ማርያም)::

(66) በአጠቃላይ (በ81) መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሚካኤል የሚል (35) ይገኛል::



ኟ፫-93 ተአምረ ፍቅርኪ ማርያም ውስተ አጽናፈ ምድር ያደ፣
እንዘ ሞገደ ባሕር ያዝኅን ወያጠፍዕ ነደ፣
በፍርሀተ ሢመት ዘምሥጢር (ስምፍርሀት ሢመት ዘክህነት)
ተመሲያሙ ረዓደ፣
ካህናት ክልኤቱ ድኅረ መተሩ ገሀደ፣
ጸገዩ እምኒኪ ልሳነ ወእደ::

*ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ተአምር በምድር ዳርቻ ሁሉ የባሕር ጎርፍን ጸጥ እያደረገና እሳትን እያጠፋ ተገለጸ፣ (ታወቀ) ምሥጢር ያለበት ሹመትን በመፍራት (ክህነት ካለበት ሹመት መፍራት የተነሣ) ድንጋጤን ተመልተው፣ ሁለቱ ካህናት አካላቸውን በግልጽ ከቆረጡ በኋላ ከአንቺ በተገኘ ተአምር ምላስንና እጅን አገኙ:: (የተቆረጡ አካሎቻቸው በተአምር ቀድሞ እንደነበሩ ሆኑላቸው):: ይህ ኃይለ ቃልም ቀኝ እጅህ ብታሰናክልህ ቆርጠህ ጣላት፣ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንዱ ቢጠፋ ይሻልሃልና የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል የፈጸመ፣ ነው ማቴ.5 30-31::*

## በብርሃን ስለታጀበው ልጅ፣

(ታሪክ) ክርስቲያን ያልሆነ አንድ ልጅ፣ ከክርስቲያን ልጆች ጋር ላሞችን እየጠበቀ ሳለ፣ እረኞቹ ምሳቸውን ሲበሉ አይቶ አብሯቸው በቀረበ ጊዜ፣ እስከምትጠመቅ ድረስ ከእኛ ጋር አትበላም አሉት እሱም ከእናንተ ጋር እንድሆን ወደ ክርስትና ሃይማኖት አስገቡኝ አላቸው፣ በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከእረኞች አንዱን ክርስቲያን ልጅ አነሳስቶት ከሚጠጡበት ምንጭ ውሃ ጠልቆ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ ማቴ.28. 18-20. ስምህም "ገሪዛን" ይሁን ብሎ አጠመቀው፣ ገሪዛን ማለትም የቡራኬ ቃል የሚነገርበት የተራራ ስም ሲሆን፣ ዘዳ.11.29. የተባረክህ ልጅ ሁን ለማለት ስሙን ገሪዛን ብሎ ጠራው፣ ይህ ልጅም ከተጠመቀ በኋላ

(67) ኢትዮጵያዊው ጻድቅ አባ ዮሐኒ፣ (በ526) ዓ.ም ሚያዝያ (5) ቀን ተወለደ፣ (ከ145-147 ያለ ተአምረ ኢየሱስ እና የቅዱሳን ታሪክ በሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ 1998 ዓ.ም)::

www.ethiopianorthodox.org

በመካከላቸው ገብቶ በላ፣ ማታ ወ[illegible] ቤቱ በገባ ጊዜም አባቱ፣ ፊቱ ብርሃን የተሞላ ሆኖ እና መዓዛው ከሽቱ ሁሉ በልጦ ስላገኘው፣ ይህን መዓዛ ከየት አገኘኸው? አለው፣ ልጁም የክርስቲያን ልጆች እንዳጠመቁት ነገረው፣ ከዚህም የተነሣ አባቱ ልጁን በእሳት ውስጥ ጣለው፣ ነገር ግን የጌታ መልአክ (3) ልጆችን ከእሳት እንዳዳናቸው ዳን.3.9-32 እመቤታችን በተአምር እሳቱን አጥፍታለት ዳነ፣ እናትና አባቱም የልጃቸውን ከእሳት መዳን ከተረዱ በኋላ አምነው ተጠምቀዋል (171 ተአምረ ማርያም)።

## የተቆረጠች እጅ በቅዳሴ ጊዜ ስለማብራቷ፣

(ታሪክ) አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘአንጾኪያ፣ ቀድሞ አረማዊ (ያላመነ) ነበር፣ ኋላ ግን አምኖ ተጠምቆ ተሾሟል፣ በሀገራቸውም የተሾመ ሁሉ አንድ ሳምንት ቀድሶ ያቈርባል። በዚህ ልማድ በመስቀል እየባረከ ሲዞር፣ ቀድሞ በአረማዊነት ሳለ፣ የምታውቀው አንዲት ሴት መስያ ይሁነኝ ብላ እጁን ነከሰችው። በዚህ ጊዜ ጸር (የዝሙት መንፈስ) ተነሳበት፣ ከዚህ ሁሉ ያደረሰችኝ ይህች እጅ አይደለችምን ብሎ ከዕቃ ቤት ገብቶ ቀኝ እጁን በሰይፍ ቆርጦ በልብስ ጠቅልሎ ከመኝታው በታች አኖራት። በነጋውም ምእመናን መጥተው አባታችን! ገብተህ ቀድስልን አሉት፣ አይቻለኝም አላቸው ሁለተኛም ገብተህ ቀድስልን አሉት እንደዚሁ አይቻለኝም አላቸው። ምእመናኑም ይህ ሰው፣ ወደ ቀደመ ግብሩ ተመለሰን? ሲሉ፣ እርሱ ወደ እመቤታችን ቢያመለክት እንደ ፀሐይ የምታበራ እጅ ቀጠለችለት፣ ገብቶም ሲቀድስ የእጁ ብርሃን ዐይን እየበዘበዘ የማያሳያቸው ቢሆን፣ ወጥተው አባታችን! ነገሩ ምንድነው? ግለጽልን አሉት። እሱም ምንጣፉን ግለጡት አላቸውና ቢገልጡት፣ እጁ ከዚያ ወድቃ አዩዋት፣ ያቺ የእኔ እጅ ናት፣ የምታበራዋ ይህቺ እጅ ግን፣ እመቤታችን የሰጠችኝ እጅ ናት ሲላቸው፣ ሁሉም ተደንቀዋል፣ (104 ተአምረ ማርያም ትንሣኤ ዘጉባኤ 1989 ዓ.ም)።

(68) በሕፃንነቱ አራዊት የሰገዱለት አባ ዮሐኒ፣ በተወለደ (በ14) ዓመቱ መነኰሰ፣ ድርሳነ ኤልያስ ግእዝ እትም 1964 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ።



ሁለቱ ካህናት፣ አካላቸውን ቆሬጡ ለሚለው ኃይለቃል አንዱ ታሪክ ይህ ሲሆን፣ ሁለተኛው ታሪክ ደግሞ ከሮሜ ጳጳሳት ውስጥ ጌታን የሚፈራ ስሙ አባስ የሚባል አንድ ካህን ነበር፣ ከታላላቅ በዓላት ውስጥ በአንዲት ቀንም ሥርዓተ ቅዳሴውን ከፈጸመ ፣ በኋላ እንደ ሥርዓቱ አንዲት ሴት የካህኑን እጅ ስትሳለም፣ በልቡናው ውስጥ የሥጋ ፍትወት አደረበትና ልቡናው በዝሙት ጸር ተወጋ፣ ሥርዓቱንም ፈጽሞ ወደ ቤቱ ሄዶ ሰይፍ አንሥቶ እጁን ቆርጦ እመቤቴ ማርያም ሆይ ኃጢአቴን ይቅር በዩኝ እያለ ሲያለቅስ፣ የተቆረጠች እጁ እንደ ቀድሞ ሆናለታለች። ስለዚህ (2ቱ) ካህናት በተአምርሽ ምላስንና እጅን አገኙ አለ። እጅን ምላስ ማለቱም ስለምን ነው? ቢሉ የሰው አንዱ አካል፣ ከታመመና ከተቆረጠ፣ ሁሉም አካል ታማሚ ነውና። 1ኛ.ቆሮ. 12.14-27. (223 ተአምረ ማርያም)።

፬-94 ተአምርኪ ጽጌ ሐና በገጸ ከሲፋ አመ ተዐውቀ፣
ሠረረ ያፍ ነሢአ ዘመጽሐፈ መልእክት ረቀ፣
በትእዛዘ ጽጌኪ (ዚአኪ) ያብጽሕ ብሔረ ርኁቀ፣
ዓሣ ባሕርኒ እንዘ ይጸውር ወርቀ፣
ይጸብት ቀላያተ ወየዐርግ ሐይቀ።

*የሐና አበባዋ የሆንሽ ማርያም ሆይ ተአምርሽ በከሲፋ ፊት በታወቀ ጊዜ፣ በልጅሽ (በአንቺ) ትእዛዝ ወፍ መልእክት ያለበትን ደብዳቤ ይዞ ያደርስ ዘንድ ወደ ሩቅ አገር በረረ፤ የባሕር ዓሣም ወርቅን ተሸክሞ በባሕር ላይ ይዋኛል፣ ወደወደቡም ይወጣል።*

## ስለ መልእክተኛው ወፍ፣

(ታሪክ) በመቄዶንያ አገር የነገሠና ቤተ ክርስቲያንን የሚዘርፍ ከሲፋ የሚባል ንጉሥ ነበር፣ ሰራዊቱ አትሪብ በምትባል አገር በእመቤታችን ስም የተሠራች ቤተ ክርስቲያንን ሊያቃጥሉ ሲሉ፣ ቀሲስ ዮሐንስ የሚባል የገዳሙ አስተዳዳሪ እስከ (3) ቀን ድረስ ጊዜ እንዲሰጡት ሰራዊቱን ለመነና በእመቤታችን ሥዕል ፊት ቆሞ ጸለየ፣ (ከ3) ቀን በኋላም በጥቁር ቀለም የተጻፈች ደብዳቤ ወደ ከሲፋ

(69) አባ ዮሐኒ፣ (በ558) ዓ.ም በተወለደ (በ32) ዓመቱ ኅዳር (5) ቀን ክንፍ አውጥቶ ብሔረ ሕያዋን ገባ፣ ድርሳነ ኤልያስ ግእዝ እትም 1964 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ።

www.ethiopianorthodox.org

ደርሳለች የሚል ቃል ሰማና ተደሰተ:: ይህንን መልእክትም ያደረሰ፣ የነቢዩ ኤርምያስ ደቀ መዝሙር የነበረ የባሮክን የጽሑፍ መልእክት ይዞ ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን እንደ በረረውና የሞተ ሰውን እንዳስነሣው ንስር ሁሉ፣ ተረ.ኤር.11.1-7. ነጭ ወፍ ነበር:: መስፍኑም በድንኳን ውስጥ ከአልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ የፋና መብራት ሲበራ አይቶ ተደነቀ፣ ወፉ የጣለለትን ደብዳቤም አንብቦ ተረዳ፣ በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያኒቱ ሳትቃጠል ቀርታለች፣ (ከ271-275 ተአምረ ማርያም)::

## ወርቅን የያዘ ዓሣ፣

(ታሪክ) በንግድ ሥራ ከሚተዳደርና ስሙ ሚካኤል ከሚባል ዲያቆን፣ ክርስቲያን ያልሆነ አንድ ሰው የጣቱ የወርቅ ቀለበትን አስይዞ ዕቃ ገዛ፣ ዲያቆኑም የእመቤታችንን ሰላምታ በዚሁ በሥራ ቦታው ጸልዮ እስኪመለስ ድረስ፣ ሰውዬው ወርቁን ወስዶ ማንም እንዳያገኘው ከባሕር ጨመረው፣ ቀኑም እመቤታችን ያረፈችበት ጥር (21) ቀን ነበር፣ ዲያቆኑም ከቤቱ ገብቶ ከቤተሰቡ ጋር ምግብ ሲበላ፣ ታናሽ ልጁ ከዓሣ በቀር ሌላ ምግብ አልበላም ብሎ ሲያለቅስ፣ አባቱ ዓሣ ገዝቶ እንደተለመደው ዓሣውን ለምግብነት ለማዘጋጀት ሆዱን ሲቀዱ፣ ሌባው ሰውዬ ወስዶ ከባሕር የጣለው የወርቅ ቀለበት ተገኘ፣ በዚህ ጊዜ ዲያቆኑና ሌባው ሰውዬ እጅግ ተገረሙ፣ ሌባውም ከዲያቆኑ እግር ሥር ወድቆ ይቅር በለኝ፣ የክርስትና ሃይማኖትም እውነተኛ (ትክክለኛ) ሃይማኖት ነው ብሎ አምኖ ተጠመቀ፣ መንኵሶም ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግል ኖሮ በክብር ዐረፈ (ከ307- 308 ተአምረ ማርያም)::

፺፭-95 ጽጌኪ ማርያም ገቢረ ተአምር አመ ወጠነ፣
በትእዛዝኪ አኮኑ ማየ መሳብክት አውየነ፣
ምንተ ገቢረ ቃለ ዚአኪ ዘስዕነ፣
ሶበሰ ትፈቅዲ ከመ ታርእዩ ሥልጣነ፣
ዕብንኒ ኅብስተ እምኮነ::

(70) ቅዱስ ያሬድ፣ ስለ አባ ዮሐኒ ክብር፣ ኅዳር (5) ቀን በሚዘመሩ ድጓ፣ ዝማሬ መዋሥዕት በተባሉ ድርሰቶቹ ብዙ ተናግሯል::



*ማርያም ሆይ ልጅሽ ተአምር መሥራትን በጀመረ (ባሰበ) ጊዜ፣ በአማላጅነትሽ የጋኖችን ውሃ ወይን አድርጎ የለምን? ዮሐ. 2.12.* የአንቺ ተአምር (ኃይልሽ) ምንም ከማድረግ የሚሳነው የለም:: *(የተሳነው! ምን ነገር አለ?)* ተአምርሽን ልታሳዪ ብትወጂስ፣ ድንጋዩ ዳቦ በሆነ ነበር:: (ሐተታ) ተአምርሽን ልታሳዪ ብትወጂስ ድንጋዩ ዳቦ በሆነ ነበር ማለቱ፣ ማድረግ ትችያለሽ ማለቱ ነው::

## እመቤታችን፣ በቃና ሰርግ፣ ወይን እኮ! አልቆባቸዋል ያለችበት ምሥጢር

(ታሪክ) የገሊላ አውራጃ በምትሆንና ቃና በምትባል መንደር (ባቲለስ በምትባል ቀበሌ) ሰርግ ተደረገ፣ ጌታና እናቱ፣ ደቀ መዛሙርቱም ለሰርጉ ተጠርተው ሄዱ፣ የሙሽራውም አባት ስሙ ዮካን ሲሆን፣ የሙሽራው ስም ደግሞ ዶኪማስ ይባላል፣ ለሰርጉ የተጠሩትም ሁሉ ምሳ እየተጋበዙ ሳለ፣ የወይኑ ጠጅ አለቀ፣ እመቤታችንም ልጇንና ፈጣሪዋን ወይን እኮ! አልቆባቸዋል አለችው፣ ጌታም ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት:: ጌታ፣ ጊዜዬ ገና አልደረሰም ያለበት ምክንያትም አምነው የሚቀበሉትና በእውነት የሕወይት መጠጥ የሚሆን ዮሐ.6.53-57. ወይን በደሜ ተለውጦ የሚሰጥበት ጊዜ (የምሰቀልበት ቀን) ገና አልደረሰም ብሎ ከማስረዳቱ ባሻገር፣ ጊዜው ሲደርስ ወይን፣ የደሙ ምሳሌ እንደሚሆን ምሥጢሩን ለመግለጽ ነው፣ ከዚህ በኋላም እመቤታችን አሳላፊዎቹን ልጄ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸውና (በ6) ጋኖች ውሃን ሞሉ፣ ጌታም በጋን የሞላችሁትን ውሃ ለጠጅ አሳላፊዎች (ለአስተናጋጆች) አለቃ ስጡት አለ፣ የአስተናጋጆች አለቃም ወይኑን ቀምሶ አደነቀ:: እንዲሁም እመቤታችን፣ ልጇን ወይን እኮ! አልቆባቸዋል ያለችው ምሥጢር፣ መጽሐፈ ምሥጢር እንደገለጸው ለጊዜው የሰዎችን ምድራዊ ችግር

(71) ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአባቱ ከዘሮንቶስና ከእናቱ ከቴዎብስታ (በ277) ዓ.ም በፍልስጥኤም ውስጥ ልዳ በምትባል አገር ጥር (2) ቀን ተወለደ፣ ዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ በአዜብ በርሄ 1ኛ መጽሐፍ ሚያዝያ 2000 ዓ.ም ሜጋ ቤተ መጻሕፍት::

www.ethiopianorthodox.org

ለመፍታት ነው ፍጻሜው ግን ይህ የቃና ሰርግ የሆነው በአላመኑት ዘንድ ጌታ ከነቢያት አንዱ ነው በሚባልበት ጊዜ እና ቅዱስ ጴጥሮስ፣ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ የልጇን አምላክነት ከመመስከሩ በፊት ነውና። ማቴ.16.13-21. አይሁድና ደቀመዛሙርቱም፣ አምላክነቱን በፍጹም ልብ ገና አላመኑም ነበር። ስለዚህ ልጇ፣ ተአምሩን ይገልጽላቸውና ያምኑበት ዘንድ አስባ ነው። ለዚህ ነው! የምሥጢር ባለቤት የሆኑ ቅዱስ ዮሐንስ እና ቅዱስ ያሬድ፣ ጥር (11) ቀን (የቃና ዋዜማ) ከሚዘመረው፣ በከፊል እንመልከትና! አርአዮሙ ስብሓቲሁ አምኑ ቦቱ አርዳኢሁ፣ "የአምላክነቱን ክብር ገለጸላቸው፣ ደቀመዛሙርቱም አመኑበት" ያሉ። ዮሐ.2.11-12 እና መጽሐፈ ድጓ። በዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያውን ተአምር በአደባባይ አደረገ። የእመቤታችንም አማላጅነቷ በአደባባይ ታወቀ፣ በምን ቢሉ ሰዎች ጌታን ለበዓል ወደ ይሁዳ ሂድ ብለው ቢለምኑት ፈቃዱ ስላልሆነ ጊዜዬ ገና አልደረሰምና፣ ዛሬ አልወጣም ብሎ በገሊላ ቀርቶ ሰዎች ወደ በዓሉ ከወጡ በኋላ ተሠውሮ እንደሄደው ሳይሆን ዮሐ.7.2-11. እናቱ ያለችውን በዚያው ሰዓት በግልጽ ፈጽሟልና ዮሐ.2.1-12፣ ጌታ በቃና ሰርግ የመጀመሪያውን ተአምር አደረገ መባሉም ስለ ምን ነው ቢሉ? በዮርዳኖስ ከተጠመቀና ከገዳመ ቆሮንቶስ ከወጣ በኋላ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በግልጽ ያደረገው ተአምር በቃና ሰርግ ስለነበረ ነው። ሰርጉም የተደረገው በዘመነ ሉቃስ (በ30) ዓ.ም የካቲት (23) ቀን ማክሰኞ ነው። ይህም ጌታ ጥር (11) ቀን ከሊሊቱ (10) ሰዓት

(72) የፊቅጦር እናት ማርታ፣ ጌታ ኀዘኔን አስረሳኝ፣ አስወገደልኝ ለማለት፣ ልጇን ፊቅጦር ብላ ጠራችው (የሚያዝያ 27 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)።



ተጠምቆ ሉቃ.4.1-3. ዕለቱን ገዳም ገብቶ (የ40) ቀኑን ሱባዔ የካቲት (20)፣ ቅዳሜ ፈጽሞ ማለት ነው፣ ሆኖም የውሃ በዓል ከውሃ በዓል (ከጥምቀት በዓል) ጋር ይከበር ብለው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ስለ ወሰኑ ጥር (12) ቀን በቃና ሰርግ ሆነ እየተባለ ይተረካል፣ (ይዘመራል)።

ፃ፮-96 ሶበ አተበ ለማይ በቅዳሴኪ እንዘ ይጼሊ፣
ረሰዮ ኅብስተ ጽጌ ሃይማኖት ዘሐቅለ ዋሊ፣
(ረሰዮ ኅብስተ ጽጌ ሃይማኖት ሳሙኤል ዘሐቅለ ዋሊ)፣
ምሕረተ ወፍትሐ ለተአምርኪ እኅሊ፣
ሥረዪ ኃጢአትየ ወዕሁበየ አትልሊ፣
እስመ ኵሎ ገቢረ ማርያም ትክሊ።

*ማርያም ሆይ ዋሊ በሚባል በረሃ ያለና የሃይማኖት አበባ (ምሰሶ) የሆነ ሳሙኤል፣ በቅዳሴሽ እየጸለየ (ቅዳሴሽን እየጸለየ ውሃውን በባረከው ጊዜ ኅብስት አደረገው፣ ምሕረትና ፍትሕ ያለበት ተአምርሽን አስብ ዘንድ ኃጢአቴን አስተሥርዪልኝ፣ ችግሬንም አቅልሊልኝ፣ አንቺ ሁሉን ማድረግ ትችያለሽና።*

## ውሃውን ባርኮ ኅብስት ስላደረገው ጻድቅ፣

(ታሪክ) ሳሙኤል ከአባቱ ከእስጢፋኖስና ከእናቱ ከእመተ ማርያም በ1295 ዓ.ም መጋቢት (12) ቀን በአክሱም ተወለደ፣ ሳሙኤል ማለትም ልመናዬን ጌታ ሰማኝ ማለት ነው፣ 1ኛ.ሳሙ.1.19-21. የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እየተማረ ሳለ፣ አባትና እናቱ ሲሞቱ፣ መድኃኒነ እግዚእ ወደሚባለው ባሕታዊ ሄዶ (በ18) ዓመቱ መነኮሰ በጾምና በጸሎት እየተጋደለ ከቆየ በኋላ፣ ዋልድባ ወደሚባል ገዳም ገባ። የእመቤታችንን ቅዳሴም ሲጸልይ ከንድ ከስንዝር ያህል ከምድር ወደ ላይ ከፍ ይል ነበር። እመቤታችንም በረድኤት ወደ እርሱ

(73) የበለዓም አህያ፣ አፍ አውጥታ በሰው አንደበት እንደተናገረች ሁሉ፣ ዘኁ.22.21-35፣ 2ኛ.ጴጥ.2.15-17 በነቢዩ ኤርምያስ የተመሰለ ድንጋይ፣ በሰው አንደበት [illegible] 11.53-62 እና የግንቦት (5) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)።

www.ethiopianorthodox.org

*መጥታ የሚያበራ ዕንቍንና ንጹሕ ዕጣንን ሰጠችው፣ ቅዳሴዋንም ደግሞ ውሃውን ቢባርከው ኅብስት ሆኖላቸው ደቀ መዛሙርቱ ተመግበዋል፣* አባ ሳሙኤል፣ ዘዋልድባ እንዲህ ሲያገለግል ኖሮ (በ100) ዓመቱ ታኅሣሥ (12) ቀን ዐረፈ (324 ተአምረ ማርያም እና የቅዱሳን ታሪክ፣ በሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ 1998 ዓ.ም)።

፺፯-97 ቅዳሴኪ ማርያም ጸገየ መለኮተ፣
ወፈረየ ብኪ ለቅዱሳን ቅድሳተ፣
ለላዕካኒሁ እምግዘት ከመ የሀቡ ፍትሐተ፣
አርአዮሙ ለመምህራን ዓበይተ ኃይላተ፣
እንዘ ይገብር ተአምረ ወመንክረ በኀበ ተአኩተ፣
ወለማይኒ ረሰዮ ኅብስተ።

*ማርያም ሆይ ቅድስናሽ አምላክን ለመውለድ አበቃሽ፣ አምላክ ከአንቺ በነሣው ባሕርይም ክብርን አስገኘ። (ከኃጢአት ለነጹ ሁሉ ሥጋውንና ደሙን ሰጠ) ለሐዋርያትም የታሰሩትን ይፈቱ ዘንድ ሥልጣንን ሰጠ፣ ማቴ.18.18. ለመምህራንም ድንቅ ድንቅ ተአምርን እየሠራ በሚመሰገንበት ሥራ፣ ታላላቅ ተአምራትን አሳያቸው፣ ውሃውንም ወደ ወይን ጠጅ ለወጠ።*

፺፰ :-98 ለተአምርኪ ማርያም ኅጥእ ውእቱ ዘአስተቶ፣
ከመ ስብሐቲሁ ኢይርአይ እስመ ጽጌኪ አእተቶ፣
ለተአምርኪሰ እንዘ ይነገር ረድኤቶ፣
በ፡ ዘፈለሰ ኀዲጎ ብእሲቶ፣
ወበ፡ ገዳመ ዘተግኅሠ (ዘወፈረ) መኒኖ መንግሥቶ።

*ድንግል ሆይ ሃይማኖቱን የካደ አንድ ደሃ ሰው፣ በአሳተው በሰይጣን ፊት፣ አንቺን መካድ እንቢ ባለ ጊዜ፣ አንቺን ማመኑ ነፍሱን*

(74) ጸድቃን፣ ድል ባደረጉ ጊዜ ብዙ ክብር አለ (በጻድቃን ጸሎት ብዙ ተአምራት ይደረጋል)፣ ኃጥአን ከፍ ከፍ ባሉ ጊዜ ግን ሰው ይሸሸጋል (በኃጥአን ኃጢአት ብዙ ሰዎች ይጠፋሉ ምሳ. 28.12)።



*ለማዳን ጠቀመችው፣ (ረዳችው) ተአምርሽንና የልጅሽን ቸርነቱንም እየነገረ ከእንቅልፉ ነቅቶ ወደ ቤቱ ገባ።*

## ድንጋዩ፣ ወርቅ መስሎት ሃይማኖቱን ስለካደ ሰው፣

(ታሪክ) መጽሐፍ፣ ቀናተኛ ሰው ባለጸጋ ለመሆን ይቸኩላል፣ ችግር እንደሚመጣበትም አያውቅም፣ ምሳ.28.22.. ምግብና ልብስ ካለን እርሱ ይበቃናል፣ ዘፍ.28.18-22 ያለአግባብ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ስር ነው፣ አንዳንዶችም ማለት የሶርያ ንጉሥ አለቃ የነበረ ንዕማንን እና መምህሩ ኤልሳዕን የዋሸ ግያዝ፣ 2ኛ.ነገ.5.20-27 ፈጣሪንም የሸጠ ይሁዳ ገንዘብን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳሳቱ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ማቴ.26.14. 1ኛ.ጢሞ.6.6-11. ያልተገነዘበ አንድ ባለጸጋ ሰው፣ ገንዘቡ ባልቀበት ተከብሬ በኖርኩበት አገር ተዋርጄ አልኖርም ብሎ አገር ጥሎ ሲሄድ፣ሰይጣን ከጎዳና ቆይቶ ድንጋዩን ወርቅ አስመስሎ ሰጥቶ፣ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስን ካድልኝ አለው፣ ካደለት፣ መላእክት፣ጻድቃን፣ ሰማዕታትም አያማልዱም በል አለው፣ እሱም አያማልዱም አለ። በኋላም ሰይጣን ማርያም፣ ወላዲተ አምላክ መሆኗን ካድልጅ ሲለው፣ እሷንስ አልክድም አለው። በዚህ ጊዜ ሰይጣን ወርቅ አስመስሎ የሰጠውን ድንጋይ ተቀብሎ መትቶ ገደለው። ይህ ሰውም በእመቤታችን አማላጅነትና በጌታ ፈቃድ፣ ነፍሱ ከሥጋው ተዋሕዳ የአንድ ባለጸጋ ልጅ አግብቶ የእመቤታችንን ስሟን እየጠራና ዝክሯን እየዘከረ ሲያገለግል ኖሮ በክብር ዐርፎ መንግሥተ ሰማያትን ወረሰ። ይህ ታሪክ በቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ. ምዕ. 2.ቍ. 9. ወስሉጥ ስምኪ በኀበ እግዚአብሔር "ስምሽ በእግዚአብሔር ዘንድ በማማለድ የሰለጠነ ነው" ከሚለው እና ከ380- 381 ድረስ ከአለው ተአምረ ማርያም የተወሰደ ነው። በተመሳሳይ ታሪክም ቅፍጥ በሚባል አገር በሀብት እጅግ የከበረና ስሙ ጥብርያዶስ የሚባል አንድ ነጋዴ ነበር፣ ክብሮ (ገኖ) ብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ፣ዘመን ተለወጠበትና ገንዘቡ ሁሉ አለቀ፣ አኗኗሩም ጎሰቆለ፣ ስለዚህ ወደ

(75) በደብረ ዘይት ተራራ ላይ የቆመ እና ስሙ ከዋኒት (ከዋኒት) የሚባል ድንጋይ፣ ጌታ [illegible] ተንቀሳቅሶ ምን ተናገረ? →

www.ethiopianorthodox.org

ሌላ አገር ሄጀ እየነገድኩ እኖራለሁ ብሎ እያዘነ ሲሄድ፣ ሰይጣንበመንገድ አገኘውና ወንድሜ ሆይ ለምን ታዝናለህ? ለምንስ ታለቅሳለህ አለው፣ ጥብርያዶስም ያገኘኝን እነግርህ ዘንድ አንተ ማነህ? አለው፣ እኔ ሰይጣን ነኝ አለው፣ ጥብርያዶስም አንተ ሰይጣን ስትሆን ልትረዳኝ ይቻልሃልን? አለው፣ ሰይጣንም አዎን ብሎ ለጥብርያዶስ ሁለት ዕንቍዎችን ሰጠውና ክርስቶስን፤ መላእክትን፣ ማርያምን፣ ጻድቃንን፣ ሰማዕታትን ሁሉ ካድልኝ አለው፣ ጥብርያዶስም የነገሩን ፍጻሜ በሰማ ጊዜ፣ እመቤታችን! የሰማይና የምድር ንግሥት ናትና፣ እሷን አልክድም እንጂ ሁሉንም እክዳለሁ አለው፣ ሰይጣንም ማርያምን ካልካድካትስ የምትሠራው ሁሉ አይረባህም ብሎ ከእሱ ተሠወረ፣ ሰይጣን የሰጠውን ዕንቍም ቢያይ፣ ወዲያው ተለውጦ የድንጋይ ጠጠር ሆነበት፣ ገንዘቤን አጥፍቼ፣ ፈጣሪዬንና ሃይማኖቴን ክጄ፣ ወዮታ አለብኝ እያለና እያዘነ ሲሄድ፣ በእመቤታችን ስም የታነጸች ቤተ ክርስቲያንን አግኝቶ በሥዕሏ ፊት እያለቀሰ ከልጅሽ አማልጅኝ አለ፣ በእንቅልፍ ላይም እያለ እመቤታችን ጥብርያዶስን እንዲምርላት (በደሉን ይቅር እንዲልለት) ልጅዋንና ፈጣሪዋን ተማፀነችው፣ ጌታም ይህ ሰው ተጸጽቶ በመመለሱ ምሬዋለሁ አላት፣ እመቤታችንም ሁለተኛ አትበድል አለችውና ከእርሱ ተሠወረች፣ እርሱም (ጥብርያዶስ) ወደ ገዳም ሄዶ መንኵሶ ሲያገለግል ኖረ፣ (211 ተአምረ ማርያም)።

፺፱-99 ለብእሲት ብዙኃ ዘአፍቀረቶ ወቀብዐቶ ዕፍረተ በእዴሃ፣
ከመ ኃጢአታ ኀደገ በከመ ጽጌኪ ፊትሐ፣
ኀድጊ ሊተ ማርያም ኃጢአትየ ብዙኃ፣
ፀረ ተአምርኪሰ እመኒ ነስሐ፣
እምኃጢአቱ ኢይረክብ ንጽሐ።

*ማርያም ሆይ እጅግ ለወደደችውና በእጅዋ ሽቱን ለቀባችው ሴት ልጅሽ ኃጢአቷን ይቅር ብሎ እንደፈረደላት ሁሉ ማቴ. 26. 6 -14.*

(76) ከዋኒት (ከዋኒት) የሚባል ድንጋይ፣ በይሁዳ ራስ ላይ እየተሽከረከረና ጌታን አሳልፈህ የምትሰጥ ይሁዳ ሆይ ወዮልህ እያለ እንደ በለዓም [illegible] 22.21-[illegible] እንደበት መሰከረ ማቴ.26.14 ንባቡና ትርጓሜው፣(82ኛ ተአምረ ኢየሱስ እና፣



*ብዙ ኃጢአቴን ይቅር በዪኝ፣ የተአምርሽ ጠላት የሆነ ግን ንስሓ ቢገባም ሥርየትን አያገኝም።* (ሐተታ) የተአምርሽ ጠላት የሆነ ንስሓ ቢገባም ሥርየትን አያገኝም ማለቱ፡-

1. በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ በሰማይና በምድር ያሉ ሁሉ በእርሱ (በኢየሱስ ክርስቶስ) ተፈጠሩ፣ ከሆነውም ሁሉ አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም ዘፍ.1.1፣ ዮሐ.1.1-6፣ ቈላ.1.15-22፣ እኛ አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለመውረስ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን፣ ኤፌ.2.10-11፣ ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፤ በወልድ የሚያምን ደግሞ አብ አለው፣ የዘለዓለም ሕይወትም አለው። የማያምን ግን፣ ሕይወትን አያይም፣ 1ኛ.ዮሐ.2.21-22፣ ዮሐ.3.35፣ ⌣ እናንተ ከታች (ፍጡራን) ናችሁ እኔ ከላይ (ፈጣሪ) ነኝ ብሎ እርሱ ራሱ ፈጣሪ እንደሆነ ለአይሁድ ማስረዳቱን መጻሕፍት እየመሰከሩ ዮሐ.8.21-24 አርዮስ፣ ወልድ ፍጡር ነው በማለት፣
2. የእግዚአብሔር (የአብ) ቸርነት ምድርን ሞላ፣ በእግዚአብሔር (በወልድ) ቃል፣ በአፉ እስትንፋስ (በመንፈስ ቅዱስ) ሰማዮችና ሠራዊቶቻቸው ሁሉ ፀኑ (ተፈጠሩ)፣ ዘፍ.1.1-3፣ መዝ.32.4-7. አንድ ሰው ወደ እግዚአብሐር መንግሥት ሊገባ የሚችል በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኖ ሲጠመቅ ብቻ መሆኑ (መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደሆነ) እንዲህ እየታወቀ፣ ዮሐ.3.3-8፣ ማቴ.28.19፣ መቅዶንዮስ፣ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ያንሳል በማለት፣
3. በነቢይ፣ ድንግል ትፀንሳለች የተባለላትን፣ ወንድ ልጅ ተወለደልን፣ ስሙም ድንቅና ኃያል አምላክ ነው የተባለለትን፣ ኢሳ.7.14-9፣9.6-9 ዘርሽን አበዛዋለሁ፣ ከብዛቱ የተነሣም አይቈጠርም እንደተባለችው እንደ ግብፃዊቷ አጋር ያይደለችውን፣ ዘፍ.16.5-12. በሰማይ እናት፣ በምድር አባት፣

(77) ድንጋዮች፣ ሆሳዕና በአርያም (በሰማይ ላለ ጌታ ምስጋና ይሁን) እያሉ ከኢየሩሳሌም ሕፃናት ጋር በሰው አንደበት ዘመሩ ሉቃ. 19.28-41 (78ኛ ተአምረ ኢየሱስ 1998 [illegible])።

www.ethiopianorthodox.org

ተቀዳሚና ተከታይ (ታላቅ፣ ታናሽ ወንድምና እኅት) ለሌለውና በዘር (በሰው ልማድ) ሳልበዛና ለማይባዛ፣ ነገር ግን ምሕረቱ ለሚበዛና ቸርነቱ ለማይቈጠር አምላክ የድንግልና እናቱ ልትሆን የተመረጠችውን፣ አራት ልጆችን ወልዳ መውለድ ከአቋረጠች በኋላ በልጆቿ ተመክታ ሴቶች ያመሰግኑኛል እንዳለች እንደ ልያ እና ልጅ ካልሰጠኸኝ እሞታለሁ ብላ ባሏ ያዕቆብን እንዳስጨነቀች እንደ ራሔል፣ ዘፍ.29.31-35 እና 30.1-14፣ ልጅ ስጠኝ ብላ ዮሴፍን ያላስጨነቀችውን፣ (የዚህ ዓለም ሐሳብ የሌላትን)፣ በቅዱስ ገብርኤል እና በቅድስት ኤልሳቤጥ፣ አንች ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የተባለላትን፣ ከእርሷ የተፀንሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና፣ ዮሴፍ ሆይ እጮኛህ ማርያምን ለመውሰድ (በመንፈስ ቅዱስ የሆነውን ነገር ለመቀበል) አትፍራ ተብሎ አምላክነቱ የተረጋገጠለትን፣ በእናቱ ማህፀን ያለ የ6 ወር ፅንስ እንኳ ሳይቀር የሰገደለትን ጌታ በማህፀኗ ተሸክማ፣ ታሪኩን ከላይ እንደተመለከትነው እንደልያ ሳትመካ (ሴቶች ብቻ ብፅዕት ይሉኛል ሳትል) በማህፀኔ ያለው የትውልዱ ሁሉ ፈጣሪ ነው ለማለት፣ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ብላ አቢዳራ በሚባለው ሰው ቤት (3) ወር ለቆየችው ታባተ ሕግ 2ኛ.ሳሙ.6.1. ምሳሌ ሆና በዘካርያስ ቤት (3) ወር ቆይታ ሉቃ.1.26-57. ትንቢቱ ሁሉ ተፈጽሞላት አምላክን የወለደች ድንግል ማርያምን ማቴ.1.18-25. ንስጥሮስ፣ ሰውን እንጂ አምላክን አልወለደችም ብሎ የአምላክ እናት መሆንዋን ክደዋልና ነው::

(1) ሎቱ ስብሐት (ለእግዚአብሔር ወልድ ምስጋና ይግባውና) ቄስ የነበረው እና በ318 ዓ.ም ወልድ ፍጡር ነው ብሎ የተነሳው አርዮስ፣ አባታችን አብርሃም፣ አሕዛብን ድል አድርጎ ምርኮን በመለሰባቸው በ318 ቤተሰቦቹ ዘፍ.14.10-17 በተመሰሉ፣ በ318

(78) በምድር የምታስሩት ሁሉ፣ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድር የምትፈቱትም ሁሉ፣ በሰማይ የተፈታ ይሆናል ሲል፣ ጌታ ለሐዋርያት (ለካህናት) ሥልጣነ ክህነትን ሰጠ ማቴ.18.18::



ኤጲስቆጶሳት (በሊቃውንት) በ325 ዓ.ም ኅዳር (9) ቀን፤

(2) ሎቱ ስብሐት (ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይግባውና) የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው መቅዶንዮስ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ አይደለም ብሎ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በመካዱ፣ በቍስጥንጥንያ ጉባኤ በ150 ኤጲስቆሳት በ381 ዓ.ም የካቲት (1) ቀን፤

(3) ላቲ ስብሐት (ለቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋና ይግባትና) ሊቀ ጳጳስ የነበረው ንስጥሮስ፣ ድንግል ማርያም ሰው እንጅ አምላክን አልወለደችም ብሎ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ መሆኗን በመካዱ፣ *በኤፌሶን ጉባኤ በ200 ኤጲስቆጶሳት በ431 ዓ.ም መስከረም (12) ቀን ተወግዘው ከቅድስት ቤተክርስቲያን መለየታቸውም ይታወቃል::(የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ አዘጋጅ አባ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ፣ 1978 ዓ.ም)::*

## ጌታ ሴቲቱ ሽቱውን ለመቃብሬ ጠበቀች ለምን አለ?

(ታሪክ) ብዙ ጊዜዋን በዝሙት ያሳለፈች፤ የአልዓዛር እኅት የሆነችና ስሟ ማርያም የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፣ ከዕለታት አንድ ቀን መልኳን በመስተዋት አይታ ይህ መልክ እንደ ጧት ጤዛ ጠፊና ረጋፊ መሆኑን ተገንዝባ፣ወደ ንስሓ መመለስ አሰበችና ጌታ ወዳለበት ሄዳ በብዙ ገንዘብ የተገዛ ሽቱን ወስዳ እግሩን እየቀባች ስታለቅስ፣ አንቺ ሴት ኃጢአትሽ ተሠርዮልሻል እምነትሽ አዳነሽ ብሎ ከበደሏ አነጻት:: (ማቴ.26.6-14፣ የካቲት (6) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር):: ይህች ሴትም የጌታን እግር የቀባችው (በ33) ዓ.ም መጋቢት (21) ቀን ቅዳሜ ሲሆን፣ ጌታ ይህች ሴት ሽቱውን ለመቃብሬ ቀን ጠበቀችው ማለቱም ማቴ.26.12 (ከ6) ቀን በኋላ እንደሚሞትና እነ መግደላዊት ማርያም ሽቱን ይዘው ወደ መቃብሩ የሚገሰግሱበትን ምሥጢር መግለጽ ነው::

(79) ከእግዚአብሔር ባለሟሎች (ከቅዱሳን) ክብር የተነሣ፣ ንስር የሞተ ሰውን አስነሣ ተረ.ኤር.11.1-7.::

www.ethiopianorthodox.org

፻-100 ዮሳ፣ ወልደ-ዮሴፍ ምንተ ገብረ ኃጢአተ፣
ዘያደነግጸኪ ዜና በእንተ ዘአምጽአ (እንበለ ዘአሞጽአ) ግብተ፣
አኮኑ ጻድቅ በትእዛዘ ጽጌኪ ሞተ,
ለምንት ድንግል ታረምሚ ወታበዝኂ ትዕግሥተ፣
ፀረ ተአምርኪ ለአውዕዮ አዝንሚ እሳተ::

*ድንግል ሆይ ዮሳ የተባለው የዮሴፍ ልጅ የሚያስደነግጥሽን ዜና በድንገት ስለ አመጣ ነው እንጂ፣ (ከማምጣቱ በቀር)፣ ምን ኃጢአትን ሠራ? ጻድቁ (እውነተኛው) ዮሳ እንኳ በልጅሽ ፍርድ ሞቶ የለምን? ለምን ዝም ትያለሽ? ትዕግሥትንስ ለምን ታበዣለሺ? የተአምርሽ ጠላት የሆነውን ለማጥፋት እሳትን አዝንሚ እንጂ::*

ከአነጋገር ጉድለት የመጣ መቅሠፍት፣

(ታሪክ) ንጉሥ ሄሮድስ (በ2) ዓ.ም ሕፃናትን ለመግደል በተነሳ ጊዜ፣ ዮሴፍና እመቤታችን፣ ጌታን ይዘው ወደ ግብፅ ሲሸሹ፣ ጊጋር በሚባለው ሰው ቤት ሰነበቱ፣ የዮሴፍ ልጅ ዮሳም ታሞ ከጊጋር ቤት ነበረና፣ የጊጋር ቤተሰቦች በሄሮድስ ሰራዊት ሲፈለጉ ሰምቶ፣ ወደእነ ዮሴፍ ሄዶ የሄሮድስ ሰራዊት ወደእነሱ እየገሠገሡ መሆኑን ሲነግራቸው፣ እመቤታችን ደንግጣ ምርር ብላ ብታለቅስ፣ ጌታ «ዮሳ» አመጣጥህ ዋጋ የሚያሰጥ መልካም ነው:: ነገር ግን እናቴን ስለ አስደነገጥካት በምጽአት ጊዜ መጥቼ መልካም ዋጋህን እስክከፍልህ ድረስ ይህችን ድንጋይ ተንተርሰህ ተኛ ብሎት ከዚያው አርፏል፣ (ነገረ ማርያም የተባለ መጽሐፍ ግእዝና አማርኛ ተስፋ ገ/ሥላሴ 1991 ዓ.ም):: የዮሳ ሞትም (በዮሳ ላይ የተሰጠው ፍርድ) ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር የተነጻጸረ ነው፣ ይህም ከዕለታት አንድ ቀን እስራኤል ውሃ ተጠምተው ሙሴ! ውሃ፣ ሙሴ! ውሃ እያሉ ሲዘበዝቡት፣ ሙሴ ደክሞት ቀድሞ መናውንና ውሃውን ሲሰጣቸው ይጸልየው የነበረውን ንሴብሖ (እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን) የሚለውን ምስጋና ዘጸ.15.1-20. ሳይጸልይ (ጌታን ሳያመሰግን) ምግባቸውን በመስጠቱ፣ ጌታ ተቈጥቶ ወዳጆቹ የሆኑ

(80) ከቃልህ የተነሳ ይፈረድልሃል፣ ከቃልህ የተነሣም ይፈረድብሃል ማቴ.12.36



ሙሴንና አሮንን ምድረ ርስት (ከነዓን) አትገቡም እንዳላቸውና ዘኍ.20.1-14. ሳይገቡ እንደቀሩት ያለ ታሪክ ነው፣ (መዝ. 105.32-33. ንባቡና ትርጓሜው):: ጌታም በኋላ ከቃልህ የተነሳ ይፈረድልሃል፣ ከቃልህ የተነሣም ይፈረድብሃል የምትል ሕገ ወንጌልን የሚያስተምር ነውና፣ እርሱ ባወቀ በዮሳ ላይ ፍርድ ሰጥቷል:: ማቴ.12.36:: ዮሳ፣ የተባለው ሰውም፣ አባቱ ዮሴፍ ከሞተች ሚስቱ ቀድሞ ከወለዳቸው ልጆች አንዱ ሲሆን፣ (ማቴ.13.55-57 እና 18 ተአምረ ማርያም):: ልጅ ሆይ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ፣ በገሠጸህም ጊዜ አትማረር እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና ተብሎ እንደተጻፈ (ምሳ. 3.11-15)፣ ዕብ. 12.5-7. እነሆ ዋጋው (ለጻድቃን የሚሰጠው ክብር) በፊቱ የሆነ ጌታ ኢሳ. 40.10. ዮሳን በሥጋ ቢቀጣው በነፍስ ዋጋን (የጽድቅን ተስፋ) እንደሰጠው ከላይ ታሪኩን ተመልክተናል::

፻፩-101 ዘያስተሐቅር ተአምረኪ ወኢይፈርህ መርገመ፣
ሰይጣን (ሰይጣነ) ወልዶ መስተቃርነ አቀመ፣
ጸግዮ አሥዋከ ከመ ኢይፍረይ ዳግመ፣
ፈንዊ ድንግል (ላዕሌሁ) ጕድበ ሞት ግሩመ፣
ምስለ አዕፁቂሁ ዘይገዝም ፀላዔኪ ያመ::

*ድንግል ሆይ ተአምርሽን የሚያቃልል እና ርግማንን የማይፈራን ሰው፡ ሰይጣን፣ የበጎ ሥራ ተቃራኒ የሆነ ልጁን አድርጎ ሾመ፣ (ተአምርሽን የሚያቃልል እና ርግማንን የማይፈራ ሰው፣ ሰይጣንን እንደ ልጁ አድርጎ ተካ)፣ እሾህንም አብቦ ዳግመኛ እንዳያፈራ ከቅርንጫፎቹ ከአጋንንት ጋር ጠላትሽ ዛፍን የሚቆርጥና የሚያስፈራ ገጀሞ (መጥረቢያ) ሞትን ላኪበት::*

የክፍል ሁለት ማኅሌተ ጽጌ ትርጕምና ታሪክ
በእግዚአብሔር ቸርነት ተፈጸመ::

(81) ... እና ዘካርያስ) ጌታ (በ30) ብር ይሸጣል ብለው ትንቢት ... ዘካ.11.4-15፣ ጌታ (በ30) ብር ...

www.ethiopianorthodox.org

## (ዋቢ መጻሕፍት)


- ማኅሌተ ጽጌ፣ ግእዝ ትንሣኤ ዘጉባኤ 1941 ዓ.ም አዲስ አበባ፣
- መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ኪዳነ-ወልድ ክፍሌ 1948 ዓ.ም፣
- ድርሳነ ኤልያስ፣ ግእዝ እትም ትንሣኤ ዘጉባኤ 1964 ዓ.ም አዲስ አበባ፣
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አማርኛ 1974 ዓ.ም፣
- ገድለ አቡነ ዜና ማርቆስ የብራና፣
- የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ በዓለም መድረክ አዘጋጅ አባ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ 1978 ዓ.ም፣
- በተለያዩ አድባራትና ገዳማት የሚገኙ የብራና ተአምረ ማርያም፣
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ 81 አማርኛ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ 1980 ዓ.ም፣
- መዝሙረ ዳዊት፣ ንባቡና ትርጓሜው ተስፋ ገ/ሥላሴ 1980 ዓ.ም አዲስ አበባ፣
- መኃልየ ሰሎሞን ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ዘጉባኤ 1988 ዓ.ም፣
- ባለ 402 ተአምር፣ተአምረ ማርያም ግእዝና አማርኛ ተስፋ ገ/ሥላሴ 1988 ዓ.ም፣
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት 1988 ዓ.ም አዲስ አበባ፣
- ቅዱስ ወንጌል ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት 1988 ዓ.ም አዲስ አበባ ፣
- የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት 1988 ዓ.ም አዲስ አበባ፣
- መጽሐፈ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት 1990 ዓ.ም አዲስ አበባ፣
- መጽሐፈ ስንክሳር ግእዝ እና አማርኛ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ 1993 እና 1994 ዓ.ም፣
- የትንቢተ ኤርምያስ ትርጓሜ አሳታሚ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት 1997 ዓ.ም አዲስ አባባ፣


(82) አባ ሳሙኤል፣ ዘዋልድባ (በ100) ዓመቱ ታኅሣሥ (12) ቀን ዐረፈ (324 ተአምረ ማርያም እና የቅዱሳን ታሪክ፣ በሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ 1998 ዓ.ም)።




- የመጽሐፈ ዳንኤል እና የ12ቱ ደቂቀ ነቢያት ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ዘጉባኤ 1998 ዓ.ም፣
- ገድለ ሐዋርያት ግእዝ እና አማርኛ አዘጋጅ ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም 2ኛ እትም 1998 ዓ.ም፣
- የነቢያትን ታሪክ በተመለከተ የዓመተ ዓለም አቈጣጠር የ12ቱ ደቂቀ ነቢያት ትርጓሜ መግለጫ (መግቢያ) 1998 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ፣
- የቅዱሳን ታሪክ፣ በሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ 1998 ዓ.ም፣
- ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን 1998 ዓ.ም፣
- መጽሐፈ አክሲማሮስ ግእዝና አማርኛ 1999 ዓ.ም አዘጋጅ እና አሳታሚ አባ ሠናይ ምስክር ባሕር ዳር ማተሚያ ቤት፣
- ዝክረ ቅዱሳን፣ ዘተዋሕዶ በአዜብ በርሄ (1ኛ) መጽሐፍ ሚያዝያ 2000 ዓ.ም ሜጋ ቤተ መጻሕፍት፣
- መጽሐፈ ምሥጢር፣ ግእዝ እና አማርኛ ትርጉም መምህር ኅሩይ ኤርምያስ እትም መጋቢት 2001 ዓ.ም አሳታሚ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እና የአባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣
- መልክአ ጉባኤ (ግእዝ፣ ማኅሌተ ጽጌ)፣ አዘጋጅ መጋቤ አእላፍ ሄኖክ ወልደ ሚካኤል በጎንደር የደብረ ኃይልና የደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም የአቋቋም ምስክር ጉባኤ ቤት መምህር 2002 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣
- ገድለ አዳም አማርኛ አሳታሚ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች፣ ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን 2002 ዓም አዲስ አበባ፣
- የቅዱስ ያሬድ የድጓ ባህል የእጅ ጽሑፍ (ያልታተመ)።


(83) ንስሓ የሚለው ቃል ነስሐ ተጸጸተ፣ተመለሰ ከሚለው ግእዝ የተገኘ ሲሆን ንስሓ ማለት ጸጸት፣መመለስ፣መቀጣት ማለት ነው።

www.ethiopianorthodox.org

# ምስጋና

- ይህ መጽሐፍ፣ ለቤተ-ክርስቲያን አስፈላጊ መሆኑን አምኖበት ለሥራው ቅድሚያ በመስጠት፣ በሊቃውንት ጉባኤ እንዲመረመር ላደረገ ለመ'ንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት፣
- ይህን መጽሐፍ፣ በተደጋጋሚ መርምሮና አስተካክሎ ለኅትመት እንዲበቃ ላደረገ፣ ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ፣
- ይህን መጽሐፍ፣ በግል ተመልክተውና ሊያዩትም ይገባል፣ ብለው ላመኑባቸው ሊቃውንት፣ ላስመረመሩ፣ ለዶ/ር አባ ኃይለ ማርያም መለሰ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል መምሪያ ዋና ኃላፊ፣
- ጊዜውን መሥዋዕት አድርጎ፣ ይህን መጽሐፍ መርምሮ ለኅትመት እንዲበቃ ላደረገ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ለማኅበረ ቅዱሳን፣መጻሕፍት ምርመራ ክፍል፣

በኮምፒዩተር ጽሑፍ ለተባበሩን እኅቶች፦

- ለወ/ሮ አቡና ታከለ (ወለተ ማርያም) ከወሎ ላስታ ላሊበላ፤
- ለወ/ሪት የሺህ ሐረግ ይመር በምሥራቅ ኢትዮጵያ በኦሮምያ ክልል ከሚገኘው ከደብረ ኃይል ጭናክሰን ቅዱስ ገብርኤል፤
- ለወጣት ትርሐስ ሺሻይ (ወለተ መስቀል) ከምዕራብ ትግራይ ሽሬ እንዳሥላሴ ከተማ፤ ይህ መጽሐፍም፣ ለኅትመት እስከበቃበት ድረስ የኮምፒዩተር ሙሉ እገዛ ላደረጉልን ለአቶ አካሉ ቢረዳ (ወልደ ጊዮርጊስ) እና ለባለቤታቸው ለወ/ሮ ፀሐይ ወልደ ሐዋርያት (ወለተ መስቀል) ከጉራጌ ምሁር፣ ቦጠቅላላ ለረዱን ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ መልካም ጤናንና ረጅም ዕድሜን ይስጥልን።

ትርጉም፦ ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያብል፣
አዘጋጅ፦ ዶር.ጋለም ወሰኑ።

www.ethiopianorthodox.org